## መቅድም

ኦሪት ዘኍልቍ፣ ዜና ዘኍልቍ ሲል ነው፣ የእስራኤልን ቍጥር የሚናገር መጽሐፍ ይህ ነው፤ ኦሪት ዘፀዓት፣ የአበውን (የአባቶችን) ነገር ይናገራል፤ ኦሪት ዘኍልቍ፣ የውሉድን (የልጆችን) ነገር ይናገራል፣ ይህንንም ሠለስቱ ምእት ለመጻሕፍት አርእስት ሲሰጡ ሰጥተውታል፣ እርሱ ግን ነገሩን ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ብሎ ያመጣዋል፤

## ምዕራፍ ፩

፩፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ በገዳም ዘሲና በውስተ ደብተራ ዘመርጡል አመ ርእሰ ሠርቀ ካልእ ወርኅ በካልእት ዓመት እምዘወፅኡ እምድረ ግብጽ፣

እስራኤል ከግብጽ በወጡ በሁለተኛው ዓመት በሁለተኛው ወር በግንቦት መባቻ በሲና ምድረበዳ ልዩ በሆነች ድንኳን እግዚአብሔር ሙሴን ተነጋገረው፤ ዘመን የሚለውጡ በሚያዝያ ነውና ግንቦትን ለሚያዝያ ካልዕ አለው፤

፪፤ ወይቤሎ አኅዙ እምጥንቱ ወኍልቍዎሙ ለኵሉ ተዓይነ ደቂቀ እስራኤል በበነገዶሙ ወበበቤተ አበዊሆሙ ወበበአስማቲሆሙ ለለአሐዱ አሐዱ፤

የእስራኤልን ልጆች ሠራዊት ሁሉ ከሮቤል ጀምራችሁ በየነገዳቸው፣ በየአባቶቻቸው ወገን በየስማቸው፣ አንዱንም አንዱን ቍጠሯቸው አለው፤

፫፤ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ፀብዓ እምኃይለ እስራኤል ወአስተፋቅድዎሙ በበኃይሎሙ አንተ ወአሮን፣

ከእስራኤል ሠራዊት ወደ ሰልፍ የሚወጣውን ሁሉ እስከ ሃያ አምስት ዓመት የሆነውን ወንድ ወንዱን ሁሉ አንተና አሮን በየሠራዊታቸው ቍጠሯቸው አለው፤

፬፤ ወየሀልዉ ምስሌክሙ አሐዱ አሐዱ እመላእክተ ነገዶሙ እለ እምአብያተ አበዊሆሙ፣

ከአባቶቻቸው ወገኖች ከሚሆኑ ከነገዳቸው አለቆችም የተመረጡ አንዳንዱም አንዱ ከናንተ ጋር ይኑሩ፤



፭፤ ወዝንቱ ውእቱ አስማተ አበዊሆሙ ወአስማቲሆሙ ለውእቶሙ ዕደው እለ መጽኡ ምስሌሆሙ፤

ከነርሱ ጋር የመጡት ሰዎች ስምና የአባቶቻቸውም ስም ይህ ነው፤

ዘእምሮቤል ኤሌሱር ወልደ ሴድዩር፣

ከሮቤል ነገድ የተመረጠው የሴድዩር ልጅ ኤሌሱር ነው፤

፯፤ ወዘእምስምዖን ሰላምያል ወልደ ሴሩሳዴ፣

ከነገደ ስምዖን የተመረጠው የሴሩሳዴ ልጅ ሰላምያል ነው፤

፰፤ ወዘእምይሁዳ ነአሶን ወልደ አሚናዳብ፣

ከነገደ ይሁዳም የተመረጠው የአሚናዳብ ልጅ ነአሶን ነው፤

፱፤ ወዘእምይሳኮር ናትናኤል ወልደ ሰገር፣

ከነገደ ይሳኮርም የተመረጠው የሰገር ልጅ ናትናኤል ነው፤

፲፤ ወዘእምዛብሎን ኤልያብ ወልደ ኬሎን፣

ከዛብሎን ነገድ የተመረጠው የኬሎን ልጅ ኤልያብ ነው፤

፲፩፤ ወዘእምትውልደ ዮሴፍ ዘእም ኤፍሬም ኤልስማ ወልደ ሰምዩድ፤

ከዮሴፍ ልጅ ከኤፍሬም ነገድ የተመረጠው የሰምዩድ ልጅ ኤልስማ ነው፤

፲፪፤ ወዘእምናሴ ገማልያል ወልደ ፈዳሱር፣

ከምናሴ ነገድ የተመረጠው የፈዳሱር ልጅ ገማልያል ነው፤

፲፫፤ ወዘእምብንያም አቢዳን ወልደ ጋድዮን፣

ከነገደ ብንያም የተመረጠው የጋድዮን ልጅ አቢዳን ነው፤

፲፬፤ ወዘእምዳን አክያዜር ወልደ ሳሚሳዲ፣

ከነገደ ዳንም የተመረጠው የሳሚሳዲ ልጅ አክያዜር ነው፤

ወዘእምአሴር ፋጋኤል ወልደ አክራን፣

ከነገደ አሴር የተመረጠው የአክራን ልጅ ፋጋኤል ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፬፤ ወዘእምጋድ ኤልሳፍ ወልደ ራጉኤል፤

ከነገደ ጋድ የተመረጠው የራጉኤል ልጅ ኤልሳፍ ነው፤

፲፭፤ ወዘእምንፍታሌም አኪሬ ወልደ ኤናን፤

ከንፍታሌም ነገድ የተመረጠው የኤናን ልጅ አኪሬ ነው፤

፲፮፤ እሉ እሙንቱ ኅሩያነ ተዓይኒሆሙ ወመላእክተ ነገዶሙ ዘበበአዝማዲሆሙ ወመሳፍንቲሆሙ ለእስራኤል እሙንቱ፤

በየወገኖቻቸው የሚጠሩ ከየነገዳቸው የተመረጡ የእስራኤል አለቆች እሊህ ናቸው እሊህም የእስራኤል ገዥዎች ናቸው፤

፲፯፤ ወነሥእዎሙ ሙሴ ወአሮን ለእሉ ዕደው እለ ተሰምዩ በበአስማቲሆሙ፤

በየስማቸው የተጠሩ እሊህን ሰዎች ሙሴና አሮን ወሰዷቸው፤

፲፰፤ ወአስተጋብኡ ኵሎ ተዓይነ አመ ርእሰ ሠርቀ ወርኅ ካልእ በካልእ ዓመት ወኍለቍዎሙ በበነገዶሙ ወበበአዝማዲሆሙ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ለኵሉ ተባዕቶሙ በበርእሶሙ፤

በሁለተኛው ዓመት በሁለተኛው ወር መባቻ ሠራዊቱን ሁሉ ሰብስበው በየነገዳቸው በየዘመዶቻቸው በየስማቸው ቍጥር ከሃያ ዓመት ጀምሮ፤ ከሃያ ዓመት በላይ ያለውን ወንድ ወንዱን ሁሉ በየራሳቸው ቈጠሯቸው፤

፲፱፤ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ወኍለቍዎሙ እሙንቱ በደብረ ሲና፤

እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው እነሱም በደብረ ሲና ቈጠሯቸው፤

፳፤ ወኮኑ ደቂቀ ሮቤል በኵሩ ለእስራኤል በበትውልዶሙ ወበበሕዘቢሆሙ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ወበበርእሶሙ ኵሉ ተባዕቶሙ ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኃይል፤

የያዕቆብ የበኵር ልጁ የሮቤል ልጆች በየትውልዳቸው፤ በየወገኖቻቸው፤ በየአባቶቻቸው ወገኖች፤ በየስማቸው ቍጥር፤ በየራሳቸው ከሠራዊቶቻቸው ጋር ወደ ሠልፍ የሚወጣው ሁሉ ከሃያ ዘመን ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወንድ ወንዱ ሁሉ፤

፳፩፤ ኍላቌሆሙ ዘእምነገደ ሮቤል አርባዕቱ እልፍ ወስሳ ምእት ወሐምስቱ ምእት፤

ከሮቤል ነገድ የተቈጠሩት ሰዎች ቍጥራቸው አራት እልፍ ስድስት ሽህ አምስት መቶ (አርባ ስድስት ሽህ አምስት መቶ) ናቸው፤

፳፪፤ ወደቂቀ ስምዖን በበትውልዶሙ ወበበሕዘቢሆሙ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ዘበበርእሶሙ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኃይል፤

የስምዖንም ልጆች በየትውልዳቸው በየወገናቸው በየአባቶቻቸው ወገን በየስማቸው ቍጥር ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሰልፍ የሚወጣው ከሃያ ዘመን ጀምሮ እስከ ሃምሳ ያሉት ወንድ ወንዱ ሁሉ፤

፳፫፤ ኍላቌሆሙ ዘእምነገደ ስምዖን ሐምስቱ እልፍ ወተስዓ ምእት ወሠለስቱ ምእት፤

የነገደ ስምዖን ቍጥራቸው አምስት እልፍ ዘጠኝ ሽህ (ሐምሳ ዘጠኝ ሽህ ሦስት መቶ) ናቸው፤



፳፬፤ ወደቂቀ ይሁዳ በበትውልዶሙ ወበበሕዘቢሆሙ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ዘበበርእሶሙ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኃይል፤

የይሁዳም ልጆች በየትውልዳቸው በየወገናቸው በየአባቶቻቸው ወገን በየስማቸው ቍጥር ከሠራዊት ጋራ ወደ ሰልፍ የሚወጣው ከሃያ ዘመን ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወንድ ወንዱ ሁሉ በየራሳቸው ተቈጥረው፤

፳፭፤ ኍላቌሆሙ ዘእምነገደ ይሁዳ ሰብአቱ እልፍ ወአርባዓ ምእት ወስድስቱ ምእት፤

የነገደ ይሁዳ ቍጥራቸው ሰባት እልፍ አራት ሺህ (ሰባ አራት ሺህ ስድስት መቶ) ናቸው፤

፳፮፤ ወደቂቀ ይሳኮር በበትውልዶሙ ወበበዘመዶሙ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ዘበበርእሶሙ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኃይል፤

የይሳኮርም ልጆች በየትውልዳቸው፤ በየዘመዶቻቸው፤ በየአባቶቻቸው ወገን በየስማቸው ቍጥር ከሠራዊቱ ጋር

www.ethiopianorthodox.org

ወደ ሰልፍ የሚወጣው ከሃያ ዘመን ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወንድ ወንዱ ሁሉ በየራሳቸው ተቈጥረው፤

፳፯፤ ኍላቌሆሙ ዘእምነገደ ይሳኮር ሐምስቱ እልፍ ወአርብዓ ምእት ወአርባዕቱ ምእት፤

የነገደ ይሳኮር ቍጥራቸው አምስት እልፍ አራት ሺህ (አምሳ አራት ሺህ አራት መቶ) ናቸው፤

፳፰፤ ወደቂቁኒ ለዛብሎን በበትውልዶሙ ወበበሕዘቢሆሙ ወበበ አብያተ አበዊሆሙ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ዘበበርእሶሙ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኃይል፤

የዛብሎንም ልጆች በየትውልዳቸው በየወገኖቻቸው በየአባቶቻቸው ወገኖች በየስሞቻቸው ቍጥር ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሰልፍ የሚወጣው ከሃያ ዘመን ጀምሮ ከሃያ ዘመንም በላይ ያለው ወንድ ወንዱ ሁሉ በየራሳቸው ተቈጥረው፤

፳፱፤ ኍላቌሆሙ ዘእምነገደ ዛብሎን ሐምስቱ እልፍ ወሰብዓ ምእት ወአርባዕቱ ምእት፤

የነገደ ዛብሎን ቍጥራቸው አምስት እልፍ ሰባት ሺህ (አምሳ ሰባት ሺህ አራት መቶ) ናቸው፤

፴፤ ወደቂቁኒ ለዮሴፍ ደቂቀ ኤፍሬም በበትውልዶሙ ወበበ ሕዘቢሆሙ ወበበአብያተ አበ ዊሆሙ ወበበኍልቈ አስማቲ ሆሙ ዘበበርእሶሙ ኵሉ ተባ ዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኃይል፤

ከዮሴፍ የተወለደ የኤፍሬምም ልጆች በየትውልዳቸው በየወገኖቻቸው በየአባቶቻቸው ወገኖች በየስሞቻቸው ቍጥር ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሰልፍ የሚወጣው ከሃያ ዘመን ጀምሮ ከሃያ ዘመንም በላይ ያለው ወንድ ወንዱ ሁሉ በየራሳቸው ተቈጥረው፤

፴፩፤ ኍላቌሆሙ ዘእምነገደ ኤፍሬም አርባዕቱ እልፍ ወኃምስቱ ምእት፤

ከነገደ ኤፍሬም የተቈጠሩ ቍጥራቸው አራት እልፍ አርባ ሺህ አምስት መቶ ናቸው፤

፴፪፤ ወደቂቁኒ ለምናሴ በበትውልዶሙ ወበበሕዘቢሆሙ ወበበ አብያተ አበዊሆሙ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ዘበበርእሶሙ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኃይል፤



የምናሴ ልጆች በየትውልዳቸው በየወገኖቻቸው በየአባቶቻቸው ወገኖች በየስሞቻቸው ቍጥር ከሠራዊቱ ጋራ ወደ ሰልፍ የሚወጣው ከሃያ ዘመን ጀምሮ ከሃያ ዘመን በላይም ያለው ወንድ ወንዱ በየራሳቸው ተቈጥረው፤

፴፫፤ ኍላቌሆሙ ዘእምነገደ ምናሴ ሠለስቱ እልፍ ወዕሥራ ምእት ወክልኤቱ ምእት፤

የነገደ ምናሴ ቍጥራቸው ሦስት እልፍ ሁለት ሺህ (ሠላሳ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ) ናቸው፤

፴፬፤ ወደቂቁኒ ለብንያም በበትውልዶሙ ወበበሕዘቢሆሙ ወበበ አብያተ አበዊሆሙ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ዘበበርእሶሙ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኃይል፤

የብንያም ልጆች በየትውልዳቸው በየወገናቸው በየአባቶቻቸው ወገን በየስማቸው ቍጥር ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሰልፍ የሚወጣው ከሃያ ዘመን ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወንድ ወንዱ በየራሳቸው ተቈጥረው፤

፴፭፤ ኍላቌሆሙ ዘእምነገደ ብንያም ሠለስቱ እልፍ ወሐምሳ ምእት ወአርባዕቱ ምእት፤

የነገደ ብንያም ቍጥራቸው ሦስት እልፍ አምስት ሺህ (ሠላሳ አምስት ሺህ አራት መቶ) ናቸው፤

፴፮፤ ወደቂቁኒ ለጋድ በበትውልዶሙ ወበበሕዘቢሆሙ ወበበ አብያተ አበዊሆሙ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ዘበበርእሶሙ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኃይል፤

የጋድ ልጆችም በየትውልዳቸው በየወገናቸው በየስማቸው ቍጥር ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሰልፍ የሚወጣው ከሃያ ዘመን ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወንድ ወንዱ ሁሉ በየራሳቸው ተቈጥረው፤

፴፯፤ ኍላቌሆሙ ዘእምነገደ ጋድ አርባዕቱ እልፍ ወሐምሳ ምእት ወሰባቱ ምእት ወሐምሳ፤

የነገደ ጋድ ቍጥራቸው አራት እልፍ አምስት ሺህ (አርባ አምስት ሺህ ሰባት መቶ አምሳ) ናቸው፤

፴፰፤ ወደቂቁኒ ለዳን በበትውልዶሙ ወበበሕዘቢሆሙ ወበበ አብያተ አበዊሆሙ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ ዘበበርእሶሙ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኃይል፤

www.ethiopianorthodox.org

የዳንም ልጆች በየትውልዳቸው በየወገኖቻቸው በየስማቸው ቍጥር ከሃያ ዘመን ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወደ ሰልፍ የሚወጣው ወንድ ወንዱ በየራሳቸው ተቈጥረው፤

፴፱፤ ኊላቌሆሙ ዘእምነገደ ዳን ስድስቱ እልፍ ወዕሥራ ምእት ወሰብዓቱ ምእት፤

የነገደ ዳን ቍጥራቸው ስድስት እልፍ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ (ስድሳ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ) ናቸው፤

፵፤ ወደቂቁኒ ለአሴር በበትውልዶሙ ወበበሕዘቢሆሙ ወበበ አብያተ አበዊሆሙ ወበበኊልቈ አስማቲሆሙ ዘበበርእሶሙ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኃይል፤

የአሴርም ልጆች በየትውልዳቸው በየወገናቸው በየስማቸው ቍጥር ወደ ሰልፍ የሚወጣው ከሃያ ዘመን ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወንድ ወንዱ ሁሉ በየራሳቸው ተቆጥረው፤

፵፩፤ ኊላቌሆሙ ዘእምነገደ አሴር አርባዕቱ እልፍ ወዐሠርቱ ምእት ወሐምስቱ ምእት፤

የነገደ አሴር ቍጥራቸው አራት እልፍ አንድ ሺህ አምስት መቶ (አርባ አንድ ሺህ አምስት መቶ) ናቸው፤

፵፪፤ ወደቂቁኒ ለንፍታሌም በበትውልዶሙ ወበበሕዘቢሆሙ ወበበ አብያተ አበዊሆሙ ወበበኊልቈ አስማቲሆሙ ዘበበርእሶሙ ኵሉ ተባዕት ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ኵሉ ዘይወፅእ ምስለ ኃይል፤

የንፍታሌም ልጆችም በየትውልዳቸው በየወገናቸው በየስማቸው ቍጥር ከሃያ ዘመን ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው ወደ ሰልፍ የሚወጣው ወንድ ወንዱ በየራሳቸው ተቈጥረው፤

፵፫፤ ኊላቌሆሙ ዘእምነገደ ንፍታሌም ሐምስቱ እልፍ ወሠላሳ ምእት ወአርባዕቱ እልፍ ወሠላሳ ምእት ወአርባዕቱ ምእት ፤

የነገደ ንፍታሌም ቍጥራቸው አምስት እልፍ ሦስት ሽህ አራት መቶ (አምሳ ሦስት ሺሕ አራት መቶ) ናቸው፤

፵፬፤ ዛቲ ይእቲ ፍቅድ እንተ አስተፋቀድዎሙ ሙሴ ወአሮን ወመላእክቲሆሙ ለእስራኤል ዐሠርቱ ወክልኤቱ ዕደው አሐዱ አሐዱ ብእሲ እምአሐዱ አሐዱ ነገድ እምነገደ አብያተ አበዊሆሙ ውእቶሙ፤

ሙሴና አሮን ዐሥራ ሁለቱ የእስራኤልም አለቆች የቈጠ



ሯቸው ቍጥር ይህች ናት፤ እሊህም አንዱም አንዱም ሰው ከአባቶቻቸው ወገን ከየአንዳንዱ ነገድ የተመረጡ ናቸው፤ ‹ሐተታ› ሙሴ ስለ ምን ቈጠራቸው ቢሉ የእግዚ አብሔርን ቸርነት ለመናገር፤ ሰባ ሁነው ግብጽ ወርደው ይህን ያህል በዙ ለማለት፤ አንድም ለአብርሃም የነገ ረው ተስፋ እንዳልቀረ ለማጠ የቅ፤ ልጆችህን እንደ ሰማይ ኮከብ እንደባሕር አሸዋ አበዛ ልሃለሁ ብሎት ነበርና ይህ እንደ ተፈጸመ ለማጠየቅ፤

፵፭፤ ወኮነ ኵሉ ኊላቌሆሙ ለደቂቀ እስራኤል በበኃይሎሙ ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ ዘይወፅእ ፀብዓ እምእስራኤል ስሳ እልፍ ወሠላሳ ምእት ወሐምስቱ ምእት ወሐምሳ፤

ከእስራኤል ወደሰልፍ የሚ ወጣው ከሃያ ዘመን ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለው በየሠራ ዊታቸው ተቈጥረው የእስራ ኤል ልጆች መላ ቍጥራቸው ስሳ እልፍ ሦስት ሺሕ አምስት መቶ አምሳ (ስድስት መቶ ሦስት ሺሕ አምስት መቶ አምሳ) ሆነ፤

ጉባኤ

፵፮፤ ወለሌዋውያንሰ ምስለ ነገደ ልደቶሙ እሙንቱ ወኢኊለቍዎሙ ምስለ ደቂቀ እስራኤል፤

የሌዊን ልጆችና ከነሱ የተ ወለዱ ልጆቻቸውን ግን ሙሴና አሮን ከእስራኤል ልጆች ጋር አልቈጠሯቸውም፤

፵፯፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፤

እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተነጋገረው፤

፵፰፤ ዑቅ ኢትኊልቆሙ ለነገደ ሌዊ ወኢትትመጠው ኊላቌሆሙ እምደቂቀ አስራኤል፤

የሌዊን ነገድ እንዳትቈጥ ራቸው ዕወቅ፤ ከእስራኤልም ልጆች ጋር ቍጥራቸውን አትቀበል አለው፤

፵፱፤ ወሢሞሙ ለሌዋውያን ዲበ ደብተራ ዘመርጡል ወዲበ ኵሉ ንዋያ ወዲበ ኵሉ ዘሀሎ ውስቴታ ፤

የሌዊን ልጆች በደብተራ ኦሪትና በገንዘቧ ሁሉ በውስጧ ባለውም ዕቃ ሁሉ ሹማቸው፤

፶፤ ከመ እሙንቱ ያነሥእዋ ለደብተራ ወለኵሉ ንዋያ ወከመ

www.ethiopianorthodox.org

እሙንቱ ይግበሩ ውስቴታ ወዓውደ ደብተራ ይትዓየኑ፤

ደብተራ ኦሪትን ዕቃዋንም ሁሉ እንሥተው ይሸከሙ ዘንድ፣ በውስጧ ሥራ ይሠሩ ዘንድ ደብተራ ኦሪትንም ከበው ይቆሙ ዘንድ ሾማቸው፤

፶፩፤ ወእመኒ ግዕዘት ደብተራ ይተ ክልዋ ሌዋውያን ወእመሰ ኀድርት ይእቲ እሙንቱ ያነሥእዋ፤

ደብተራ ኦሪት ብትጓዝም ሌዋውያን ዕቃዋን በመሸ ከም ያገልግሏት፣ ብታድርም አድራ ስትነሣ ጓዟን ያንሡ፤ አንድም ይህን ሁሉ ያደርጉ ላት ዘንድ ሾማቸው፤

ወዘእምባዕድ ዘመድ ዘንብረ ምስሌሆሙ ሐዊረ ለይሙት፤

ከሌዋውያን ያልተወለደ ከሌላ ወገን የሆነ ከነሱ ጋር የተጓዘ በድንጊያ ተወግሮ በእሳት ተቃ ጥሎ ይሙት ፤

፶፪፤ ወይትዐየኑ ደቂቀ እስራኤል ብእሲ ብእሲ በትዕይንቱ ወብእሲ ብእሲ በምስፍናሁ ወበበኃይሎሙ፤

የእስራኤል ልጆች አንዱም አንዱም ሰው በየሰፈሩ በየአለቃው በየሠራዊታቸው ይስፈሩ፤

፶፫፤ ወሌዋውያንሰ ይትዐየኑ ፍጽመ ውስተ ዐውደ ደብተራ ዘመርጡል ወኢይኩን ጌጋይ ላዕለ ደቂቀ እስራኤል ወይዕቀቡ ሌዋ ውያን ሕጋ ለደብተራ መርጡል፤

በእስራኤል ልጆች ላይ ዕዳ በደል እንዳይሆን ሌዋውያን ግን በደብተራ ኦሪት ፊት ለፊት ሰፍረው የደብተራ ኦሪትን ሥርዓቷን ይጠብቁ፤

፶፬፤ ወገብሩ ደቂቀ እስራኤል ኵሎ ዘአዘዞሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ከማሁ ገብሩ፤

የእስራኤል ልጆችም እግ ዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዳዘዛቸው አደረጉ።

## ምዕራፍ ፪

፩፤ ወነበቦሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን፤

እግዚአብሔር ሙሴንና አሮ ንን ተናገራቸው፤

፪፤ ወይቤሎሙ ብእሲ ብእሲ በበሥርዓቱ ወበበትእምርቱ ወበበ ቤተ አበዊሆሙ ይትዐየኑ ደቂቀ እስራኤል አንጻረ ዐውደ ደብተራ ዘመርጡል፤

የእስራኤል ልጆች አንዱም አንዱም ሰው በየሥራቱ በየምልክቱ በየአባቶቻቸው



ወገን በደብተራ ኦሪት ዙሪያ አንጻር ይስፈሩ፣ ‹ሐተታ› የሚሠፍሩ በምሥራቅ፣ በም ዕራብ፣ በሰሜን፣ በደቡብ፣ ነውና፤ አንድም ‹‹በበሥርዓቱ ወበበትእምርቱ ባለው›› በየዓ ላማቸው ይሠፍራሉ፣ የነገደ ይሁዳ አላማ ሥዕለ አንበሳ ነው፣ ‹‹ይሁዳ ዕጓለ አንበሳ ዕርገ እምሕዝባትከ ይለዋልና፣›› የሮቤል አላማ ሥዕለ ሰብእ ነው፣ በፊት ባለ አእምሮ ነበርና፣ ‹‹ዐቢይ ጥይቅና ልቡ ለሮቤል›› እንዲል፣ የኤፍሬም አላማ ሥዕለ እንስሳ ነው፣ ሁለት ዕጓላተ ላሕም ያቆመ ኢዮርብአም ከርሱ ይወለ ዳልና፣ የዳን አላማ ሥዕለ ንስር ነው፣ ሥዕለ ንስር ዘቂሣርያን ያመልካሉና፤ አን ድም የሮቤል አላማ ሥዕለ እንስሳ ነው፣ የእንስሳ ግብር ሥራ ሠርቷልና ማለት ከአባቱ ዕቅብት ደርሷልና ፣ የኤፍሬም ዐላማ ሥዕለ ሰብእ ነው፣ ባለ አእምሮ ኢያሱ ከርሱ ተወልዷልና፣ የዳን ዓላማ ሥዕለ ተመን ነው፣ ዘንዶ ያመልካሉና፤ አንድም ሐሳዊ መሢሕ ከእርሱ ወገን ይወለዳልና ፤

፫፤ ወእለ ይቀድሙ ተዓይኖ መንገለ ጽባሕ ይኀድሩ ተዐይነ ይሁዳ ምስለ ኃይሉ፤

መጀመሪያ የሚሰፍሩ ‹መስ ፈርን የሚቀድሙ› ይሁዳ ይሳኮር ዛብሎን በምሥራቅ በኩል ይስፈሩ፤

፬፤ ወመልአኮሙ ለደቂቀ ይሁዳ ነአሶን ወልደ አሚናዳብ ምስለ ኃይሉ እለ ተኍለቁ ሰብዓቱ እልፍ ወአርብዓ ምእት ወስድስቱ ምእት፤

ከተቈጠሩት ሰባት እልፍ ከአ ራት ሺህ ‹ሰባ አራት ሺሕ ስድስት መቶ› ሠራዊት ጋር የይሁዳ ልጆች አለቃቸው የአሚናዳብ ልጅ ነአሶን ነው፤

፭፤ ወእምድኀሬሆሙ ይትዐየኑ ነገደ ይሳኮር፤

ከይሁዳ ልጆች ቀጥለው የይ ሳኮር ልጆች ይስፈሩ፤

፮፤ ወመልአኮሙ ለደቂቀ ይሳኮር ናትናኤል ወልደ ሰገር ምስለ ኃይሉ እለ ተኍለቁ ሐምስቱ እልፍ ወአርባዕቱ ምእት ወአርባዕቱ ምእት፤

ከተቈጠሩት ከአምስት እልፍ አራት ሺህ ከአራት መቶ ‹አምሳ አራት ሺህ አራት መቶ› ሠራዊት ጋር የይሳኮር ልጆች አለቃቸው የሰገር ልጅ ናትናኤል ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

፯፤ ወእምድኅሬሆሙ ይትዓየኑ ነገደ ዛብሎን፤

ከይሳኮር ነገድ ቀጥሎ የዛብሎን ነገድ ይሰፈሩ፤

፰፤ ወመልአኮሙ ለደቂቀ ዛብሎን ኤልያብ ወልደ ኬሎን ምስለ ኃይሉ እለ ተኈለቁ ሐምስቱ እልፍ ወሰብዓ ምእት ወአርባዕቱ ምእት፤

ከተቈጠሩት ከአምስት እልፍ ሰባት ሺህ አራት መቶ ‹አምሳ ሰባት ሺህ አራት መቶ› ሠራዊት ጋር የዛብሎን ነገድ አለቃ የኬሎን ልጅ ኤልያብ ነው፤

፱፤ ወኵሉ እለ ተኈለቁ እምትዕይንተ ይሁዳ ዐሠርቱ ወሰመንቱ እልፍ ስሳ ምእት ወአርባዕቱ ምእት ምስለ ኃይሎሙ እሙንቱ ይቀድሙ አንሥኡ፤

ከይሁዳ ነገድ የተቈጠሩት ሁሉ ዐሥራ ስምንት እልፍ ከስድስት ሺህ አራት መቶ ናቸው፣ (አንድ መቶ ሰማንያ ስድስት ሺህ ከአራት መቶ) ናቸው፣ ከሠራዊቶቻቸው ጋራ በመንገዝ ጊዜ መነሣትን ይቀድማሉ፤

፲፤ ወየኃድሩ ትዕይንተ ሮቤል መንገለ አዜብ ምስለ ኃይሎሙ፣

በደቡብ ከሠራዊቶቻቸው ጋራ ሮቤል ስምዖንና ጋድ ይሰፈሩ፤

፲፩፤ ወመልአኮሙ ለደቂቀ ሮቤል ኤልሱር ወልደ ሴድዩር ምስለ ኃይሉ እለ ተኈለቁ አርባዕቱ እልፍ ወስሳ ምእት ወሐምስቱ ምእት፣

ከተቈጠሩት አራት እልፍ ከስድስት ሺህ አምስት መቶ ‹አርባ ስድስት ሺህ ከአምስት መቶ› ሠራዊት ጋራ የሮቤል ልጆች አለቃቸው የሴድዩር ልጅ ኤልሱር ነው፤

፲፪፤ ወይትዐየኑ በገቦሆሙ ነገደ ስምዖን፣

በአጠገባቸው የስምዖን ነገድ ይሰፈሩ፤

፲፫፤ ወመልአኮሙ ለደቂቀ ስምዖን ሰላምያል ወልደ ሲሩሳዴ ምስለ ኃይሉ እለ ተኈለቁ ሐምስቱ እልፍ ወተስዓ ምእት ወሠለስቱ ምእት፣

ከተቈጠሩት ከአምስት እልፍ ከዘጠኝ ሺህ ሦስት መቶ ‹አምሳ ዘጠኝ ሺህ ሦስት መቶ› ሠራዊት ጋራ የስምዖን ነገድ አለቃቸው የሲሩሳዴ ልጅ ሰላምያል ነው፤

፲፬፤ ወየኃድሩ በገቦሆሙ ነገደ ጋድ፣

በነገደ ስምዖን አጠገብ ነገደ ጋድ ይሰፈሩ፤

፲፭፤ ወመልአኮሙ ለነገደ ጋድ ኤልሳፍ ወልደ ራጉኤል ምስለ ኃይሉ እለ ተኈለቁ አርባዕቱ እልፍ ወሐምሳ ምእት ወስድስቱ ምእት ወሐምሳ፣



ከተቈጠሩት አራት እልፍ ከአምስት ሺህ ስድስት መቶ አምሳ ‹አርባ አምስት ሺህ ከስድስት መቶ አምሳ› ሠራዊት ጋራ ለጋድ ልጆች አለቃቸው የራጉኤል ልጅ ኤልሳፍ ነው፤

፲፮፤ ወኵሉ እለ ተኈለቁ እምትዕይንተ ሮቤል ፀሠርቱ ወሐምስቱ እልፍ ፀሠርቱ ወአርባዕቱ ምእት ወሐምሳ ምስለ ኃይሎሙ፣

ከሮቤል ሰፈር ከሠራዊቶቻቸው ጋራ የተቈጠሩት ሁሉ ዐሥራ አምስት እልፍ ከአንድ ሺህ አራት መቶ አምሳ ‹አንድ መቶ አምሳ አንድ ሺህ አራት መቶ አምሳ› ናቸው፤

ወበዳግም ያነሥኡ እሙንቱ፣

በሁለተኛው ጉዞ የደብተራ ኦሪትን ዕቃ እሊህ ያነሣሉ፤

፲፯፤ ወትትነሣእ ደብተራ ኦሪት ዘመርጡል፣

ደብተራ ኦሪትም ትነሣለች፤

ወትዕይንቶሙ ለሌዋውያን ማዕከለ ተዓይን በከመ ይትዐየኑ ከማሁ ያነሥኡ አሐዱ አሐዱ ዘዘይታለዉ በበምስፍናሁ፤

የሌዋውያን ሰፈራቸው በሰፈሩ መካከል ነው፣ እንዳሰፋፈራቸው አንዱም አንዱም በየአለቃቸው እየተከታተሉ የደብተራ ኦሪትን ዕቃ ያነሣሉ፤

፲፰፤ ወየኃድሩ ትዕይንተ ኤፍሬም መንገለ ገጸ ባሕር ምስለ ኃይሎሙ፣

በምዕራብ በኩል ኤፍሬም ብንያም ምናሴ ይሰፍራሉ ፤ (ይሰፈሩ)

፲፱፤ ወመልአኮሙ ለደቂቀ ኤፍሬም ኤሊሳማ ወልደ አምዩድ ምስለ ኃይሉ እለ ተኈለቁ አርባዕቱ እልፍ ወሐምስቱ ምእት፣

ከተቈጠሩት ከአራት እልፍ አምስት መቶ ‹አርባ ሺህ አምስት መቶ› ሠራዊት ጋራ የኤፍሬም ልጆች አለቃቸው የአምዩድ ልጅ ኤሊሳማ ነው፤

፳፤ ወየኃድሩ በገቦሆሙ ነገደ ምናሴ፣

ነገደ ምናሴ በአጠገባቸው ይሰፈሩ (ይሠፍራሉ)፤

፳፩፤ ወመልአኮሙ ለነገደ ምናሴ ገማልያል ወልደ ፈዳሱር፣

ምስለ ኃይሉ እለ ተኈለቁ ሠለስቱ እልፍ ወዕሥራ ምእት ወክልኤቱ ምእት፣

ከተቈጠሩት ከሦስት እልፍ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ‹ሠላሳ ሁለት ሺህ ከሁለት መቶ› ሠራዊት

www.ethiopianorthodox.org

በየነገዳቸው ፣ በየአለቃቸው ሰፈሩ፣ እንደዚሁም በየነገዳቸው በየአባቶቻቸው ወገን እየራሳቸው ጓዛቸውን ያነሣሉ።

## ምዕራፍ ፫

፩፤ ወከመዝ ይእቲ ልደቶሙ ለሙሴ ወለአሮን በዕለተ ተናገሮ እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ ሲና፤

እግዚአብሔር ሙሴን በደብረ ሲና በተናገረው ጊዜ የሙሴና የአሮን የልጆቻቸው ቍጥር ይህ ነው፤

፪፤ ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ አሮን፣

የአሮን ልጆች ስማቸው ይህ ነው፤

በኵሩ ናዳብ ወአብዩድ ወአልዓዛር ወኢታምር ፤

መጀመሪያው ናዳብ ፣ ሁለተኛው አብዩድ፣ ሦስተኛው አልዓዛር፣ አራተኛው ኢታምር ነው፤

፫፤ ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ አሮን ካህናት እለ ቅቡዓን ወእለ ፍጹማን እደዊሆሙ ከመ ይኩኑ ካህናተ፣

ለቤተ እግዚአብሔር አገልጋዮች የሆኑ ደሙንና ዘይቱን እጃቸውን የተቀቡ የአሮን ልጆች የካህናቱ ስማቸው ይህ ነው፤

፬፤ ወሞቱ ናዳብ ወአብዩድ በቅድመ እግዚአብሔር፣

ናዳብና አብዩድ በእግዚአብሔር ትእዛዝ በቤተ እግዚአብሔር ሞቱ፤

እስመ አምጽኡ እሳተ ዘእምባዕድ ቅድመ እግዚአብሔር በሐቅለ ሲና ወአልቦሙ ውሉድ፣

በደብረ ሲና አውራጃ ሳሉ ከውጭ እሳት ጭረው ወደ ቤተ እግዚአብሔር አምጥተው ነበርና ሞቱ፣ የሞቱበትን ምክንያት በኦሪት ዘሌዋውያን ተናግሮት ነበርና ከዚህም ደገመው፣ በሥራቸው የሚተካ ልጅም አልነበራቸውም፤

ወኮኑ አልዓዛር ወኢታምር ካህናተ ምስለ አሮን አቡሆሙ፣

አልዓዛርና ኢታምር ከአባታቸው ከአሮን ጋር ለቤተ እግዚአብሔር አገልጋይ ሆኑ፤

፭፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው፤



፮፤ ወይቤሎ ንሥኦሙ ለነገደ ሌዊ ወአቅሞሙ ቅድመ አሮን ካህን ወይትለአክዎ፣

የሌዊን ነገድ ወስደህ ያገለግሉት ዘንድ በካህኑ በአሮን ፊት አቁማቸው፤

፯፤ ወይዕቀቡ ሕጎ ወሕጎሙ ለደቂቀ እስራኤል በቅድመ ደብተራ ዘመርጡል ወይግበሩ ምግባራቲሃ ለደብተራ፣

ልዩ በሆነች ድንኳን የእስራኤልን ልጆች ሕግና የእግዚአብሔርን ሕግ ይጠብቁ ዘንድ የደብተራ ኦሪትንም ሥራዋን ይሠሩ ዘንድ፤

፰፤ ወይዕቀቡ ንዋያ ለደብተራ መርጡል ወኵሎ ሕጎሙ ለደቂቀ እስራኤል በኵሉ ምግባራቲሃ ለደብተራ፣

የደብተራ ኦሪትን ዕቃዋን ይጠብቁ ዘንድ፣ በደብተራ ኦሪት በሚሠራው ሥራ ሁሉ የእስራኤልን ልጆች ሕጋቸውን ይጠብቁ ዘንድ የሌዋውያንን ነገድ በአሮን ፊት አቁማቸው፤

፱፤ ወታገብኦሙ ለሌዋውያን ኀበ አሮን እትኩ ወኀበ ደቂቁ ካህናት፣

ሌዋውያንን ወደ ወንድምህ ወደ አሮንና አገልጋዮች ወደ ሆኑ ልጆቹ አቅርባቸው፤

እስመ ሀብተ ተውህቡ ሊተ እሙንቱ እምደቂቀ እስራኤል፣

ሌዋውያን ከእስራኤል ልጆች ተለይተው ስጦታ ሁነው ተሰጥተውኛልና፤

፲፤ ወትሠይሞሙ ለአሮን ወለደቂቁ ላዕለ ደብተራ ዘመርጡል ወይዕቀቡ ክህነቶሙ ወኵሎ ዘምሥዋዕ ወዘውስጥ እመንጦላዕት፤

ከመጋረጃው ውስጥ ያለውንና በመሠዊያው የሚሠራውን ሁሉ አገልግሎታቸውን ይጠብቁ ዘንድ አሮንንና ልጆቹን በደብተራ ኦሪት ሹማቸው፤

ወእመቦ ዘገሠሠ እምባዕድ ዘመድ ለይሙት፤

ከሌዊ ወገን ያልተወለደ ከሌላ የተወለደ ንዋየ ቅድሳቱን የነካ ሰው ቢኖር የሞት ሞት ይሙት፤

፲፩፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ፣

እግዚአብሔር ሙሴን ታየው፣ ተነጋገረው፤

ወይቤሎ ናሁ አነ ነሣእክዎሙ ለሌዋውያን እማዕከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል፣

እነሆ ሌዋውያንን ከእስራኤል ልጆች መካከል መርጫቸዋለሁ አለው፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፪፤ ህየንተ ኵሉ በኵር ዘይፈትሕ ማኅፀነ ዘእምደቂቀ እስራኤል ቤዛ ዚአሆሙ ይኩኑኒ ሌዋውያን ይቤ እግዚአብሔር፣

ከእስራኤል ወገን ለናቱ በኵር ሁኖ ስለሚወለደው ፈንታ ሌዋውያን መቤዥ ይሁኑኝ አለ እግዚአብሔር፤

፲፫፤ እስመ ኵሉ በኵረ ቀተልኩ በምድረ ግብጽ ኵሉ በኵር ዘእምደቂቀ እሥራኤል እምሰብእ እስከ እንስሳ ሊተ ውእቱ እስመ አነ እግዚአብሔር ፣

የማድን የምገድል ፈጣሪ እኔ ስለሆንኩ በግብጽ በኵር በኵሩን ሁሉ አጥፍቻለሁና ከእስራኤል ልጆች ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ ድረስ በኵር በኵሩ ለኔ አገልጋይ ነው አለው፤

ጉባኤ

፲፬፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ በሐቅለ ሲና ፣

እግዚአብሔር ሙሴን በሲና አውራጃ ታየው ተነጋገረው፤

፲፭፤ ወይቤሎ ኊልቆሙ ለደቂቀ ሌዊ በበአብያተ አበዊሆሙ ወበበ ሕዘቢሆሙ ኵሎ ተባዕቶሙ ዘእም አሐዱ ወርኅ ወላዕሉ፣

የሌዊን ልጆች በየአባቶቻቸው በየወገኖቻቸው ካንድ ወር ጀምሮ ከዚያም በላይ የሆነውን ወንድ ወንዱን ቍጠራቸው አለው፣ ‹ሐተታ› ባለፈው ለጦር የሚወጡትን ነውና ከሃያ ዘመን ጀምሮ እስከ ስሳ ዘመን ያለውን ቆጠረ፣ ከዚህ ግን መላውን የሚቈጥር ነውና ካንድ ወር ጀምሮ ቈጠረ፤

፲፮፤ ወኆለቆሙ ሙሴ ወአሮን በቃለ እግዚአብሔር በከመ አዘዞሙ እግዚአብሔር ፣

አሮንና ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው ቈጠሯቸው፤

፲፯፤ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ሌዊ በበአስማቲሆሙ ጌድሶን ወቀዓት ወሜራሪ፣

በየስማቸው የሚጠሩ የሌዊ ልጆችም ጌድሶን ቀዓት ሜራሪ ናቸው፤

፲፰፤ ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ ጌድሶን በበሕዘቢሆሙ ሎቤን ወሴሜይ፣

የጌድሶን ልጆች ስማቸው በየወገናቸው ሎቤን ሴሜይ ናቸው፤



፲፱፤ ወደቂቀኒ ለቀዓት በበሕዘቢሆሙ እንበረም ወይሰዓር ወኬብሮን ወአዛሄል፣

የቀዓት ልጆችም በየወገናቸው እንበረምና ይሰዓር ኬብሮንና አዛሄል ናቸው፤

፳፤ ወደቂቀኒ ለሜራሪ በበሕዘቢሆሙ ሙሐሊ ወሐሙሲ፣

የሜራሪ ልጆችም በየወገናቸው ሙሐሊና ሐሙሲ ናቸው፤

ዝንቱ ውእቱ ነገደ ሌዋውያን በበአብያተ አበዊሆሙ፣

በየአባቶቻቸው ወገን የሌዋውያን ነገድ ይህ ነው፤

፳፩፤ ዘጌድሶን ሕዝበ ጌድሶን ዘሎቤን ሕዝበ ሎቤን ዘሴሜይ ሕዝበ ሴሜይ፣

የጌድሶን ወገኖች ሕዝበ ጌድሶን ይባላሉ፣ የሎቤን ወገኖች ሕዝበ ሎቤን ይባላሉ፣ የሴሜይ ወገኖችም ሕዝበ ሴሜይ ተብለው ይቈጠራሉ፤

ዝንቱ ሕዝብ ዘጌድሶን፣

የጌድሶን ወገን ይህ ነው፤

፳፪፤ ወዘአስተፋቀዱ ኊልቈ ኵሉ ተባዕቶሙ ዘእምአሐዱ ወርኅ ወላዕሉ ኊላቌሆሙ ፸፻ወ፭፻፣

ከአንድ ወር ጀምሮ ከዚያም በላይ የሆነው ወንድ ወንዱን ሁሉ የቈጠሯቸው ቍጥር ሰባት ሺህ አራት መቶ ናቸው፤

፳፫፤ ወየኃድሩ ደቂቀ ጌድሶን ድኅረ ደብተራ መንገለ ገጸ ባሕር፣

የጌድሶን ልጆች ከደብተራ ኦሪት በኋላ ኤፍሬም ምናሴ ብንያም በሚሰፍሩበት ያድራሉ፤

፳፬፤ ወመልአኮሙ ለቤተ አበዊሆሙ ለሕዝበ ጌድሶን ኤልሳፍ ወልደ አዳሄል፣

የጌድሶን ወገኖች የአባቶቻቸው ወገን አለቃቸው የአዳሄል ልጅ ኤልሳፍ ነው፤

፳፭፤ ወዘይትሐበዩ ደቂቀ ጌድሶን እምደብተራ ዘመርጡል፣

ወዘይፀውሩ ሲል ነው፣ የጌድሶን ልጆች ከደብተራ ኦሪት ዕቃ የሚሸከሙት ይህ ነው፤

ደብተራ ወሠቃቲሃ ወመክደና ወመንጦላዕተ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል፣

አራቱን ኅብር ግምጃ፣ ዐሥሩን ፈርጅ፣ ዓሥራ አንዱን ፈርጅ፣ ወሠቃቲሃ ብስጥ፣ ወመክደና፣ ማዕሰ መጸጺት፣

www.ethiopianorthodox.org

ሰቀልኛ የምትሆን የደብተራ ኦሪትን የደጃፉን መጋረጃ፤

፳፮፤ ወአልባሰ ዐፀድ ወመንጦላዕት አንቀጽ ዘዐፀደ ደብተራ ወዘተርፈ ኵሉ ምግባራቲሃ፤

ያጥሩን መጋረጃ፣ የሃያውን ክንድ መጋረጃ፣ የደብተራ ኦሪትን የዙርያዋን በር መጋ ረጃ፣ የቀረውን ዕቃዋን ሁሉ የሚሸከሙ እሊህ ናቸው፤

፳፯፤ ወዘቀዓትኒ ሕዝበ እንበረም ወሕዝበ ይሰዓር ወሕዝበ ኬብሮን ወሕዝበ አዛሄል እሉ እሙንቱ ሕዝብ ዘቀዓት፣

የቀዓት ልጆች የሚሆኑ የእ ንበረምና የይሰዐር የኬብሮ ንና የአዛሄል ወገኖች እሊህ የቀዓት ወገኖች ናቸው፤

፳፰፤ በበኍልቌ ኵሉ ተባዕቶሙ ዘእምአሐዱ ወርኅ ወላዕሉ ሰማንያ ምእት ወስድስቱ ምእት፣

ከአንድ ወር ጀምሮ ከዚያም በላይ የሚሆነው ወንድ ወንዱ ሁሉ በየቍጥራቸው ስምንት ሺህ ስድስት መቶ ናቸው፤

ወየዓቅቡ ሕጎሙ ለቅዱሳን

የካህናቱን ሕግ ይጠብቃሉ፣ አንድም የንዋየ ቅድሳቱን ሕግ ይጠብቃሉ፤

፳፱፤ ወየኃድሩ ሕዝቦሙ ለደቂቀ ቀዓት እምገቦሃ ለደብተራ ዘመንገለ አዜብ፣

የቀዓት ልጆች ሮቤል፣ ስም ዖን፣ ጋድ ይሰፍሩበት በነበ ረው በደቡብ በደብተራ ኦሪት አጠገብ ይሰፍሩ ነበር፤

፴፤ ወመልአኮሙ ለቤተ አበዊ ሆሙ ለሕዝበ ቀዓት ኤልሳፍ ወልደ አዛሄል፣

የቀዓት ልጆች የአባቶቻቸው ወገን አለቃ የአዛሄል ልጅ ኤልሳፍ ነው፤

፴፩፤ ወዘይትሐበዩ እሙንቱ ታቦተ ወማዕደ ወመራናተ ወምሥዋዓ ወንዋያተ ቅድሳት ወኵሉ ዘይገብሩ ቦቱ ወመክደነ ወኵሉ ምግባራተ፣

እነሱም ታቦትንና ማዕዱን፣ መቅረዙንና መሠዊያውን፣ መሥዋዕቱን የሚያዘጋጁበትን ንዋየ ቅድሳቱን፣ መክደኛውን መሣሪያውን ሁሉ የሚሸከሙ የቀዓት ልጆች ነበሩ (ናቸው፤)

፴፪፤ ወመልአክ ዘይቤ ዘዲበ መሳ ፍንቲሆሙ ለሌዋውያን አልዓዛር ወልደ አሮን ዘተሠይመ ይዕቀብ ሕጎሙ ለቅዱሳን፣

የካህናቱን ሥርዓት፤ አንድም የንዋየ ቅድሳቱን ሥርዓት



ይጠብቅ ዘንድ በሌዋውያን ሹማምት ላይ የተሾመው አለቃ የአሮን ልጅ አልዓዛር ነው፤

፴፫፤ ወዘሜራሪኒ ሕዝበ ሙሐሊ ወሕዝበ ሐሙሲ እሉ እሙንቱ ሕዝበ ሜራሪ፣

የሜራሪ ልጆች የሚሆኑ የሙሐሊና የሐሙሲ ልጆች እሊህ ናቸው፤

፴፬፤ ወኍላቄሆሙ በከመ አስተ ፋቀድዎሙ ኵሉ ተባዕቶሙ ዘእምአሐዱ ወርኅ ወላዕሉ ስሳ ምእት፣

ከአንድ ወር ጀምሮ ከዚያም በላይ የሆነው ሙሴና አሮን እንደቈጠሯቸው ወንድ ወንዱ ሁሉ ቍጥራቸው ስድስት ሺህ ናቸው፤

፴፭፤ ወመልአኮሙ ለቤተ አበዊ ሆሙ ለሕዝበ ሜራሪ ሱራሄል ወልደ አቤኪያ፣

የሜራሪ ወገኖች የአባቶቻ ቸው ወገን አለቃ የአቤኪያ ልጅ ሱራሄል ነው፤

ወየኀድሩ በገቦሃ ለደብተራ ዘመን ገለ መስዕ፣

እነዚህም የሜራሪ ልጆች አሴር፣ ዳን፣ ንፍታሌም በሚ ሰፍሩበት በሰሜን በኩል በደ ብተራ ኦሪት አጠገብ ይሰፍሩ ነበር፤

፴፮፤ ወዘይትሐበዩ ነገደ ደቂቀ ሜራሪ አርእስተ አዕማድ ዘደብተራ ወመናስግቲሆን ወአዕማዲሃ ወመ ከየዲሆን ወኵሉ ንዋዮን ወምግባ ራቲሆን፣

የሜራሪ ልጆችም የሚሸከ ሙት የደብተራ ኦሪትን የአ ዕማዷን ክባስ፣ ቍልፏን፣ አዕ ማዷን፣ ወመከየዲሆን ሰክተ ቷን፣ ዕቃዋን ሁሉ መሣሪያ ቸውን ነው፤

፴፯፤ ወአዕማደ ዘዓውደ ዓፀድ ወመከየዲሆን ወመታክሊሆን ወመ ታግሪሆን፣

በደብተራ ኦሪት ዙሪያ የሚ ቆሙትን የመጋረጃውን አዕ ማድ፣ ወመከየዲሆን ሰክተታ ቸውን፣ ወመታክሊሆን ካስ ማቸውን፣ መታግሪሆን መም ቻቸውን ሁሉ የሚሸከሙ እሊህ ናቸው፤

፴፰፤ ወእለሰ የኀድሩ ቅድመ ደብተራ ዘመርጡል መንገለ ጽባሕ ሙሴ ወአሮን ወደቂቁ ከመ ይዕቀቡ ሕገ መቅደስ ወሕጎሙ ለደቂቀ እስራኤል፣

ሙሴና አሮን የአሮንም ልጆች የቤተ መቅደስን ሥርዓቷን

www.ethiopianorthodox.org

፶፡ ወነሥአ ወርቀ ዐሠርተ ምእተ ወሠለስተ ምእተ ስሳ ወሐምስተ ሰቅሎ በሰቅል ቅዱስ፤

ሺሕ ሦስት መቶ ስሳ አምስት ወቄት ወርቅ በቤተ እግዚአብ ሔር ዐዋቂ (ሚዛን) ተቀብሎ፤

፶፩፡ ወወሀቦሙ ሙሴ ውእተ ወርቀ ቤዛሆሙ ለእለ ፈድፈዱ ለአሮን ወለደቂቁ በቃለ እግዚአ ብሔር በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንደ አዘዘው ከሌዋውያን የሚበዙ ትን የእስራኤልን የበኵር ልጃ ቸውን መቤዣ (ዋጋ) ሙሴ ለአሮንና ለልጆቹ ሰጣቸው፤ (ሐተታ) ምነው ከኔ ብቻ እንዳይሉ ከሁለት እልፍ ሁለት ሺሕ ሁለት መቶ ሰባ ሦስት ሰዎች ከመላው ተቀብ ኋል፤ ለኋላውም ሥርዓት ሆኖ ቀርቷል፤ ለበኵር ልጅ አምስት አምስት ዓቀመት ይከፍል ነበር።

## ምዕራፍ ፬

፩፡ ወነበቦሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን፤

እግዚአብሔር ሙሴንና አሮ ንን ታያቸው ተነጋገራቸው፤

፪፡ ወይቤሎሙ ፍልጥዎሙ ለደ ቂቀ ቀዓት እማዕከሎሙ ለደቂቀ ሌዊ በበሕዘቢሆሙ ወበበቤተ አበ ዊሆሙ፤

የቀዓትን ልጆች በየወገናቸው በየአባቶቻቸው ወገን ከሌዊ ልጆች መካከል ለዩአቸው ብሎ ነገራቸው፤

፫፡ ዘእምዕሥራ ወሐምስቱ ዓም ወላዕሉ እስከ ሐምሳ ዓም፤

ከሃያ አምስት ዘመን እስከ ሐምሳ ዘመን ያሉትን ለዩአቸው፤

ኵሉ ዘይበውእ ይግበር ግብረ ኵሉ ምግባር ዘውስተ ደብተራ፤

ወደ ደብተራ ኦሪት የሚገባ ሁሉ በደብተራ ኦሪት የሚ ሠራውን ሥራ ይሠራ ዘንድ ለዩአቸው አለው፤ አንድም ወደ ደብተራ ኦሪት የሚገባ ሰው ሁሉ የደብተራ ኦሪትን ሥራ ይሥራ፤ (ሐተታ) ባለፈው ለቍጥር ብቻ ነውና ካንድ ወር ጀምሮ ቈጠረ፤ ከዚህ ግን ለተልዕኮ ነውና ከሃያ ዘመን በታች ያለው ሕፃን ይሆናል፤ ከሐምሳ ዘመን በላይ ያለውም ያረጃልና ብሎ ከሃያ አምስት ጀምሮ እስከ ሐምሳ ዘመን ያለውን ቆጠረ፤



፬፡ ወዝንቱ ውእቱ ግብሮሙ ለደቂቀ ቀዓት በደብተራ ዘመርጡል ቅድስት ዘቅዱሳን፤

ከተለዩ በተለየች በደብተራ ኦሪት የቀዓት ልጆች የሚ ሠሩት ሥራቸው ይህ ነው፤

፭፡ ወይበውኡ አሮን ወደቂቁ ሶበ ይትነሣእ ትዕይንት ወያወርዱ መንጦላዕተ ዘይሤውር ወይከድንዋ ባቲ ለታቦት ዘመርጡል፤

ጓዙ በሚነሣበት ጊዜ አሮንና ልጆቹ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገብተው ደብተራ ኦሪትን የሚሸፍነውን መጋረጃውን አውርደው ይሸከሙ፤

፮፡ ወይወድዩ መልዕልቶ ክዳነ ዘማዕሰ መጸጺት ወይወድዩ መል ዕልቶ ልብሰ ዘኵለንታሁ ያክንት ወይወድዩ መዓውርቲሃ፤

ማዕሰ መጸጺትን ያልብሱት፤ ሰማያዊ ቀለም የገባ የባሕር ዓረብ ያልብሱት፤ ከዚያም በላይ ሁለንተናው ሰማያዊ ሐር የሚሆን ልብስ ያልብሱት፤ መሎጊያውንም ይሸከሙት፤

፯፡ ወዳበ ማዕድኒ እንተ ሥርዕት ይወ ድዩ ልብሰ ዘኵለንታሁ ኅብረ ከብድ፤

በተሠራች ማዕድም ላይ ሁለ ንተናው ብጫ የሆነ ልብስን ያለብሱ ነበር፤

ወይወድዩ ላዕሌሃ መጸብሕቲሃ ወአጽሕልቲሃ ወመዳምሒሃኒ ወመዋጽሕቲሃኒ በዘቦቱ ያወጽሑ ወኅብስተኒ ዘይሠርዐ በኵሉ ጊዜ ላዕሌሃ፤

ታላቅ ወጭትና ታናሽ ወጭት፤ ወይኑን ፍልቅ አድ ርገው የሚያፈሱበት ጽዋዋ ንና ማንካዋን፤ በየጊዜው የሚሠሩት ኅብስቱንም በላ ይዋ ላይ ያኑሩ፤

፰፡ ወይወድዩ ላዕሌሃ ልብሰ ለይ ወይከድንዋ መክድነ ዘማዕሰ መጸጺት፤

ቀይ ሐር ልብስ አልብሰው ቀለም የገባ ባሕር ዐረብ ይሸፍኗት፤

ወያስተዋድዱ መዓውርቲሃ፤

መሎጊያዋንም በቀለበት ያግቡ፤

፱፡ ወይነሥኡ ልብሰ ያክንት ወይከድንዋ ለመራናት እንተ ላዕሌሃ የኀትዉ መኃትዊሃ፤

ሰማያዊ ሐር የሚሆን ልብ ስን አምጥተው በላይዋ መብ ራት የሚያበሩባት መቅረዝን ያልብሷት፤

ወጉጠታቲሃ በዘቦቱ ያሤንይዋ ወኵሎ ግምዔያቲሃ ዘቅብዕ ዘእ ምውስቴቱ ይገብርዋ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፰፤ ወከመዝ ግበሩ ሎሙ ወየሐይዉ ወኢይመውቱ በበ ዊኦቶሙ ውስተ ቅድስተ ቅዱሳን፡፡

ይሕየዉ ወኢይሙቱ ሲል ነው፡፡ በንግህና በሠርክ በሚደረገው መሥዋዕት ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በመግባታቸው ይድኑ ዘንድ እንጂ እንዳይቀሰፉ እንዲህ አድርጉላቸው ማለት ዕቃውን ሳይሸፈን አይንኩ፤

፲፱፤ አሮን ወደቂቁ ይባኡ ወያስተዳልዉ ሎሙ ያሮሙ ለለአሐዱ እም ኔሆሙ፡፡

አሮንና ልጆቹ ገብተው ከነሱ ላንዱም ላንዱም ሸክማቸውን ያዘጋጁላቸው፤

፳፤ ወኢይባኡ ግብተ ይርአዩ ቅድ ድሳተ ወኢይሙቱ፡፡

እንዳይቀሠፉ ንዋየ ቅድሳቱን ያዩ ዘንድ ድንገት ወደ ደብተራ ኦሪት አይግቡ፤

፳፩፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፡፡

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤

፳፪፤ አኀዝ ወኍልቆሙ ለደቂቀ ጌድሶን እምጥንቱ በበአብያተ አበዊሆሙ ወበበሕዘቢሆሙ፡፡

የጌድሶንን ልጆች ከበኵሩ ጀምረህ በየአባቶቻቸው ወገን በየወገኖቻቸውም ቁጠራቸው፤

፳፫፤ ዘእምዕሥራ ወሐምስቱ ዓም ወላዕሉ እስከ ዘሐምሳ ዓም ኍልቆሙ ለኵሉ ዘይበውእ ይግበር ግብረ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል፡፡

ከሃያ አምስት ዓመት ጀምሮ እስከ ሃምሳ ዘመን ያሉትን ልዩ በሆነች በደብተራ ኦሪት ውስጥ ሥራ ይሠሩ ዘንድ የሚገባቸውን ሁሉ ቁጠራቸው አለው፤

፳፬፤ ወዝንቱ ውእቱ ግብሮሙ ለነገደ ጌድሶን ዘይገብሩ ወይፀውሩ፡፡

የጌድሶን ልጆች የሚሠሩት ሥራ የሚሸከሙት ይህ ነው፡፡ ይህ ነው ያለውን (ያምጣው)፤

፳፭፤ አዕፃዳተ ደብተራ ወሠቃተ ዘመርጡል መክደኒሁ ወመክደን ዘመጸጺት ዘእምላዕሉ ዘዲቤሃ ወመክደኒ ኆኅተ ደብተራ ዘመ ርጡል፡፡

አዕፃደተ፡፡ አሥራ አንዱን ፈርጅ፡፡ ወሠቃተ፡፡ ዓሥሩን ፈርጅ መጋረጃ፡፡ ወመክደኒ ዘመጸጺት፡፡ በላይዋ የሚሆን ብስጥን፡፡ ቀለም የገባ የባሕር ዓረብ፡፡ ወመክደኒ ኆኅት የሃ



ያው ክንድና ያሥሩን ክንድ የውስጥ መጋረጃ፤

፳፮፤ ወመንጦላዕተ ዓፀድኒ ወመክ ደኒ አንቀጸ ዓፀድኒ ዘደብተራ ወኵሉ ንዋየ ግብሮሙ በዘቦቱ ይገብሩ፡፡

የድንኳኑን ዙሪያ መጋረጃ ማለት የመቶውን ክንድ መጋ ረጃ፡፡ ወመክደኒ አንቀጸ ዓፀ ድኒ የደብተራ ኦሪትን የበሩን ሁሉ መጋረጃ፡፡ ሥራቸውን በሚሠሩበት ገንዘብ ዕቃውን ሁሉ ይሸከማሉ (ይሸከሙ)፤

፳፯፤ ወይግበሩ በከመ አዘዝዎሙ አሮን ወደቂቁ ከማሁ ይኩን ግብ ሮሙ ለደቂቀ ጌድሶን በኵሉ ሕቢ ቶሙ ወበኵሉ ግብሮሙ፡፡

የጌድሶን ልጆች ሥራቸው በሰ ሞናቸው በፈንታቸው፡፡ በሥራ ቸው ሁሉ አሮንና ልጆቹ እን ዳዘዟቸው ይሁን፤

ወኍሎቆሙ በበአስማቲሆሙ ለኵሉ ዘይፀውሩ፡፡

የደብተራ ኦሪትን ዕቃዋን የሚሸከሙትን ሁሉ በየስማ ቸው ቆጠራቸው፤

፳፰፤ ዝንቱ ውእቱ ሕቢቶሙ ለደ ቂቀ ጌድሶን በውስተ ደብተራ ዘመርጡል፡፡

የጌድሶን ልጆች በደብተራ ኦሪት ውስጥ የሚሠሩበት ሰሞናቸው ይህ ነው፤

ወሊቃሙ ኢታምር ወልደ አሮን ካህን፡፡

አለቃቸውም የካህኑ የአሮን ልጅ ኢታምር ነው፤

፳፱፤ ወለደቂቀ ሜራሪኒ በበሕዘቢ ሆሙ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ኍልቆሙ፡፡

የሜራሪን ልጆች በየወገ ኖቻቸው በየአባቶቻቸው ወገን ቁጠራቸው፤

፴፤ ዘእምዕሥራ ወሐምስቱ ዓም ወላዕሉ እስከ ዘሐምሳ ዓም ኍል ቈሙ ለኵሉ ዘይበውኡ ይግበሩ ግብረ ደብተራ ዘመርጡል ፡፡

ከሃያ አምስት ዘመን ጀምሮ ከዚያም በላይ እስከ ሃምሳ ዘመን ያለውን የደብተራ ኦሪትን ሥራ ይሠሩ ዘንድ ወደሷ የሚገቡትን ሁሉ ቁጠራቸው አለው፤

፴፩፤ ወዝንቱ ውእቱ ሕቢቶሙ ዘይፀውሩ እሙንቱ በኵሉ ግብ ሮሙ ዘውስተ ደብተራ ዘመር ጡል፤

በደብተራ ኦሪት በሚሠሩት በሥራቸው ሁሉ የሚሸ ከሙት ሰሞናቸው ይህ ነው፤

አርእስቲሃ ለደብተራ ወአዕማዲሃ ወመናሥግቲሃ ወመከየዲሆን ወአ ዕማደ ዘብሩር ዘመንጦላዕተ ኆኅተ

www.ethiopianorthodox.org

፵፪፤ ወኍለቍዎሙ ለነገደ ደቂቀ ሜራሪ በበሕዘቢሆሙ ወበበአብያተ አበዊሆሙ፤

በየአባቶቻቸው ወገን በየወገኖቻቸው የሜራሪንም ልጆች ቈጠሯቸው፤

፵፫፤ ዘእምዕሥራ ወሐምስቱ ዓም ወላዕሉ እስከ ዘሐምሳ ዓም ኵሉ ዘይበውእ ይግበር ውስተ ደብተራ ዘመርጡል፤

ከሃያ አምስት ዘመን ጀምሮ ከዚያም በላይ እስከ ሃምሳ ዘመን ያለውን የደብተራ ኦሪትን ሥራ ይሠራ ዘንድ ወደ ደብተራ ኦሪት የሚገባውን ሁሉ ቈጠሯቸው፤

፵፬፤ ወኮነ ኍላቌሆሙ በበሕዘቢሆሙ ወበበአብያተ አበዊሆሙ ሠላሳ ምእት ወክልኤቱ ምእት፤

የሜራሪ ልጆች በየወገናቸው በየአባቶቻቸው ወገን ቍጥራቸው ሦስት ሺሕ ሁለት መቶ ሆነ፤

፵፭፤ ዝንቱ ውእቱ ኍላቌሆሙ ለነገደ ደቂቀ ሜራሪ ዘኍለቍዎሙ ሙሴ ወአሮን በቃለ እግዚአብሔር ወበእደ ሙሴ፤

በእግዚአብሔር ትእዛዝ በሙሴ ቃል አሮንና ሙሴ የቈጠሯቸው የሜራሪ ልጆች ወገን ቍጥራቸው ይህ ነው፤

፵፮፤ ወኵሉ እለ ተኈለቁ ዘኍለቍዎሙ ሙሴ ወአሮን ወመላእክቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል፤

ሙሴና አሮን የእስራኤልም አለቆች የቈጠሯቸው የተቈጠሩት ቍጥር ይህ ነው፤

ወኵሎሙ እለ ተኈለቁ ሌዋውያን በበሕዘቢሆሙ ወበበአብያተ አበዊሆሙ፤

በየወገናቸው በየአባቶቻቸው ወገን የተቈጠሩ ሌዋውያን ሁሉ፤

፵፯፤ ዘእምዕሥራ ወሐምስቱ ዓም ወላዕሉ እስከ ዘሃምሳ ዓም ኵሉ ዘይበውእ ውስተ ምግባረ ግብር ዘይፀውሩ ዘደብተራ መርጡል፤

ከሃያ አምስት ዘመን ጀምሮ ከዚያም በላይ እስከ ሃምሳ ዓመት ያለው ወደ ደብተራ ኦሪት የሚገቡ የደብተራ ኦሪትን ዕቃ የሚሸከሙ ሁሉ፤

፵፰፤ ኮኑ እለ ተኈለቁ ሰማንያ ምእት ወሰብዓቱ ምእት

ተኈለቁና ተኈለቁ አንድ ወገን ነው፤ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሆኑ፤

፵፱፤ በቃለ እግዚአብሔር ተኈለቁ ብእሲ ብእሲ በበምግባሮሙ ወበበ

ደጀን ሬቻና ቤተሰቡ
የግል ቤተ መጻሕፍት



ፆሮሙ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፤

እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ከእስራኤል አንዱም አንዱም በየሥራቸው በየሸክማቸው በእግዚአብሔር ትእዛዝ ተቈጠሩ።

## ምዕራፍ ፭

## ንባብ

፩፤ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው እንዲህ አለው፤

፪፤ አዝዞሙ ለደቂቀ እስራኤል ከመ ያውፅኡ እምውስተ ትዕይንት ኵሎ ዘለምጽ ወኵሎ ዘይትከዓዎ ዘርኡ ወኵሎ ዘቦቱ ርኵስ ውስተ ነፍስቱ እምተባዕት እስከ አንስት፤

ከወንድ ጀምሮ እስከ ሴት ድረስ በሰውነቱ ርኵሰት ያለውን ዘር የሚፈሰውንና ለምጻሙን ከሰፈራቸው ያወጡ ዘንድ የእስራኤልን ልጆች እዘዛቸው አለው፤

፫፤ ወያወፅእዎሙ አፍአ እምትዕይንት ወኢያርኵሱ ተዓይኒሆሙ ዘውስቴቱ አኀድር አነ፤

ከከተማ ወደውጭ ያውጧቸው፤ እኔ የማድርበት ከተማቸውንም አያርክሱ፤

፬፤ ወገብሩ ከማሁ ደቂቀ እስራኤል ወአውፅእዎሙ አፍአ እምትዕይንት በከመ ይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ከማሁ ገብሩ ደቂቀ እስራኤል፤

እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው የእስራኤልም ልጆች አደረጉ፤ ዘር የሚፈሰውንና ለምጻሙን ከሰፈራቸው አወጧቸው፤

፭፤ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤

፮፤ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ እመኒ ብእሲ ወእመኒ ብእሲት እመቦ ዘገብረ እምኵሉ ኃጣውዕ ዘይገብሩ ኵሉ ዕጓለ እመሕያው ተዐዊሮሙ ወእመኒ በኢያእምሮ፤

ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው ወንድም ቢሆን፤ ሴትም ብትሆን፤ ሰዎች ሁሉ ከሚሠሩት ኃጢአት ሁሉ ቸል ብለው ባለማወቅም ቢሆን የሠሩት ኃጢአት ቢኖር፤

www.ethiopianorthodox.org

ካህኑ መሥዋዕቱን ባቀረበበት ቀን ራሱን ከኃጢአት ያነጻዋል፤

፲፪፤ ወይትቀደስ ለእግዚአብሔር በኵሉ መዋዕለ ብፅዓቲሁ ወያመጽእ በግዐ ዘዓመት ዘንስሐ፤

በተሳለበት ወራት ሁሉ ለእግዚአብሔር የተለየ ይሁን፤ ኃጢአቱንም ለማስተሥረይ ዓመት የሆነው ጠቦት ያምጣ፤

ወመዋዕል ቀዲሙስ ኢይትኌለቍ ሎቱ እስመ ረኵሰ ብፅዓተ ርእሱ፤

ከሞተው ሰው ቤት በመግባቱ ብፅዓቱ (ስእለቱ) ፈርሷልና የቀደመው የብፅዓቱ ወራት አይቈጠርለትም ፤

፲፫፤ ወዝንቱ ሕጉ ለዘበፅዓ አመ ዕለተ ይትፌጸም መዋዕለ ብፅዓቲሁ ይመፅእ ሊሊተ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል፤

ስዕለት ለተሳለ ሰው ሥርዓቱ ይህ ነው፣ የተሳለበት ወራት በተፈጸመ ጊዜ ልዩ ወደ ሆነች ድንኳን በሌሊት ይምጣ፤

፲፬፤ ወያበውእ ቍርባኖ ለእግዚአብሔር በግዓ ዘዓመት አሐደ ንጹሐ ለመሥዋዕት ወአሐተ በግዕተ ንጽሕተ ዘዓመት በእንተ ኃጢአት

ወሐርጌ አሐደ ንጹሐ ለመሥዋዕተ መድኃኒት፤

መሥዋዕት ሊሆነው ነውር የሌለበት አንድ ዓመት የሆነው የበግ ጠቦት፣ ሁለተኛ አንዲት ጠቦት በግ ስለ ኃጢአት ማስተሥረያ፣ ሦስተኛ የድኅነት መሥዋዕት ሊሆን አንድ ሙክት ለእግዚአብሔር ቍርባን አድርጎ ያቅርብ፤

፲፭፤ ወከፈረ ኅብስተ ስንዳሌ ዘናዕት ዘግቡር በቅብዕ ወጸራይቀ ናዕት ዘግቡር በቅብዕ ለመሥዋዕቶሙ ወሞጻሕቶሙ፤

በዘይት የታሸ ያልቦካ ድፎና ልጦ ጉርዶ የወጣለትን የስንዴ አንባሻ፣ ፍልቅ አድርገው የሚያፈሱትን ወይናቸውንና መሥዋዕታቸውን ያምጣ፤

፲፮፤ ወያበውእ ካህን ቅድመ እግዚአብሔር ወይገብር ካህን ዘበእንተ ኃጢአት ወመሥዋዕት፣

ካህኑ ወደ ቤተ እግዚአብሔር አግብቶ ኃጢአት ለማስተሥረይ መሥዋዕት ሊሆነው ያመጣውን በግ ይሠዋው፤

፲፯፤ ወይገብር ሐርጌኒ ለመሥዋዕተ መድኃኒት ለእግዚአብሔር ምስለ ዝንቱ ከፈር ዘናዕት፣



የድኅነት መሥዋዕት የሚሆን ሙክቱንም በዕንቅብ ካለው አንባሻ ጋር ያቅርብ፤

ወይገብር ካህን መሥዋዕቶ ወሞጻሕቶ፣

ካህኑም መሥዋዕቱንና ፍልቅ አድርጎ የሚያቀርበውን ወይኑን በመሠዊያው ላይ ያድርገው፤

፲፰፤ ወይላጺ ውእቱ ዘበፅዓ በኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ርእሰ ብፅዓቲሁ ወይወዲ ሥእርቶ ላዕለ እሳት ዘመሥዋዕተ መድኃኒት፣

የተሳለው ሰው ልዩ በሆነች ድንኳን ደጃፍ የብፅዓቱን ጠጕሩን ተላጭቶ፣ ጠጕሩን የድኅነት መሥዋዕት በሚሠዋበት እሳት ላይ ይጨምረው፤

፲፱፤ ወይነሥእ ካህን መዝራዕቶ በአንዳሁ እምሐርጌ ወኅብስተ ናዕት አሐተ እምከፈር ወአሐተ ጸሪቀ ናዕት ወያንብር ውስተ እደዊሁ ለዘበፅዓ እምድኅረ ተላፀየ ርእሶ፣

ካህኑም ከሙክቱ ወርቹን በቁርበቱ ጠቅሎ ወስዶ አንዲት ያልቦካች ድፎ ከመሶብ ወስዶ፣ አንዲት አምባሻ አድርጎ ራሱን ከተላጨ በኋላ በተሳለው ሰው እጆች ያኑር፤

፳፤ ወያበውእ ካህን ቍርባኖ ቅድመ እግዚአብሔር ወቅዱስ ይከውን ለካህን ተላዕ ዘቍርባን ወመዝራዕት ዘመባዕ፣

ካህኑም በእግዚአብሔር ፊት ቍርባን አድርጎ ያቅርብ፣ ለመሥዋዕት የቀረበው የሙክቱ ፈርንባ የመባው ወርች ለካህኑ የተለየ ይሁን፤

ወእምድኅረ ዝንቱ ይሰቲ ወይነ ውእቱ ዘበፅዐ፣

ከዚህ በኋላ ማለት ብፅዓቱ ከተፈጸመ በኋላ የተሳለው ሰው ወይን ይጠጣ፤

፳፩፤ ወዝንቱ ሕጉ ለዘበፅዐ እምከመ በፅዐ ዘያመጽእ ለእግዚአብሔር ቍርባኖ በእንተ ብፅዓቲሁ ዘረከበ ውስተ እዴሁ በአምጣነ ይትከሃሎ ይግበር ለብፅዓቲሁ ዘበፅዐ በሕገ አንጽሖ፣

ለተሳለ ሰው ሥርዓቱ ይህ ነው፣ ከተሳለ በኋላ ስለተሳለው ስዕለት ቍርባን አድርጎ ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው ንጹሕ ከሚያሰኘው ሥርዓት ለተሳለው ስለት በእጁ ያገኘውን የተቻለውን ያህል ያምጣ፤

ጉባኤ

፳፪፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣

www.ethiopianorthodox.org

፳፩፤ ወላሕመ አሐደ ወበግዐ አሐደ ወመሐስአ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዓመት ለመሥዋዕት፤

አንድ ላም፤ አንድ በግ ለመሥዋዕት የሚሆን ዓመት የሆነው አንድ የበግ ጠቦት አገባ፤

፳፪፤ ወሐርጌ እምአጣሊ አሐደ በእንተ ኃጢአት፤

የኃጢአት ማስተሥረያ ሊሆን ከፍየሎች መርጦ አንድ የፍየል ሙክት አገባ፤

፳፫፤ ወለመሥዋዕተ መድኃኒት ክልኤ አጉልተ ወሐምስተ አባግዐ ወሐምስተ አጣሌ ወሐምስተ አባግዓ አንስተ፤

የድኅነት መሥዋዕት ሊሆኑ ሁለት ጊደር አምስት ተባት በጎች አምስት ፍየሎች፤ አምስት እንስት በጎች አገባ፤

ወዝንቱ ውእቱ ቍርባኑ ለናትናኤል ወልደ ሰገር፤

የሰገር ልጅ ናትናኤል ያገባው መባ ይህ ነው፤

፳፬፤ ወበሣልስት ዕለት አብአ መልአከሙ ለደቂቀ ዛብሎን ኤልያብ ወልደ ኬሎን ቍርባኖ፤

በሦስተኛይቱ ቀን የዛብሎን ልጆች አለቃ የኬሎን ልጅ ኤልያብ መባውን አገባ፤

፳፭፤ መጽብሐ አሐደ ዘብሩር ዘምእት ወሠላሳ በሰቅል ወፍያለ አሐደ ዘብሩር ሰብዓ በሰቅሎን በሰቅል ቅዱስ፤

ሚዛኑ መቶ ሠላሳ ወቄት የሚሆን አንድ የብር ወጭት በቤተ መቅደስ ዓዋቂ (ሚዛን) ሰባ ወቄት የሚሆን አንድ ጣስ አገባ፤

ወክልኤሆሙ ምሉዓን ስንዳሌ ዘግቡር በቅብዕ ለመሥዋዕት፤

ሁለቱም መሥዋዕት ሊሆን በዘይት የታሸ ስንዴን የተመሉ ናቸው፤

፳፮፤ ወጸሕለ አሐደ ዘአሥሩ ወርቀ ወምሉዕ ዕጣነ፤

ሚዛኑ አስር ወቄት የሚሆን ዕጣንን የተመላ አንድ ታናሽ የወርቅ ወጭት አገባ፤

፳፯፤ ወላሕመ አሐደ እምአልሕምት ወበግዐ አሐደ ወመሐስአ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዓመት ለመሥዋዕት፤

ከላሞች መርጦ አንድ ላም፤ አንድ በግ ለመሥዋዕት የሚሆን ዓመት የሆነው ንጹሕ የሆነ አንድ የበግ ጠቦት አገባ፤



፳፰፤ ወሐርጌ እምአጣሊ አሐደ በእንተ ኃጢአት፤

ኃጢአት ስለማስተሥረይ ከፍየሎች አንድ ሙክት አገባ፤

፳፱፤ ወለመሥዋዕተ መድኃኒት ክልኤተ ዕጉልተ ወሐምስተ አባግዓ ወሐምስተ አጣሌ ወሐምስተ አባግዓ አንስተ፤

ድኅነት ለሚደረግበት መሥዋዕት ሁለት ጊደሮች፤ አምስት ተባት በጎች፤ አምስት ፍየሎች፤ አምስት እንስት በጎች አገባ፤

ዝንቱ ውእቱ ቍርባኑ ለኤልያብ ወልደ ኬሎን፤

የኬሎን ልጅ ኤልያብ ያገባው መባ ይህ ነው፤

፴፤ ወበራብዕት ዕለት አብአ ኤሌሱር ወልደ ሴድዩር መልአኮሙ ለደቂቀ ሮቤል ቍርባኖ፤

በአራተኛይቱም ቀን የሮቤል ልጆች አለቃ የሴድዩር ልጅ ኤሌሱር መባውን አገባ፤

፴፩፤ መጽብሐ ዘብሩር አሐደ ዘምእት ወሠላሳ በሰቅል ወፍያለ ዘብሩር አሐደ ዘሰብዓ በሰቅሎን በሰቅል ቅዱስ፤

ሚዛኑ መቶ ሠላሳ ወቄት የሚሆን አንድ ታላቅ የብር ወጭት በቤተ መቅደስ ሚዛን ሰባ ወቄት የሚሆን አንድ ታናሽ የብር ጣስ አገባ፤

ወክልኤሆሙ ምሉዓን ስንዳሴ ዘግቡር በቅብዕ ለመሥዋዕት፤

ሁለቱም መሥዋዕት ሊሆን በዘይት የታሸ ስንዴ የተመሉ ናቸው፤

፴፪፤ ወፃሕለ አሐደ ዘዓሥሩ ወርቀ ዘምሉዕ ዕጣነ፤

ዕጣንን የተመላ ዐሥር ወቄት ወርቅ የሚሆን አንድ ታናሽ የወርቅ ወጭት አገባ፤

፴፫፤ ወላሕመ አሐደ ወበግዐ አሐደ መሐስአ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዐመት ለመሥዋዕት፤

አንድ ላም አንድ በግ መሥዋዕት ሊሆን ዓመት የሆነው ንጹሕ የሆነ አንድ የበግ ጠቦት አቀረበ፤

፴፬፤ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት፤

ኃጢአት ስለማስተሥረይ ከፍየሎች መርጦ አንድ ሙክት አቀረበ፤

፴፭፤ ወለመሥዋዕተ መድኃኒት ክልኤተ ዕጉልተ ወሐምስተ አባግዓ ወሐምስተ አጣሌ ወሐምስተ አባግዓ አንስተ፤

www.ethiopianorthodox.org

ድኅነት የሚደረግበት መሥዋዕት ሲሆን ሁለት ጊደር፣ አምስት ተባት በጎች አምስት ፍየሎች፣ አምስት እንስት በጎች አገባ፤

ወዝንቱ ውእቱ ቍርባኑ ለኤሌሱር ወልደ ሴድዩር፣

የሴድዩር ልጅ ኤሌሱር ያገባው መባ ይህ ነው፤

፴፮፤ ወበሐምስ ዕለት አብአ ሰላምያል ወልደ ሲሩሳዴ መልአኮሙ ለደቂቀ ስምዖን ቍርባኖ፣

ባምስተኛይቱ ቀንም የስምዖን ልጆች አለቃ የሲሩሳዴ ልጅ ሰላምያል መባውን አገባ፤

፴፯፤ መጽብሐ ዘብሩር አሐደ ዘምዕት ወሠላሳ በሰቅል ወፍያለ ዘብሩር አሐደ ዘሰብዓ በሰቅሎን በሰቅል ዘቅዱስ፣

ሚዛኑ መቶ ሠላሳ ወቄት የሚሆን አንድ ታላቅ የብር ወጭት በቤተ መቅደስ ሚዛን ሰባ ወቄት የሚሆን አንድ ታናሽ የብር ጣስ አገባ፤

ወክልኤሆሙ ምሉዓነ ሥንዳሌ ዘግቡር በቅብዕ ለመሥዋዕት፣

ሁለቱም መሥዋዕት ሲሆን በዘይት የታሸ ስንዴን የተመሉ ናቸው፤

፴፰፤ ወጻሕለ አሐደ ዘዐሥሩ ወርቁ ወምሉዕ ዕጣነ፣

ዕጣንን የተመላ ዐሥር ወቄት ወርቅ የሆነ አንድ ታናሽ የወርቅ ወጭት አገባ፤

፴፱፤ ወላሕመ አሐደ ወበግዐ አሐደ ወመሐስዐ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዓመት ለመሥዋዕት፤

ከላሞች መርጦ አንድ ላም፣ አንድ የበግ ሙክት ዓመት የሆነው ንጹሕ የሆነ፣ አንድ የበግ ጠቦት መሥዋዕት ሲሆን አቀረበ፤

፵፤ ወሐርጌ አሐደ አምአጣሊ በእንተ ኃጢአት፣

ኃጢአት ስለማስተሥረይ ከፍየሎች አንድ ሙክት መርጦ አቀረበ፤

፵፩፤ ወለመሥዋዕተ መድኃኒት ክልኤተ ዕጐልተ ወሐምስተ አባግዓ ወሐምስተ አጣሌ ወሐምስተ አባግዓ አንስተ፣

ድኅነት ለሚደረግበት መሥዋዕት ሁለት ጊደሮች፣ አምስት ተባት በጎች፣ አምስት ፍየሎች አምስት (እንስት) ሴቶች በጎች አገባ፤

ዝንቱ ውእቱ ቍርባኑ ለሰላምያል ወልደ ሲሩሳዴ፣



የሲሩሳዴ ልጅ ሰላምያል ያገባው መባ ይህ ነው፤

፵፪፤ ወበሳድስት ዕለት አብአ ኤልሳፍ ወልደ ራጉኤል መልአኮሙ ለደቂቀ ጋድ ቍርባኖ፣

በስድስተኛይቱ ቀን የጋድ ልጆች አለቃ የራጉኤል ልጅ ኤልሳፍ መባውን አገባ፤

፵፫፤ መጽብሐ ዘብሩር አሐደ ዘምእት ወሠላሳ በሰቅል ወፍያለ ዘብሩር አሐደ ዘሰብዓ በሰቅሎን በሰቅል ዘቅዱስ፣

ሚዛኑ መቶ ሠላሳ ወቄት የሚሆን አንድ ታላቅ የብር ወጭት በቤተ መቅደስ ሚዛን ሰባ ወቄት የሚሆን አንድ የብር ጣስ አገባ፤

ወክልኤሆሙ ምሉዓነ ስንዳሌ ዘግቡር በቅብዕ ለመሥዋዕት፣

ሁለቱም መሥዋዕት ሲሆን በዘይት የታሸ ስንዴን የተመሉ ናቸው፤

፵፬፤ ወጻሕለ አሐደ ዘአሥሩ ወርቁ ወምሉዕ ዕጣነ፣

ዕጣንን የተመላ ወርቁ አሥር ወቄት የሚሆን አንድ ታናሽ የወርቅ ወጭት አገባ

፵፭፤ ወላሕመ አሐደ እምአልሕምት ወበግዐ አሐደ ወመሐስአ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዓመት ለመሥዋዕት፣

ከላሞች መርጦ አንድ የሰባ ላም፣ አንድ የበግ ሙክት፣ ንጹሕ የሆነ አንድ የበግ ጠቦት አገባ፤

፵፮፤ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት፣

ኃጢአት ስለማስተሥረይ ከፍየሎች አንድ ሙክት አገባ፤

፵፯፤ ወለመሥዋዕተ መድኃኒት ክልኤተ ዕጐልተ ወሐምስተ አባግዐ ወሐምስተ አጣሌ ወሐምስተ አባግዓ አንስተ፣

ድኅነት ለሚደረግበት መሥዋዕት ሁለት ጊደሮች፣ አምስት ተባት በጎች አምስት ፍየሎች አምስት ሴቶች (እንስት) በጎች አቀረበ፤

ወዝንቱ ውእቱ ቍርባኑ ለኤልሳፍ ወልደ ራጉኤል፣

የራጉኤል ልጅ ኤልሳፍ ያገባው መባ ይህ ነው፤

፵፰፤ ወበሳብዕት ዕለት አብአ ኤልሳማ ወልደ ኤምዩድ መልአኮሙ ለደቂቀ ኤፍሬም ቍርባኖ፣

በሰባተኛው ቀን የኤፍሬም ልጆች አለቃ የኤምዩድ ልጅ ኤልሳማ መባውን አገባ፤

www.ethiopianorthodox.org

፷፫፤ ወላሕመ አሐደ ወበግዐ አሐደ ወመሐስዐ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዓመት ለመሥዋዕት ፤

አንድ ላም፣ አንድ በግ ንጹሕ የሆነ ዓመት የሆነው አንድ የበግ ጠቦት መሥዋዕት ሲሆን አቀረበ፤

፷፬፤ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት ፤

ኃጢአት ስለ ማስተሥረይ አንድ የፍየል ሙክት አገባ ፤

፷፭፤ ወለመሥዋዕተ መድኃኒት ክልኤተ ዕጐልተ ወሐምስተ አባግዐ ወኀምስተ አጣሌ ወሐምስተ አባግዓ አንስተ ፤

ለድኅነት መሥዋዕት ሁለት ጊደሮች፣ አምስት ተባት በጎች፣ አምስት ፍየሎች፣ አምስት እንስት በጎች አገባ ፤

ዝንቱ ውእቱ ቍርባኑ ለአቢዳን ወልደ ጋድዮን ፤

የጋድዮን ልጅ አቢዳን ያገባው መባ ይህ ነው ፤

፷፮፤ ወበአሥር ዕለት አብአ አክያዜር ወልደ አሚሳዲ መልአከሙ ለደቂቀ ዳን ቍርባኖ ፤

በአሥረኛውም ቀን የዳን ልጆች አለቃ የሚሆን የአሚሳዲ ልጅ አክያዜር መባውን አገባ ፤

፷፯፤ መጽብሐ ዘብሩር አሐደ ዘምዕት ወሠላሳ በሰቅል ወፍያለ ዘብሩር አሐደ ዘሰብዓ በሰቅሎን በሰቅል ዘቅዱስ ፤

መቶ ሠላሳ ወቄት የሚሆን አንድ የብር ወጭት በቤተ መቅደስ ሚዛን ሰባ ወቄት የሚሆን አንድ የብር ጣስ አገባ፤

ወክልኤሆሙ ምሉዓነ ሥንዳሌ ዘግቡር በቅብዕ ለመሥዋት ፤

ሁለቱም መሥዋዕት ሲሆን በዘይት የታሸ የስንዴ ዱቄትን የተመሉ ናቸው፤

፷፰፤ ወጸሕለ አሐደ ዘአሥሩ ወርቁ ወምሉዕ ዕጣነ ፤

ዕጣንን የተመላ ወርቁ አሥር ወቄት የሚሆን አንድ ታናሽ የወርቅ ወጭት አገባ፤

፷፱፤ ወላህመ አሐደ ወበግዐ አሐደ ወመሐስዐ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዓመት ለመሥዋዕት ፤

መሥዋዕት ሲሆን አንድ ላም፣ አንድ በግ ዓመት የሆነው ንጹሕ የሆነ አንድ የበግ ጠቦት አቀረበ ፤

፸፤ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት፣



ስለ ኃጢአት የሚሠዋ ከፍየ ሎች አንድ ሙክት አገባ ፤

፸፩፤ ወለመሥዋዕተ መድኃኒት ክልኤተ ዕጐልተ ወሐምስተ አባግዐ ወሐምስተ አጣሌ ወሐምስተ አባ ግዓ አንስተ ዘዘዓመት ፤

ለድኅነት መሥዋዕት ሲሆን ሁለት ጊደሮች፣ አምስት ተባት በጎች፣ አምስት ፍየሎች፣ አም ስት እንስት በጎች አገባ፤

ወዝንቱ ውእቱ ቍርባኑ ለአክያዜር ወልደ አሚሳዲ ፤

የአሚሳዲ ልጅ አክያዜር ያገ ባው መባ ይህ ነው ፤

፸፪፤ ወአመ ዐሡሩ ወአሚሩ ዕለት አብአ ፋጌኤል ወልደ ኤክራን መል አከሙ ለደቂቀ አሴር ቍርባኖ ፤

በአሥራ አንደኛው ቀን የአሴር ልጆች አለቃ የሚሆን የኤክ ራን ልጅ ፋጌኤል መባውን አገባ

፸፫፤ መጽብሐ ዘብሩር አሐደ ዘምዕት ወሠላሳ በሰቅል ወፍያለ ዘብሩር አሐደ ዘሰብዓ በሰቅሎን በሰቅል ዘቅዱስ ፤

መቶ ሠላሳ ወቄት የሚሆን የብር ወጭት በቤተ መቅደስ ሚዛን ሰባ ወቄት የሚሆን አንድ የብር ጣስ አገባ ፤

ወክልኤሆሙ ምሉኣነ ስንዳሌ ዘግቡር በቅብዕ ለመሥዋዕት ፤

ሁለቱም በዘይት የታሸ ልጦ ጉርዶ የወጣለትን ስንዴ የተመሉ ናቸው ፤

፸፬፤ ወጸሕለ አሐደ ዘአሥሩ ወርቁ ወምሉዕ ዕጣነ ፤

ዕጣንን የተመላ የወርቁ ሚዛን አሥር ወቄት የሆነ አንድ የወርቅ ወጭት አገባ ፤

፸፭፤ ወላሕመ አሐደ ወበግዐ አሐደ ወመሐስዐ በግዕ አሐደ ንጹሐ ዘዓመት ለመሥዋዕት :

አንድ ላም አንድ በግ አንድ የበግ ጠቦት መሥዋዕት ሲሆን አቀረበ ፤

፸፮፤ ወሐርጌ አሐደ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት ፤

ኃጢአት ስለማስተሥረይ አንድ የፍየል ሙክት አገባ፤

፸፯፤ ወለመሥዋዕተ መድኃኒት ክልኤተ ዕጐልተ ወሐምስተ አባግዐ ወሐምስተ አጣሌ ወሐምስተ አባግዓ አንስተ ዘዘዓመት ፤

ለድኅነት መሥዋዕት ሁለት ጊደር፣ አምስት ተባት በጎች አምስት ፍየሎች፣ አምስት እንስት በጎች አገባ፤

www.ethiopianorthodox.org

ዕኒ ስሳ ወአባሊዒ ስሳ ወአባግዕ አንስት ዘዘዓመት ንጹሐት ፤

ድኅነት የሚያሰጥ መሥዋዕት ሲሆኑ ከአሥራ ሁለት አለቆች የቀረቡት ሃያ አራት ጊደ ሮች፣ ስሳ ተባት በጎች፣ ስሳ ፍየሎች፣ ዓመት ዓመት የሆና ቸው ስሳ እንስት በጎች ናቸው፣

ከመዝ ውእቱ መድቅሐ ምሥዋዕ እምድኅረ ቀብዓ ፤

ቀብቶ ካከበራት በኋላ መሠ ዊያው የሚታደስበት የሚቀደስ በት እንዲህ ነው ፤

፹፱፤ ወሶበ ይበውእ ሙሴ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ከመ ይትናገሮ ይሰምዕ ቃለ እግዚአብሔር እንዘ ይትናገሮ እመልዕልተ ምስሐል ዘዲበ ታቦት ዘመርጡል እማዕከለ ክል ኤቱ ኪሩባት ወይትናገር ምስሌሁ፣

እግዚአብሔር ይናገረው ዘንድ ሙሴ ልዩ ወደሆነች ድንኳን በገባ ጊዜ በሁለቱ ኪሩቤል መካከል ባለ በታቦቱ መግጠ ሚያ ላይ ሁኖ ሲናገረው የእግ ዚአብሔርን ቃል ይሰማ ነበር ከሱም ጋር ይነጋገር ነበር ።

## ምዕራፍ ፰

፩፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው ፤

፪፤ ንግሮ ለአሮን ወበሎ እምነ መንገለ ገቦሃ ለገጸ አንብር መኃት ዊሃ ለመራናት ወአኀትዎን ለሰብዐ መኃትዊሃ ፤

በደብተራ ኦሪት መግቢያ አጠ ገብ የተቀዋምን መቅረዟን አኑር፣ ሰባቱን አዕጹቆቿን መብራቶቿንም አብራቸው ብለህ ለአሮን ንገረው አለው፤

፫፤ ወገብረ ከማሁ አሮን እምአሐዱ ገቦሃ ዘመንገለ ገጸ ለመራናት አኅተወ መኃትዊሃ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ፤

አሮንም እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው አደረገ፣ በደብተራ ኦሪት መግቢያ አጠገብ የተቀዋ ምን መብራቶች አበራ፤

፬፤ ወከመዝ ውእቱ ግብረታ ለመራናት ወአዕጹቂሃኒ ጽኑዓን ዘወርቅ ኵለንታሆሙ ወጽጌያቲሃኒ ጽኑዓን ኵለንታሆሙ ፤

የመቅረዝም ሥራ እንዲህ ነው፣ ሁለንተናቸው የወርቅ



የሚሆኑ አጽቆቿ ሥረወጥ ናቸው፣ አበባዎቿም በሁለን ተናቸው ሥረወጥ ናቸው ፤

በከመ አርአያ ዘአርአዮ እግዚ አብሔር ለሙሴ ከማሁ ገብራ ለመራናት ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዳሳ የው አምሳል መቅረዚቱን እን ደዚያው ሠራት፤

### ጉባኤ

፭፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው ፤

፮፤ ንሥኦሙ ለሌዋውያን እማዕከ ሎሙ ለደቂቀ እሥራኤል ወአንጽ ሖሙ፣

የሌዊን ልጆች ከእሥራኤል ልጆች መካከል ለይተህ አንጻቸው፤

፯፤ ወከመዝ ትገብር ሎሙ ከመ ታንጽ ሖሙ ወትነዝኖሙ በማየ አንጽሖ፤

ታነጻቸው ዘንድ እንዲህ አድርግ በሚያነጻ ውሀ እርጫቸው፤

ወይላጽዩ ኵሎ ሥጋሆሙ ወይ ሕጽቡ አልባሲሆሙ ወንጹሐነ ይከውኑ ፤

ራሳቸውን ሁሉ ይላጩ ልብሳ ቸውን ይጠቡ የነጹም ይሁኑ፤

፰፤ ወይንሥኡ አሐደ ላሕመ እምአልሕምት ወሎቱኒ መሥዋዕተ ሥንዳሴ ዘግቡር በቅብዕ ፤

ከላሞችም አንድ ላም ያምጡ፣ ለሱም በዘይት የታሸ የስንዴ መሥዋዕት ያምጡ ፤

ወካልአ ላሕመ ዘዓመት ይንሥኡ በእንተ ኃጢአት ፤

ኃጢአት ስለማስተሥረይም ዓመት የሆነው ሌላ ላም መርጠው ያምጡ ፤

፱፤ ወታመጽኦሙ ለሌዋውያን ቅድመ ደብተራ ዘመርጡል ወታስ ተጋብእ ኵሎ ተዓይኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ፣

የሌዊን ልጆች ወደ ደብተራ ኦሪት ደጃፍ አምጣቸው፣ የእስ ራኤልንም ልጆች ሠራዊት ሰብስብ ፤

፲፤ ወታቀርቦሙ ለሌዋውያን ቅድመ እግዚአብሔር ወይወድዩ እደዊሆሙ ደቂቀ እስራኤል ላዕለ ሌዋውያን ፣

ሌዋውያንን በእግዚአብሔር ፊት አቅርባቸው፣ የእስራኤ ልም ልጆች እጃቸውን በሌዊ ልጆች ላይ ያኑሩ፣ ኃጢ አታችን በናንተ ምክንያት ይሠረያል ሲሉ ነው፣

www.ethiopianorthodox.org

፲፩፤ ወያፈልጦሙ አሮን ለሌዋውያን ቅድመ እግዚአብሔር እም ደቂቀ እስራኤል ወይከውኑ ለግብረ እግዚአብሔር አሉ ይገብሩ ፡፡

አሮን ሌዋውያንን በእግዚአብሔር ፊት ከእስራኤል ይለያቸው፣ የእግዚአብሔርን ሥራ የሚሠሩ ይሁኑ ፡፡

፲፪፤ ወሌዋውያን ይወድዩ እደዊሆሙ ዲበ አርእስተ አልሕምት ፡፡

ሌዋውያን በላሞቹ ራስ ላይ እጃቸውን ያኑሩ፣ ኃጢአታችን በናንተ ምክንያት ይሠረያል ሲሉ ፡፡

ወይገብር አሐደ ዘበእንተ ኃጢአት ወአሐደ ለመሥዋዕተ እግዚአብሔር ወያስተሠሪ በእንቲአሆሙ ፡፡

አሮን አንዱን ኃጢአት ስለ ማስተሥረይ፣ አንዱን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ ያቅርብ በነሱም ምክንያት ኃጢአታቸውን ያስተሥርይላቸው፡፡

፲፫፤ ወታቀውሞሙ ለሌዋውያን ቅድመ አሮን ወቅድመ ደቂቁ ወታገብኦሙ ሀብቶ ለእግዚአብሔር ፡፡

ሌዋውያንን የእግዚአብሔር ፈንታ አድርገህ በአሮንና በልጆቹ ፊት አቁማቸው ፡፡

፲፬፤ ወትፈልጦሙ ለሌዋውያን እማዕከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ወይከውኑኒ ሊተ ፡፡

ሌዋውያንን ከእስራኤል ልጆች መካከል ለያቸው፣ ለኔም አገልጋይ ይሁኑኝ ፡፡

፲፭፤ ወእምድኅረ ዝንቱ ይበውኡ ሌዋውያን ይግበሩ ግብረ ደብተራ ዘመርጡል ፡፡

ከዚህ በኋላ የደብተራ ኦሪትን ሥራ ይሠሩ ዘንድ ሌዋውያን ወደ ደብተራ ኦሪት ይግቡ አለው ፡፡

ወታነጽሖሙ ወታገብኦሙ ቅድሜየ እስመ ሀብተ ገብኡ ሊተ እሙንቱ እማዕከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ፡፡

ከእሥራኤል ልጆች ተለይተው እነሱ ለኔ ስጦታ ተሰጥተዋልና ንጹሕ አድርገህ ወደኔ አምጣቸው፡፡

፲፮፤ ህየንተ ኵሉ ዘይፈትሕ ማኅፀነ ዘእምኵሉ በኵሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ነሣእክዎሙ ሊተ ፡፡

ከእስራኤል ልጆች በኵር ሁኖ ስለሚወለደው ሁሉ ፈንታ እኔን ሊያገለግሉ ተቀብያቸዋለሁና፡፡

፲፯፤ እስመ ሊተ ውእቱ ኵሉ በኵር ዘእምደቂቀ እስራኤል እምነ ሰብእ እስከ እንስሳሁ በዕለተ እንተ ባቲ ቀተልክዎሙ ለኵሎሙ በኵር ዘውስተ ምድረ ግብጽ ወቀደ ስክዎሙ ሊተ ፡፡

የግብጽን በኵር በኵሩን በገደልኩበት ቀን ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ ድረስ ከእስራኤል ልጆች በኵር በኵሩ ለኔ ነውና ለኔ አገልጋይ ሲሆኑ ለየኊቸው ፡፡

፲፰፤ ወነሣእክዎሙ ለሌዋውያን ህየንተ ኵሉ በኵር ዘእምደቂቀ እስራኤል ፡፡

ከእስራኤል ልጆች መጀመሪያ ስለሚወለደው ፈንታ ሌዋውያንን ተቀበልኊቸው ፡፡

፲፱፤ ወአግባእክዎሙ ለሌዋውያን ሀብተ ወተውህበ ለአሮን ወለደቂቁ እማዕከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል ከመ ይግበሩ ግብሮሙ ለደቂቀ እስራኤል በውስተ ደብተራ ዘመርጡል ፡፡

ሌዋውያንን ለኔ ስጦታ አድርጌ አስገባኊቸው፣ ልዩ በሆነች ድንኳን የእስራኤልን ልጆች ሥራ ይሠሩ ዘንድ ከእስራኤል ልጆች መካከል ተለይተው ለአሮንና ለልጆቹ ተሰጡ ፡፡

ወያስተሥርዩ በእንቲአሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ፡፡



የእስራኤልን ልጆች ኃጢአትም ያስተሠርዩ ዘንድ፡፡

ወአልቦ እምደቂቀ እስራኤል ዘይቀርብ ኀበ ቅድሳት ፡፡

ከእስራኤል ልጆች ግን ወደ ቤተ መቅደስ የሚቀርብ አይኑር ፡፡

፳፤ ወገብሩ ሙሴ ወአሮን ወኵሉ ተዓይኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ላዕለ ሌዋውያን በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ በእንተ ሌዋውያን ከማሁ ገብሩ ሎሙ ደቂቀ እስራኤል፡፡

ሙሴና አሮን የእስራኤል ሠራዊትም ሁሉ እግዚአብሔር ስለሌዋውያን እንዳዘዘው በሌዋውያን የታዘዘውን ሁሉ አደረጉላቸው፡፡

፳፩፤ ወአንጽሑ ርእሶሙ ሌዋውያን ወሐፀቡ አልባሲሆሙ ወአግብእዎሙ ኀበ አሮን ሀብተ ቅድመ እግዚአብሔር ፡፡

ሌዋውያንም ራሳቸውን ንጹሕ አደረጉ፣ ልብሳቸውንም አጥበው በእግዚአብሔር ፊት ስጦታ አድርገው ወደ አሮን አገቧቸው፡፡

ወአስተሥረየ በእንቲአሆሙ አሮን ከመ ያንጽሖሙ ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

አሮንም ከኃጢአት ከሐኬት ያነ ጻቸው ዘንድ ስለነሱ ማለደ፤

፳፪፤ ወእምድኅረ ዝንቱ ቦኡ ሌዋውያን ይግበሩ ግብሮሙ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ቅድመ አሮን ወቅድመ ደቂቁ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ በእንተ ሌዋ ውያን ከማሁ ገብሩ ሎሙ፤

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ስለሌዋውያን ሙሴን እንዳ ዘዘው በደብተራ ኦሪት ሥራ ቸውን ይሠሩ ዘንድ ሌዋ ውያን ወደ ደብተራ ኦሪት ገቡ፤

፳፫፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው ፤

፳፬፤ ዝንቱ ውእቱ ዘበእንተ ሌዋውያን ዘእምዕሥራ ወሐምስቱ ዓም ወላዕለ ይበውኡ ይግበሩ ግብሮሙ ግብረ ደብተራ ዘመርጡል እስከ ዘሐምሳ ዓም ፤

ለሌዋውያን የሚሠራው ሥራት ይህ ነው፣ ከሃያ አምስት ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ እስከ ሃምሳ ዘመን ያሉት የደብተራ ኦሪትን ሥራ ይሠሩ ዘንድ ወደ ደብተራ ኦሪት ይግቡ ብሎ ነገረው ፤

፳፭፤ ወእምድኅረ ሐምሳ ዓም ይሠዓር እምግብረ ደብተራ ወኢይትቀነይ እንከ ውእቱ፣

ከሃምሳ ዘመን በኋላ ግን ከሹ መቱ ይሻር፣ የደብተራ ኦሪ ትንም ሥራ አይሥራ ፤

፳፮፤ ወይትለአክ እኁሁ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ወይዕቀብ ሕቢ ቶሙ ወተቀኖ ባሕቲ ኢይትቀነይ ፤

በርሱ ፈንታ ወንድሙ በደ ብተራ ኦሪት ያገለግል፣ ከሹ መቱ የተሻረውም ሰው ሰሞ ናቸውን ይጠብቅ፣ አንተ ዛሬ ግባ፣ አንተ ዕረፍ እያለ ይጠ ብቅ፣ ነገር ግን እንደ ሹመቱ ወራት አያገልግል ፤

ወከመዝ ትገብር ሎሙ ለሌዋ ውያን በበሕቢቶሙ ፤

ለሌዋውያን በየሰሞናቸው እን ዲህ አድርግላቸው።

## ምዕራፍ ፱

፩፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ በገዳም ዘሲና በካልዕ ዓመት እምዘወፅኡ ደቂቀ እስራኤል እም ድረ ግብጽ በቀዳሚ ወርኅ ፤

እስራኤል ከግብጽ ከወጡ በኋላ በሁለተኛው ዓመት በመጀመሪያው ወር በሚያዝያ



በሲና ምድረ በዳ እግዚአብ ሔር ለሙሴ ነገረው ፤

፪፤ ወይቤሎ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራ ኤል ከመ ይግበሩ ፋሲካ አመ ጊዜሁ፤

በየጊዜው በዓል ያደርጉ ዘንድ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው ፤

፫፤ አመ አሡሩ ወረቡዐ ለሠርቀ ወርኅ ቀዳሚ ወፍና ሠርክ ትገ ብርዎ አመ ጊዜሁ በከመ ሕጉ ወበከመ ትእዛዙ ትገብሮ፣

የመጀመሪያው ወር በባተ በአሥራ አራተኛው ቀን ማታ ጊዜ በሠርክ አድርጉት፣ እንደ ሕጉ እንደ ትእዛዙም አድርገው አለው፤

፬፤ ወነገሮሙ ሙሴ ለደቂቀ እስራ ኤል ከመ ይግበሩ ፋሲካ፣

ሙሴም ለእስራኤል ልጆች ፋሲካን ያከብሩ ዘንድ ነገራ ቸው፤

፭፤ ወአኀዙ ይግበሩ እምዕለተ ዓሡሩ ወረቡዐ ለሠርቀ ወርኅ በገዳም ዘሲና ፤

ሚያዝያ በባተ በአሥራ አራ ተኛው ቀን በሲና ምድረ በዳ በዓል ያደርጉ ጀመሩ፤

በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ከማሁ ገብሩ ደቂቀ እስራኤል፣

እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘ ዘው የእስራኤል ልጆች አደ ረጉ፤

፮፤ ወመጽኡ ሰብእ እለ በሙ ርኩስ ውስተ ነፍስቶሙ ወስዕኑ ገቢረ ፋሲካ በይእቲ ዕለት፣

በሰውነታቸው ርኩሰት ያለባቸው ሰዎች መጥተው በዚያች ቀን ፋሲካን ከማድረግ ተከለከሉ፣

ወመጽኡ ቅድሜሆሙ ለሙሴ ወለ አሮን በይእቲ ዕለት፣

እነዚያም ሰዎች በዚያች ቀን ወደ ሙሴና ወደ አሮን መጡ፤

፯፤ ወይቤልዎሙ ውእቶሙ ዕደው ንሕነሰ ሰብእ ንሕነ እለ ብነ ርኩስ ውስተ ነፍስትነ ወኢንትኃደግ እምአብኦ ቍርባኑ ለእግዚአብሔር እማዕከሎሙ ለደቂቀ እስራኤል በበዘመኑ፣

ኢንትፈለጥ ሲል ነው፣ በሰ ውነታችን ርኩሰት ያለብን እኛም እንደናንተ ሰዎች ነንና ከእስራኤል ልጆች ተለይተን የእግዚአብሔርን መሥዋዕት ከማቅረብ በየዘመኑ እንከል ከል? (እንለይ)? አሉ፣ አሁን እነሱ በየዘመኑ የሚኖሩ ሁነው አይደለም፣ በኋላ ዘመን ለሚነሡት ሁሉ ሥርዓት መጠየቃቸው ነው እንጂ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፤ ወበኍልቍ መዋዕል ዘይከድን ደመና ዲበ ደብተራ የኃድሩ ደቂቀ እስራኤል በቃለ እግዚአብሔር ወበትእዛዘ እግዚአብሔር ይግዕዙ፣

ደመና ደብተራ ኦሪትን በሚጋርድበት ቀን ቍጥር የእሥራኤል ልጆች ድንኳናቸውን ተክለው ይሠፍሩ ነበር፣ በእግዚአብሔር ትእዛዝም ይጓዙ ነበር፤

፳፩፤ ወሶበ ይነብር ደመና እምሠርክ እስከ ነግህ ወአመ ይሴስል ደመና በጽባሕ ይግዕዙ መዓልተ፣ ወእመኒ ሌሊተ እምከመ ሰሰለ ደመና ይግዕዙ ሌሊተ በተእዛዘ እግዚአብሔር ይትዐየኑ፣

ደመናው ማታ ጀምሮ እስኪነጋ ድረስ በድንኳኑ ላይ በሰፈረ ጊዜ ይሰፍሩ ነበር፣ ጧት ደመናው በተወገደ ጊዜ በመዓልትም በሌሊትም ቢሆን ይጓዙ ነበር፣ በእግዚአብሔር ትእዛዝም ይሰፍሩ ነበር፤

፳፪፤ ወለእመኒ አብዝኃ ደመና ነቢረ እንዘ ይጼልላ እስከ መዋዕለ ወርኀ ይትዐየኑ ደቂቀ እስራኤል ወኢይግዕዙ፣

ደመናው ወር እስኪመላ ድረስ ድብተራ ኦሪትን ጋርዶ ቢሰነብት የእስራኤል ልጆች አይጓዙም ሰፍረው ይሰነብቱ ነበር፤

፳፫፤ እስመ በትእዛዘ እግዚአብሔር ይግዕዙ ወሕገጊሁ ለእግዚአብሔር የዓቅቡ በትእዛዘ እግዚአብሔር ወበእደዊሁ ለሙሴ፣

በእግዚአብሔር ትእዛዝ ይጓዙ ነበርና፣ በእግዚአብሔር ትእዛዝና በሙሴ ቃል የእግዚአብሔርን ሕግ ይጠብቁ ነበር ማለት ደመናው ደብተራ ኦሪትን በሚሸፍንበት ጊዜ ይሰፍራሉ፣ በሚነሣበት ጊዜም ይጓዙ ነበር።

## ምዕራፍ ፲

### ጉባኤ

፩፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤

፪፤ ግበር ለከ ክልኤተ መጣቅዕተ ዘብሩር ወዘዝብጦ ትገብሮሙ፣

ሁለት የብር ነጋሪቶች ሥራ ተመትተው የተሠሩም አድርጋቸው፤

ወይከውኑከ በዘቦቱ ትጼውዕ ተዓይነ ለኃዲር ወበዘቦቱ ታነሥእ ተዐይነ ለሐዊር፣





እሊህም ነጋሪቶች ሠራዊቱን ለማሥፈር የምትጠራበት በጉዞም ጊዜ ሠራዊቱን የምታስነሣበት ይሆኑሃል፤

፫፤ ወትጠቅዕ በሙ ወይትጋብኡ ኵሉ ተዐይን ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል

«ኪያሆሙ ሲል ነው»፣ እሊህንም ምታ፣ በመታሐቸው ጊዜ የእስራኤል ሠራዊት ሁሉ ወደ ደብተራ ኦሪት ይሰብሰቡ፤

፬፤ ወለእመሰ ለአሐዱ ጠቃዕክሙ ይመጽኡ ኀቤከ ኵሎሙ መላእክት ዘምስፍና እስራኤል፣

በአንድ ስልት ነጋሪቱን ብትመታ የእስራኤል አለቆች ሁሉ ወደ አንተ ይሰበሰባሉ፤

፭፤ ወትጠቅዑ በትእምርታቲሆሙ ወይግዕዙ ተዓይኒሆሙ ለእለ ተዓየኑ መንገለ ሠርቅ፣

በየስልታቸው ምቷቸው፣ በምሥራቅ የሰፈሩት ይሁዳ ይሳኮር ዛብሎን ይጓዛሉ፤

፮፤ ወትጠቅዑ በትእምርታቲሆሙ ዳግመ ወይግዕዙ ተዓይኒሆሙ ለእለ ተዓየኑ መንገለ አዜብ፣

በሁለተኛውም ስልታቸው በመታችኋቸው ጊዜ በደቡብ የሰፈሩት ሮቤል ስምዖን ጋድ ይጓዛሉ፤

፯፤ ወትጠቅዑ በትእምርታቲሆሙ ሣልስተ ወይግዕዙ ተዓይኒሆሙ ለእለ ተዓየኑ መንገለ ባሕር፣

ሦስተኛም በስልት በመታችኋቸው ጊዜ በምዕራብ በኩል የሰፈሩ ብንያም ምናሴ ኤፍሬም ይጓዛሉ፤

ወትጠቅዑ በትእምርታቲሆሙ ራብዒተ ወይግዕዙ ተዓይኒሆሙ ለእለ ተዓየኑ መንገለ መስዕ ፣

በአራተኛው በስልት በመታችኋቸው ጊዜ በሰሜን የሰፈሩ አሴር ዳን ንፍታሌም ይጓዛሉ፤

ሶበ ለግዒዝ በትእምርት ትጠቅዑ፣

በምትጓዙበትም ጊዜ በስልት ምቷቸው፤

፰፤ ወሶበ ለአስተጋብኦ ተዓይን ትጠቅዑ ዘእንበለ ትእምርት፣

ሠራዊቱን ለመሰብሰብ በሆነ ጊዜ ያለ ስልት ምቷቸው፣ ይኸውም ምሳሌ ነው፣ ሁለቱ ነጋሪት የሁለቱ ዕለታት፣ የበረከተ ሚካኤል፣ (ጥቅምት ፲፪ ቀን) የርክብ አምሳል፣ በመሰብሰብ ጊዜ በአንድ ስልት ምቱት አለ፣ ሥርዓት የፈረሰ

www.ethiopianorthodox.org

ጠል ሌሊት በሰፈሩ በወረደ ጊዜ መናውም አብሮ ይወርድ ነበር ፡፡

፲፡ ወሰምዐ ሙሴ እንዘ ይበክዩ በበሕዘቢሆሙ አሐዱ አሐዱ በኀበ ኆኅተ ደብተራሁ ፤

ሙሴም አንዱም አንዱም በየ ወገናቸው በየድንኳኑ ደጃፍ ሲያለቅሱ ሰማ ፡፡

ወተምዓ መዓተ እግዚአብሔር ጥቀ ወበቅድመ ሙሴኒ እኩየ ኮነ፡፡

እግዚአብሔር ፈጽሞ ተቆጣ፤ በሙሴም ዘንድ ይህ ነገር ክፉ ሆነ ፡፡

፲፩፡ ወይቤሎ ሙሴ ለእግዚአብሔር ለምንት አሕሰምከ ላዕለ ቍልዔከ ወለምንት ኢረከብኩ ሞገሰ በቅድሜከ ከመ ታግብእ ላዕሌየ መቅሠፍቶሙ ለእሉ ሕዝብ፤

ሙሴም እግዚአብሔርን በኔ በወዳጅህ ላይ ለምን ክፉ ነገርን አደረግህ? የነዚህን ወገኖች ጥፋት ወደኔ ትመልስ ዘንድ በፊትህ ባለሟልነትን ለምን አላገኘሁም አለው፡፡

፲፪፡ ቦኑ አነ ፀነስክዎሙ ለእሉ ሕዝብ ወቦኑ አነ ወለድክዎሙ ከመ ትቤለኒ ንሥኦሙ ውስተ ሕፅንከ ከመ ይነሥእዎ ለዘየ ሐፅንዎ ውስተ ምድር ዘመሐልከ ለአበዊሆሙ ፤

ተንከባከባቸው የምትለኝ በውኑ የፀነስኳቸው እኔ ነኝ፤ የሚያሳድጉትንም ልጅ ከምድር አንስተው እንዲንከባከቡት ለአባቶቻቸው የማልክላቸው እስራኤልን ተንከባከባቸው ትለኝ ዘንድ በውኑ የወለድ ኋቸው እኔ ነኝ ?

፲፫፡ እምአይቴ ሊተ ሥጋ ዘእሁብ ለእሉ ሕዝብ እስመ ናሁ ይበክዩ ላዕሌየ ወይብሉኒ ሀበነ ሥጋ ከመ ንብላዕ፤

እንበላ ዘንድ ሥጋ ስጠን እያሉ እነሆ በኔ ያለቅሳሉና ለነዚህ ሁሉ የምሰጠው ሥጋ ከወዴት አገኛለሁ ?

፲፬፡ ወኢይክል አነ ባሕቲትየ ዓቂቦቶሙ ለእሉ ሕዝብ እስመ ይከብዱኒ ፤

ይበዙብኛልና እሊህን ወገኖች እኔ ብቻዬን መጠበቅ አይቻለኝም፡፡

፲፭፡ ወለእመሰ ከመዝ ትሬስየኒ ቀቲለ ቅትለኒ ለእመ ረከብኩ ምሕረተ በቅድሜከ ከመ ኢይርአያ ለእኪትየ፤

እንዲህ ካደረግኸኝስ በፊትህ ይቅርታን አግኝቼ እንደሆነ



መከራዬን እንዳላያት እኔን ግደለኝ ፡፡

፲፮፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ አስተጋብእ ሊተ ፸ዓ ብእሴ እምአዕሩጊሆሙ ለደቂቀ እስራኤል እለ ተአምር ለሊከ ከመ እሙንቱ ሊቃናቲሆሙ ለሕዝብ ወጸሐፍ ቶሙኒ፤

እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፤ ከእስራኤል ልጆች ሽማግሎች፤ በዕውቀት የሕዝቡ አለቆች እንደሆኑ አንተ የምታውቃቸውን ሰባ ሰዎች ሹማምቱንም ሰብስበህ፡፡

ወታበውኦሙ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ፤

ልዩ ወደ ሆነች ድንኳን አግባቸው አለው፤

ወይቁሙ ህየ ምስሌከ ፤

ከአንተም ጋራ በዚያ ይቁሙ፡፡

፲፯፡ ወእወርድ ወእትናገር በህየ ምስሌከ ወእነሥእ እመንፈስ ዘላዕሌከ ወአነብር ዲቤሆሙ ፤

መጥቼ በደብተራ ኦሪት ካንተ ጋር እነጋገራለሁ፤ ባንተ አድሮ ካለው መንፈስ ትንቢት ነሥቼ በነሱም አሳድራለሁ ፡፡ ‹ሐተታ› የአንተን ነሥቼ ለሌላ እሰጣለሁ ማለቱ አይደለም፤ ረድኤቱን ባንተ እንዳሳደርሁ በነሱም አሳድርባቸዋለሁ ሲል ነው ፡፡

ወይፀውሩ ምስሌከ ክበዶሙ ለእሉ ሕዝብ ወኢትሥራኅ ባሕቲትከ ሎሙ ፤

ስለነሱ ብቻህን እንዳትደክም የነዚህን ወገኖች ብዛታቸውን ‹አስተዳደራቸውን› ካንተ ጋር ይሸከማሉ ማለት እንዳንተ ይሠራሉ ይቀጣሉ ፤

፲፰፡ ወትብሎሙ ለሕዝብኒ ያንጽሑ ርእሶሙ ለጌሠም ፤

ሕዝቡን ለነገ ሰውነታቸውን ያነጹ ዘንድ ንጹሐን ሁኑ በላቸው ፡፡

ወትበልኡ ሥጋ እስመ በከይክሙ ቅድመ እግዚአብሔር እንዘ ትብሉ መኑ ያበልዐነ ሥጋ ፡፡

ሥጋ ማን ያበላናል? ብላችሁ በእግዚአብሔር ፊት አልቅሳችኋልና ሥጋ ትበላላችሁ ፡፡

እስመ ይኄይሰነ ብሔረ ግብጽ ወይሁበክሙ እግዚአብሔር ትብልዑ ሥጋ፤

በግብጽ አገር መኖር ይሻለናል ብላችኋልና ሥጋ ትበሉ ዘንድ እግዚአብሔር ይሰጣችኋል፡፡

፲፱፡ አኮ አሐተ ዕለተ ዘትበልዑ ወአኮ ሰኑየ ወአኮ ሐሙሰ መዋዕለ

www.ethiopianorthodox.org

ወአኮ አሡረ ወአኮ ዕሥራ መዋዕለ፤

የምትበሉትም አንድ ቀን፣ ሁለት ቀን፣ አምስት ቀን፣ ዐሥር ቀን፣ ሃያ ቀን ብቻ አይደለም ፤

፳፤ ባሕቱ እስከ መዋዕለ ወርኅ ትበልዕዎ እስከ ይወፅእ እምውስተ አእናፊክሙ ወይከውነክሙ ሕምዘ፣

ከአፍንጫችሁ መግል ትል እስኪወጣ ድረስ፣ መርዝም እስኪሆንባችሁ ድረስ ማለት መርዝ እንዲጎዳ እስኪጎዳችሁ ድረስ እስከ ወር ትበሉታላችሁ እንጂ ፤

እስመ ክሕድክምዎ ለእግዚአብሔር ዘሀለወ ውስቴትክሙ ወበከይክሙ በቅድሜሁ እንዘ ትብሉ ለምንት ለነ አውፃእከነ እምብሔረ ግብጽ ፤

በኛንተ አድሮ ያለ እግዚአብሔርን ክዳችሁታልና ከግብጽ አገር እኛን ለምን አወጣኸን? እያላችሁ በፊቱ አልቅሳችኋልና፤

፳፩፤ ወይቤ ሙሴ ስሳ እልፍ አጋር ሕዝብ እለ ውስቴቶሙ ሀለውኩ ወአንተ ትቤለኒ እሁቦሙ ሥጋ ወይበልዑ መዋዕለ ወርኀ ፣

ሙሴም እንዲህ አለ፣ እኔ የተሾምሁባቸው ወገኖች ስሳ እልፍ አርበኞች ናቸው፣

አንተ ግን ሥጋ እሰጣቸዋለሁ፣ እስከ ወር ድረስ ሥጋ ይበላሉ አልከኝ ‹ትች›፤

፳፪፤ ቦኑ ኵሉ አባግዕ ወአልሕምት ይጠብሑ ሎሙ አው ኵሉ ዓሣተ ባሕር ይትጋብኡ ሎሙ ከመ ይእክሎሙ ፣

በውኑ ላሞችና በጎች ሁሉ ይታረዱላቸዋልን፤ ወይስ ይበቃቸው ዘንድ የባሕር ዓሣዎች ሁሉ ይሰበሰቡላቸዋልን አለ፤

፳፫፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ቦኑ ኢትክል እዴየ ናሁ ትሬኢ እመ ትረክቦ ለቃልየ ወእመ አልቦ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን በውኑ ሥልጣኔ ይህን ማድረግ አትችልምን፣ ነገሬ ይደረግም እንደሆነ አይደረግምም እንደሆነ እነሆ ታያለህ አለው ፤

፳፬፤ ወወፅአ ሙሴ ወነገሮሙ ለሕዝብ ቃለ እግዚአብሔር ወአስተጋብአ ፸ዓ ብእሴ እምአዕሩጊሆሙ ለሕዝብ ወአቀሞሙ ዐውደ ደብተራ ፣

ሙሴም ከደብተራ ኦሪት ወጥቶ የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝቡ ነገራቸው፣ ከሕዝቡም ሽማግሎች ሰባ ሰው መርጦ በደብተራ ኦሪት ዙሪያ አቆማ



ቸው፣ ‹ሐተታ› ከአሥራ ሁለቱ ነገድ አምስት አምስት ሰው ቢመርጥ አሥር ጎደለ በት፣ ስድስት ስድስት ቢመርጥ ሁለት ተረፉበት፣ ሁለቱን ትቶ ሰባውን ሾማቸዋል ፤

፳፭፤ ወወረደ እግዚአብሔር በደመና ወተናገሮ ወነሥአ እመንፈስ ዘላዕሌሁ ወሤመ ላዕለ ሰብዓ ብእሲ ሊቃውንት ፣

እግዚአብሔርም በደመና ወርዶ ሙሴን ተናገረው ፤ በርሱ አድሮ ካለ መንፈሰ ትንቢት ነሥቶ በሰባው አለቆች አሳደ ረባቸው ፤

ወእምዝ አዕረፈ ላዕሌሆሙ መንፈስ ተነብዮ ወተነበዩ ፣

ከዚህ በኋላ ትንቢት የሚያናግር መንፈስ አድሮባቸው ትንቢት ይናገሩ ጀመር ፤

፳፮፤ ወኢተወሰኩ እንከ ወተርፉ ክልኤቱ ዕደው ውስተ ትዕይንት ፣

ሁለቱ ሰዎች ግን በሰፈር ቀሩ እንጂ ከሰባው ሊቃናት አልተጨመሩም ፤

ስሙ ለአሐዱ ኤልዳድ ወለካልኡ ሙዳድ፤

ያንዱ ስሙ ኤልዳድ ነው፣ የሁለተኛውም ስሙ ሙዳድ ነው ፤

ወአዕረፈ ላዕሌሆሙኒ መንፈስ ትንቢት ወተነበዩ ፤

በነሱም ትንቢትን የሚያናግር መንፈስ አደረባቸው፣ ያልታወቀ ትንቢት ተናገሩ ፤ አንድም ነገ ለእስራኤል ሥጋ ይዘንማል ብለው ተናገሩ፤ አንድም ሙሴ እኛን ከሹመት እንደለየን ምድረ ርስት አይገባም፣ በናባው ምድረ በዳ ይቀራል ብለው ተናገሩ፣ ተመርጠዋልና መንፈስ ትንቢት አደረባቸው፣ ከቁጥር ተርፈዋልና ከሹመት ቀሩ ፤

ወእሙንቱኒ ተጽሕፉ ምስሌሆሙ ወኢመጽኡ ምስሌሆሙ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ወተነበዩ በውስተ ትእይንት ፣

እነሱም ከነሱ ጋር ተቈጠሩ፣ ነገር ግን አልተሾሙምና ወደ ደብተራ ኦሪት ከሰባው ሊቃናት ጋር አልመጡም፤ በከተማው ሁነው ትንቢት ተናገሩ እንጂ፤

፳፯፤ ወሮፀ አሐዱ ወሬዛ ወዜነዎ ለሙሴ ወይቤሎ ኤልዳድ ወሙዳድ ተነበዩ በውስተ ትዕይንት፣

www.ethiopianorthodox.org

ያልታወቀ ሰው፤ አንድም ኢያሱ ነው፣ ሩጦ ሂዶ ኤልዳድና ሙዳድ በሰፈሩ ትንቢት ተናገሩ ብሎ ለሙሴ ነገረው፣ ሙሴ ያላዘዘው ትንቢት የማ ይናገር መስሎት ነው ፤

፳፰፤ ወይቤሎ ኢያሱ ዘነዌ ዘይቀውም ቅድሜሁ ለሙሴ ዘውእቱ ኅሩዩ እግዚእየ ክልኦሙ፣

በፊቱ የሚቆም ማለት ባለ ሟሉ የሆነ የነዌ ልጅ ኢያሱ ሙሴን ጌታዬ ትንቢት እንዳ ይናገሩ ከልክላቸው አለው ፤

፳፱፤ ወይቤሎ ሙሴ አንተኑ ትቀንዕ ሊተ ወመኑ እምወሀበ ከመ ይትነበዩ ኵሉ ሕዝብ ለእግዚ አብሔር ሶበ ወሀበ እግዚአብሔር መንፈሶ ላዕሌሆሙ፣

ሙሴም እንዲህ አለው፣ አንተ ለኔ ትቀናልኛለህን ሕዝቡ ሁሉ ለእግዚአብሔር ትንቢት ይናገሩ ዘንድ ትን ቢት የሚያናግር መንፈስ ረድ ኤት ማን ባሳደረባቸው ነበር? እግዚአብሔር ትንቢት የሚያ ናግር መንፈስ ረድኤት ቢያሳ ድርባቸው እኔ እከለክላለ ሁን አለው ፤

፴፤ ወገብኡ ውስተ ትዕይንት ውእቱ ወአዕሩጊሆሙ ለእስራኤል፣

እሱም የእስራኤል ሽማግሎ ችም ወደ ሰፈር ተመለሱ ፤

፴፩፤ ወወፅአ መንፈስ እምኀበ እግዚአብሔር ወአዕደወ ፍርፍርተ እምባሕር ፤

ነፋስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ታዝዞ ወጥቶ ታላቅ ታናሽ ሥጋ፤ አንድም ዓሣ፣ የባ ሕር ዶሮ ፤ ድርጭት ይህን ሁሉ ከባሕር አስገኘላቸው፤ የባሕር ዶሮ ድርጭት ሲያዩት ከሻዋ ሲያርዱት ስብ ነው፤

ወወረደ ውስተ ትዕይንት እስከ ምሕዋረ ዕለት እምነ ዐውደ ትዕይንት እምለፌ ወእምለፌ ወተ ወጥሀ ካዕበተ እመት መልዕልተ ምድር ፤

እስከ አንድ ቀን ጎዳና ድረስ በከተማው ዙሪያ በቀኝም በግ ራም ወርዶ በምድር ላይ ሁለት ክንድ ተከመረ፤ አን ድም እንዳይጸየፉ ከመሬት ሁለት ክንድ ርቆ ተከምሯል፣ አፈር እንዳይነካው ነው ፤

፴፪፤ ወተንሥኡ ሕዝብ ኵሎ መዓልተ ወኵሎ ሌሊተ በሳኒታ ወአለዱ ሎሙ ፍርፍርተ ፤

ሕዝቡም በማግስቱ ተነሥ ተው መላ ቀኑንና መላ ሌሊ



ቱን ታላቅ ታናሹን ዓሣውን የባህር ዶሮውን ሰበሰቡ ፤

ወዘአውሀደ አልዶ አሰደ ዐሠርተ በመሥፈርተ ቆሮስ ወሰጥሁ ሎሙ ወአይበሱ ውስተ ዐውደ ተዓይኒሆሙ ፤

አሳነሼ ለቀምሁ ያለ ቆሮስ በሚባል መሥፈሪያ ዐሥር ማድጋ ሰበሰበ ፤ በሰፈራቸው ዙሪያ አስጥተው አደረቁ፤ ቆሮስ አሥራ ሁለት ጫን የሚይዝ ነው ፤

፴፫፤ ወእንዘ ሀለወ ሥጋ ውስተ ጥረሲሆሙ ዘእንበለ ያኅልቅዎ ተምዓ እግዚአብሔር ላዕለ ሕዝቡ ወቀተሎሙ በዐቢይ መቅሠፍት ጥቀ ፤

ሥጋውን በልተው ሳይጨ ርሱ ገና ባፋቸው ሳለ እግዚአ ብሔር በወገኖቹ ተቆጥቶ እጅግ ጽኑ በሆነ መቅሠፍት አጠፋቸው ፤

፴፬፤ ወተሰምየ ስሙ ለውእቱ መካን መቃብረ ፍትወት እስመ ቀበርዎሙ ለሕዝብ እለ ፈተዉ፣

ሥጋ ማን በሰጠን? ብለው የተመኙትን ሰዎች በዚያ ቀብ ረዋቸዋልና የዚያ ቦታ ስሙ ሥጋ ተመኝተው የተቀበሩበት ተባለ ፤

፴፭፤ ወግእዙ ሕዝብ እመቃብረ ፍትወት ውስተ አሴሮት ወነበሩ በአሴሮት ፤

የቀሩት ሕዝቡም ከዚያ ቦታ ተነሥተው ወደ አሴሮት ተጉ ዘው በአሴሮት ተቀመጡ ።

## ምዕራፍ ፲፪

፩፤ ወሐመይዎ ለሙሴ ማርያም ወአሮን በበይነ ብእሲት ኢትዮ ጵያዊት እንተ ነሥአ እስመ ብእሲተ ኢትዮጵያዊተ ነሥአ ሙሴ፣

ሙሴ የኢትዮጵያን (የምድ ያምን) ሴት አግብቶ ነበርና ስለ አገባት ስለ ምድያም ሴት አሮንና ማርያም ሙሴን አሙት፣ ‹ሐተታ› እኛን ከአረ ማውያን አትጋቡ ይለናል፤ እሱ ግን ያገባል፣ እኛን ከሴት አድራችሁ ወደ ደብተራ ኦሪት አትግቡ ይለናል፣ እርሱ ግን ይገባል ብለው አሙት ፤

፪፤ ወይቤሉ ቦኑ ለሙሴ ተናገሮ እግዚአብሔር አኮኑ ለነሂ ተናገረነ ወሰምዐ እግዚአብሔር፣

በውኑ እግዚአብሔር ሙሴን ብቻ ተናገረውን እኛንስ የተ

www.ethiopianorthodox.org

ናገረን አይደለምን አሉ፤ እግዚአብሔርም ይህን ነገር ሰማ፤

፫፤ ወሙሴሰ ብእሲ የዋህ ውእቱ ጥቀ እምኵሉ ዕጓለ እመሕያው ዘሀሎ ውስተ ምድር ፤

ሙሴ ግን በዚህ ዓለም ካለው ሰው ሁሉ ይልቅ ፈጽሞ ደግ ሰው ነበር ፤ ለአሮንና ለእኅቱ ማርያም ጸለየላቸው የሚል ነውና የዋህ ውእቱ ጥቀ አለው ፤

፬፤ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ወለማርያም በጊዜሃ ንዑ አንትሙ ሠለስቲክሙ ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ወወፅኡ ሠለስ ቲሆሙ ፤

እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን፣ ማርያምን፣ ሦስታችሁ ፈጥናችሁ ወደ ደብተራ ኦሪት ኑ አላቸው፣ ሦስቱም ወጥተው ሄዱ ፤

፭፤ ወወረደ እግዚአብሔር በዓምደ ደመና ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወጸውዖሙ ለአሮን ወለማርያም ወሖሩ ክልኤሆሙ ፤

እግዚአብሔርም በዓምደ ብርሃን ወደ ደብተራ ኦሪት ወርዶ አሮንንና ማርያምን ጠራቸው፣ ሁለቱም ሄዱ ፤

፮፤ ወይቤሎሙ ስምዑ ቃልየ ለእመቦ ዘኮነ ነቢየ እምኔክሙ ለእግዚአብሔር በራእይ አስተርአዮ ወበሕልም እትናገሮ ፤

ነገሬን ስሙ ከናንተ ለእግዚአብሔር ነቢይ የሆነ ሰው ቢኖር በራእይ እገለጽለታለሁ ፤ በሕልም እነጋገረዋለሁ አላቸው ፤

፯፤ ወአኮ ከመ ቍልዔየ ሙሴ ምእመን ውእቱ ላዕለ ኵሉ ቤትየ ፤

ነገር ግን የምናገረው እንደ ታመነ ወዳጄ እንደ ሙሴ አይደለም፣ እሱ በወገኖቼ በእስራኤል ሁሉ የታመነ ነውና ፤

፰፤ አፈ በአፍ እትናገሮ ገሃደ ወአኮ በሥውር ወርእየ ስብሐተ እግዚአብሔር ፤

ተገልጬ ቃል በቃል እነጋገረዋለሁ እንጂ በራእይ በሕልም የምነጋገረው አይደለም፣ የእግዚአብሔርነቴን ጌትነትም ያየ እሱ ነው ፤

ወለምንት ኢፈራህክሙ ሐምዮቶ ለቍልዔየ ሙሴ ፤

ወዳጄ ሙሴን ማማትን ለምን አልፈራችሁም ?



፱፤ ወኮነ ላዕሌሆሙ መንሱተ መዓቱ ለእግዚአብሔር ወሖሩ ፤

እግዚአብሔር ፈርዶ የመጣው መከራ በነሱ ላይ ተደረገ፣ አሮንና ማርያም ሄዱ ፤

፲፤ ወሰሰለ ደመና እምደብተራ ዘመርጡል ወአኀዛ ለምጽ ለማርያም ወባዕደወት ኵለንታሃ ከመ በረድ፣

ደመናውም ከደብተራ ኦሪት ተወገደ ‹ራቀ›፣ ማርያምን ወዲያው ለምጽ ያዛት ፤ ሁለን ተናዋም እንደ በረዶ ነጭ ሆነች ፤

ወተይመይጠ አሮን ኀበ ማርያም ወናሁ አኀዛ ለምጽ ፤

አሮንም ወደማርያም ተመልሶ ቢያይ ለምጽ ይዟት አገኛት ፤

፲፩ ወይቤሎ አሮን ለሙሴ ብቍዓኒ እግዚእየ ኢትረስያ ለነ ኃጢአተ እስመ ኢያእመርነ ከመ አበስነ ፤

አሮንም ሙሴን እንዲህ አለው፣ ጌታዬ በጄ በለኝ፣ እንደበደልን አላወቅንምና በኛ ዕዳ አታደርግብን አለው፤

፲፪ ወኢንኩን ትዕሪራነ በሞት ከመ ዛዕዛዕ ዘይወፅእ እማኅፀነ እሙ ፤

ከናቱ ማኅፀን እንደወጣ ጭንጋፍ በሞት የተለቀምን አንሁን፣ ጭንጋፍ ከማኅፀን ወጥቶ ይሞታልና ፤ አንድም በሞት የተለቀምን አንሁን፣ ‹ወከመ ዛዕዛእ ኢንኩን› ከናቱ ማኅፀን የወጣ ጭንጋፍ ነጭ እንዲሆን እንደዚያ አንሁን ፤

ወተበልዓ መንፈቀ ሥጋሃ ፤

ወንድሟን አምታለችና የማርያም የሰውነቷ እኩሌታ በለምጽ ነደደ ፤

፲፫፤ ወጸርሐ ሙሴ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤ እግዚኦ ብቍዓኒ አሕይዋ ፤

ሙሴም አቤቱ በጄ በለኝና ማርያምን ከለምጽ አድናት ብሎ ወደ እግዚአብሔር አመለከተ ፤

፲፬፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ሶበ አቡሃ ተፍዓ ትፍዓቶ ውስተ ገጻ እምኢኃፍረትኑ ሰቡዓ መዋዕለ ለትትገኃሥ አፍአ እምትዕይንት ሰቡዓ መዋዕለ ወእምዝ ትበውእ ውስተ ትዕይንት ፤

አባቷ በፊቷ እንትፍ ቢልባትም አይቶብኝ ብላ ሰባት ቀን ባላፈረችም ነበርን ፤ አሁንም ከከተማው ሰባት ቀን ወደ ውጭ ትውጣ፣ ከዚያ

www.ethiopianorthodox.org

በኋላ ወደ ከተማው ትግባ አለው ፤

፲፭፤ ወተግኅሠት ማርያም አፍአ እምትዕይንት ሰቡዓ መዋዕለ ወኢ ግዕዙ ሕዝብ እስከ ነጽሐት ማርያም ፤

ማርያምም ከከተማው ወጥታ ሰባት ቀን ተቀመጠች፤ ማር ያም ከለምጿ እስክትነጻ ድረ ስም ሕዝቡ አልተጓዙም፤ አሮን ሊቀ ካህናት ነውና ውስጥ ውስጡን በልቶት አለተገለጸበትም፤ አንድም በን ስሐ ቀርቶለታል ፤

፲፮፤ ወእምድኅረ ዝንቱ ግዕዙ ሕዝብ እምአሴሮት ውስተ ገዳም ዘፋራን ፤

ከዚህ በኋላ ሕዝቡ ከአሴሮት ወደፋራን ምድረ በዳ ተጓዙ።

## ምዕራፍ ፲፫

፩፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እን ዲህ ብሎ ነገረው ፤

፪፤ ፈኑ ዕደወ ሰብአ ዐይን እለ ይሬእይዋ ለምድረ ከነአን ዘአነ እሁቦሙ ለደቂቀ እስራኤል ከመ ይኩንንዋ ፤

ይገዟት ዘንድ ለእስራኤል ልጆች እኔ የምሰጣቸው የከነዓንን ምድር የሚያይዋት ጉበኞች ሰዎችን ላክ አለው ፤

አሐዱ አሐዱ ብእሲ እምነገዶሙ ወእምሕዘቢሆሙ ዘዘአብያተ አበ ዊሆሙ ትፌኑ ኵሎ ዓበይቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ፤

ከየነገዳቸው ከየአባቶቻቸው ወገን ከእስራኤል አንዳንድ ሰው ታላላቆችን ‹አለቆችን› ላክ አለው ፤

፫፤ ወፈነዎሙ ሙሴ እምገዳም ዘፋራን በቃለ እግዚአብሔር ፤

ሙሴም በእግዚአብሔር ትእ ዛዝ ከፋራን ምድረ በዳ ላካቸው ፤

ወእሉ ኵሎሙ ዕደው ዐበይቶሙ ለደቂቀ እስራኤል እሙንቱ ፤

እነዚህም ሁሉ ሰዎች የእስራ ኤል ልጆች አለቆች ናቸው ፤

፬፤ ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆሙ ዘእምነገደ ሮቤል ስሙ ወልደ ዝኩር ፤

ስማቸውም ይህ ነው፤ ከሮቤል ነገድ የተላከው ስሙ ወልደ ዝኩር ነው፤ ጥቅል ስም ነው፤ አንድም ሳሙ ይላል፤



ከሮቤል ነገድ የተላከው የዝ ኩር ልጅ ሳሙ ነው ፤

፭፤ ወዘእምነገደ ስምዖን ሰፈጥ ወልደ ሱሪ፤

ከስምዖን ነገድ የተላከው የሱሪ ልጅ ሰፈጥ ነው ፤

፮፤ ወዘእምነገደ ይሁዳ ካሌብ ወልደ ዮፎኒ ፤

ከይሁዳ ነገድ የተላከው የዮፎኒ ልጅ ካሌብ ነው ፤

፯፤ ወዘእምነገደ ይሳኮር ኤጋል ወልደ ዮሴፍ ፤

ከይሳኮር ነገድ የተላከው የዮሴፍ ልጅ ኤጋል ነው ፤

፰፤ ወዘእምነገደ ኤፍሬም አውሴ ወልደ ነዌ፤

ከኤፍሬም ነገድ የተላከው የነዌ ልጅ አውሴ ነው ፤

፱፤ ወዘእምነገደ ብንያም ፈልጢ ወልደ ራፋው ፤

ከብንያም ወገን የተላከው የራፋው ልጅ ፈልጢ ነው ፤

፲፤ ወዘእምነገደ ዛብሎን ጉድዬል ወልደ ሳዲ ፤

ከዛብሎን ነገድ የተላከው የሳዲ ልጅ ጉድዬል ነው ፤

፲፩፤ ወዘእምነገደ ዮሴፍ ዘእምነገደ ደቂቀ ምናሴ ጋዲ ወልደ ሱሲ ፤

ከዮሴፍ ነገድ የተላከው፤ ከም ናሴ ልጆች ወገን የሚሆን የሱሲ ልጅ ጋዲ ነው ፤

፲፪፤ ወዘእምነገደ ዳን አሚሄል ወልደ ገማሊ ፤

ከዳን ነገድ የተላከው የገማሊ ልጅ አሚሄል ነው ፤

፲፫፤ ወዘእምነገደ አሴር ሳቱር ወልደ ሚካኤል ፤

ከአሴር ነገድ የተላከው የሚካ ኤል ልጅ ሳቱር ነው ፤

፲፬፤ ወዘእምነገደ ንፍታሌም ናቢ ወልደ ያቢ ፤

ከንፍታሌም ነገድ የተላከው የያቢ ልጅ ናቤ ነው ፤

፲፭፤ ወዘእምነገደ ጋድ ጉድያል ወልደ ማኪ ፤

ከጋድ ነገድ የተላከው የማኪ ልጅ ጉድያል ነው ፤

### ጉባኤ

፲፮፤ ዝንቱ ውእቱ አስማቲሆሙ ለዕደው እለ ፈነወ ሙሴ ከመ ይርአይዋ ለይእቲ ምድር ፤

ምድረ ርስትን ያዩ ዘንድ ሙሴ የላካቸው ሰዎች ስማ ቸው ይህ ነው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፮፥ ወሐዊሮሙ በጽሑ ኀበ ሙሴ ወአሮን ወኀበ ኵሉ ተዓ ይኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ውስተ ገዳም ዘፋራን ዘቃዴስ፤

ሄደውም ከአሮንና ከሙሴ ከእስራኤልም ልጆች ሠራ ዊት ዘንድ የቃዴስ ክፍል ወደሆነች ወደ ፋራን ምድረ በዳ ደረሱ፤

ወነገርዎሙ ዜናሆሙ ለኵሉ ተዓ ይኒሆሙ ወአርአይዎሙ ፍሬሃ ለይእቲ ምድር፤

የሰብአ ከነዓንን የሠራዊ ቶቻቸውን ወሬያቸውን ነገ ሯቸው፤ የዚያችንም አገር ፍሬዋን አሳዩአቸው፤

፳፯፥ ወነገርዎሙ ወይቤሉ በጻ ሕነ ውስተ ይእቲ ምድር ኀበ ፈነውከነ ምድር እንተ ትውኅዝ ሀሊበ ወመዓረ ወናሁ ፍሬሃ፤

ወተትና ማር ወደሚፈስባት ማለት፤ ተድላ ደስታ ወዳለ ባት ወደ ላክኸን ወደ ዚያች ምድር ደረስን፤ እነሆ ፍሬዋም ይህ ነው ብለው ነገሯቸው፤

፳፰፥ ወሕዝብኒ እለ ይነብሩ ውስ ቴታ ለይእቲ ምድር ጽኑዓን ወአ ህጉሪሙኒ ጽኑዓት ጥቀ ወዓ በይት ወቦሙ ቅጽር ወትውል ዶሂ ለኤናቅ ርኢነ በህየ፤

በዚያች አገር የሚኖሩ ወገኖ ችም አርበኞች ናቸው፤ አም ባዎቻቸውም እጅግ የጸኑ ታላላቆች ናቸው፤ ቅጥርም አላቸው፤ የኤናቅንም ልጆች በዚያ አየን፤

፳፱፥ ወአማሌቅ ኅዱራን ውስተ ምድር እንተ መንገለ አዜብ፤

አማሌቃውያንም በዚያች አገር በአዜብ በኩል ሰፍ ረው ይኖራሉ፤

ወኬጤዎን ወአሞሬዎን ወኤዌ ዎን ወኢያቡሴዎን ኅዱራን ውስተ አድባሪሃ ወከነዓን ኅዱ ራን መንገለ ባሕር ወመንገለ ፈለገ ዮርዳኖስ፤

የኬጤዎን የአሞሬዎን የኤዌ ዎን የኢያቡሴዎን ልጆች በደጋዋ ሰፍረዋል፤ የከነዓንም ሰዎች በኤርትራና በዮር ዳኖስ በኩል ሰፍረው ይኖ ራሉና እነዚህን አጥፍተን መውረስ አይቻለንም ብለው ነገሯቸው፤

፴፥ ወአዘዘ ካሌብ ያርምሙ ሕዝብ በኀበ ሙሴ ወይቤ አልቦ አላ ዓሪገ ነዓርግ ወንወርስ እስመ ክሂለ ንክሎሙ፤

ካሌብም በሙሴ ዘንድ ያሉ ወገኖች ዝም ይሉ ዘንድ



ዝም በሉ ብሎ ከአዘዘ በኋላ፥ እነሱን ማጥፋት እንችላለ ንና ወጥተን እንወርሳታለን እንጂ አንወርሳትም እንዳ ላችሁት አይደለም አላቸው፤

፴፩፥ ወይቤሉ እልክቱ ዕደው እለ ዓርጉ ምስሌሁ ኢነዓርግ እስመ ኢንክል ዓሪገ ኀበ እሙንቱ ሕዝብ እስመ ይጸንዑ እምኔነ ፈድፋደ፤

ከካሌብ ጋር የሄዱት እነዚያ ሰዎች ግን እነሱ ከኛ ፈጽ መው የሚፀኑ ስለ ሆኑ ወደነ ዚያ ወገኖች መዝመት አን ችልምና አገሪቱን አንወር ስም አሉ፤

፴፪፥ ወግርምተ ረሰይዋ ለይእቲ ምድር እንተ ርእይዋ በኀበ ደቂቀ ፳ኤል

ያዩዋትን ያችን ምድር በእስራኤል ልጆች ዘንድ አስፈርተው ተናገሩ፤

እንዘ ይብሉ ምድር እንተ ሖርነ ከመ ንርአያ ምድር ይእቲ እንተ ተዓቅቦሙ ለእለ ይነብሩ ውስቴታ ወኵሉ ሕዝብ ዘሀለዉ ውስቴታ ዘርኢነ ዕደው እሙንቱ እለ ፈድፋደ ኑኆሙ፤

ልንሰልላት የሄድንባት አገር በውስጧ ያሉትን ሰዎች የምትጠብቃቸው ናት፤ ያየና ቸው በዚ የሚኖሩ ወገኖችም ሁሉ ቁመታቸው እጅግ የረ ዘመ ነው፤ እንደ ዋንዛ እንደ ዝግባ የሆኑ ናቸው፤

፴፫፥ ወርኢነ በህየ እለ ያርብሕ ወከነ በቅድሜሆሙ ከመ አናብጥ እለ ከማሆሙኒ ቅድሜሆሙ፤

በዚያም ቦታ አርበኞችን አየን፤ በፊታቸውም እንደ አንበጣ ሆንን፤ ከማሆሙ ለአ ናብጥ ነው፤ እንደነሱ እን ደሆኑ እንደ ኵብኵባም ሆንነ ማለት የተናቅን ሆንነ፤ አንድም በግብር በልደት እንደነሱ ያሉ አሕዛብ በነሱ ዘንድ እንደ አንበጣ ሆኑ፤ ብዙ ናቸው ብለው አስፈር ተው ተናገሩ።

## ምዕራፍ ፲፬

፩፥ ወኀብሩ ኵሉ ተዓይን ወጸ ርሑ በዐቢይ ቃል ወበከዩ ኵሉ ሕዝብ ኵላ ሌሊተ፤

ሠራዊቱም ሁሉ አንድ ሁነው አሰምተው ጮሁ፤ ሕዝቡም መላ ሌሊቱን አለቀሱ፤

፪፥ ወአንጐርጐሩ ላዕለ ሙሴ ወላ ዕለ አሮን ኵሎሙ ደቂቀ እስራ ኤል፤

www.ethiopianorthodox.org

ጠማው ወይኑም እንደ ሥር ዓቱ ነው፤

ወአሐዱ ሐርጌ እምአጣሊ በእንተ ኃጢአት፤

ከፍየሎችም ኃጢአት ለማስ ተሥረይ አንድ ሙክት ያቅ ርብ (ታቅርብ)፤

፳፭፤ ወያስተሥሪ ካህን በእንተ ኵሉ ተዓይኒሆሙ ለደቂቀ እስ ራኤል ወይትኃደግ ሎሙ እስመ በኢያእምሮ ውእቱ፤

ካህኑም የእስራኤልን ልጆች ሠራዊት ሁሉ ኃጢአት ያስተ ሥርይ፤ ባለማወቅ የተደረገ ነውና ኃጢአታቸውም ይሠ ረያል፤

ወእሙንቱኒ ያመጽኡ ቍርባኖሙ ወመሥዋዕቶሙ ለእግዚአብሔር በእንተ ኃጢአቶሙ ቅድመ እግዚ አብሔር ወበእንተ ኢያእምሮ ቶሙ፤

እነሱም ባለማወቅ ስለሠሩት ኃጢአታቸው ቍርባናቸውን መሥዋዕታቸውን በእግዚአብ ሔር ፊት ማለት በደብተራ ኦሪት ያቅርቡ፤

፳፮፤ ወይትኃደግ ለኵሉ ትዕይ ንቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ወለ ግዩርኒ ዘይመጽእ ኀቤክሙ እስመ ለኵሉ ሕዝብ በኢያእምሮ ኮነ፤

ለሕዝቡ ሁሉ ባለማወቅ የተ ሠራ ኃጢአት ነውና የእስራ ኤል ልጆች ሠራዊት ሁሉ ኃጢአት ወደናንተ የመጣው የመጻተኛውም ኃጢአት በዚህ ይሠረያል፤

፳፯፤ ወለእመሰ አሐዱ ብእሲ አበሰ በኢያእምሮ ያመጽእ አሐተ ጠሊተ እንተ ዓመት በእንተ ኃጢአት፤

አንድ ሰው ባለማወቅ ቢበድል ግን ኃጢአቱን ስለ ማስተ ሥረይ ዓመት የሆናት አን ዲት ፍየል ያምጣ፤

፳፰፤ ወያስተሥሪ ካህን በእንተ ውእቱ ብእሲ እንተ በኢያእምሮ አበሰ ቅድመ እግዚአብሔር ወያስ ተሥሪ ካህን በእንቲአሁ፤

ካህኑም በእግዚአብሔር ፊት ባለማወቅ ስለበደለው ሰው ኃጢአቱን ያስተሥርይለት፤

፳፱፤ ዘእምፍጥረቱሂ ውስተ ደቂቀ እስራኤል ወለግዩራንሂ ዘሀለዉ ውስቴትክሙ አሐዱ ውእቱ ሕጉ ሎሙ ወለክሙ እምከመ በኢያ እምሮ ገብሩ፤

ትውልዱ ከእስራኤል ልጆች ወገን የሆነ ነውና በመ ካከላችሁ የሚኖሩ የመጻተኞ ችንም ኃጢአት ካህኑ ያስተ ሥርይ፤ ባለማወቅ ከሠሩ



የነሱም የናንተም ሥርዓቱ አንድ ነውና፤

፴፤ ወብእሲ እንተ ገብረ በእዴሁ ትዕቢተ እመኒ እለ እምፍጥረቶሙ ወእመኒ እምግዩራኒሁ ለእግዚ አብሔር ወአምዕዐ በዝንቱ ለይሠሮ ውእቱ ብእሲ እምሕዝቡ፤

በቃሉ አምላክ ነኝ ያለ ሰው ትውልዳቸው ከእስራኤል ከሆኑ ሰዎችም ቢሆን በዚህ ሰውንም እግዚአብሔርንም ቢያሳዝን ያ ሰው ከወገኑ ተለይቶ ይጥፋ፤

፴፩፤ እስመ ላዕለ ቃለ እግዚ አብሔር አበሰ ወዐለወ ትእዛዞ ተቀጥቅጦ ለይትቀጥቀጥ ውእቱ ብእሲ ወኃጢአቱሂ ላዕሌሁ፤

እግዚአብሔርን በድሏልና፤ ትእ ዛዙንም አፍርሷልና ያ ሰው በደንጊያ ተወግሮ በእሳት ተቃ ጥሎ ይሙት፤ የኃጢአቱም ፍዳ በራሱ ላይ ነው፤

ገባኤ

፴፪፤ ወሀለዉ ደቂቀ እስራኤል ውስተ ገዳም ወረከቡ ብእሴ እንዘ ይዔልድ ዕፀወ በዕለተ ሰንበት፤

የእስራኤል ልጆች በምድረ በዳ ሳሉ አንድ ሰው ቅዳሜ ቀን እንጨት ሲለቅም አገኙ፤

፴፫፤ ወአምጽእዎ እለ ረከብዎ ኀበ ሙሴ ወአሮን ወኀበ ኵሉ ተዓይኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል፤

እንጨት ሲለቅም ያገኙትም ሰዎች ያን ሰው ወደ ሙሴና ወደ አሮን ወደ እስራኤልም ልጆች ሠራዊት ሁሉ አመጡት፤

፴፬፤ ወአውዐልዎ ውስተ ሙዓል እስመ አልቦ ዘከሠቱ ዘከመ ይሬስይዎ፤

ከዚያ አስቀድመው በሰንበት ቀን እንጨት ሲለቅም አግ ኝተው የፈረዱበት ሰው አል ነበረምና ወደ እግዚአብሔር እስኪያመለክቱ ድረስ በግዞት ቤት አኖሩት፤

፴፭፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ሞተ ለይሙት ውእቱ ብእሲ ወይውግርዎ በዕብን ኵሉ ትዕይንት፤

ሙሴ ይህ ሰው ይሙት፤ ይዳን ብሎ ቃለ እግዚአ ብሔር ጠይቆ ነበርና፤ እግዚ አብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤ ያ ሰው የሞት ሞት ይሙት፤ ሠራዊቱ ሁሉ በደ ንጊያ ወግረው በእሳት አቃጥ ለው ይግደሉት አለው፤

www.ethiopianorthodox.org

ጠፉ ያውቃልና በሕዝቡ ጥፋት አዘነ ሲል ነው እንጂ፤

ወይቤሎ ለእግዚአብሔር ኢትነጽር መሥዋዕቶሙ እልቦ ዘነሣእኩ ወኢዘአሐዱ እምኔሆሙ ፈተውየ ወአልቦ ዘአሕሠምኩ ወኢላዕለ አሐዱ እምኔሆሙ ።

እግዚአብሔርንም እንዲህ አለው፤ የነዚህን መሥዋዕታቸውን በዓይነ ምሕረት አትመልከት፤ ገንዘብ ወድጄ ከነሱ ከአንዱ ስንኳን የተቀበልኩት የለም፤ ከነሱ በአንዱ ላይ ክፉ ሥራ የሠራሁትም የለም አለው ፤

፲፮፤ ወይቤሎ ሙሴ ለቆሬ ቀድስ ትዕይንተከ ወኩኑ ድልዋነ ቅድመ እግዚአብሔር አንተ ወእሙንቱ ወአሮን ለጌሠም ፡

ሙሴም ቆሬን ሠራዊትህን ለይ፤ አንድም ሰውነትህን ንጹሕ አድርግ፤ አንተም እነሱም በእግዚአብሔር ፊት የተዘጋጃችሁ ሁኑ፤ አሮንም ለነገ ይዘጋጅ አለው ፤

፲፯፤ ወይንሣእ አሐዱ አሐዱ ማዕጠንቶ ወይደይ ዕጣነ ወያብእ አሐዱ አሐዱ ማዕጠንቶ ቅድመ እግዚአብሔር ፡

አንዱም አንዱም ጽናውን ይዞ ዕጣኑን ይጨምር፤ አንዱም አንዱም ጽናውን ይዞ ወደ ደብተራ ኦሪት ይግባ ፤

፲፰፤ ወነሥአ አሐዱ አሐዱ ማዕጠንቶ ወወደዩ ውስቴቱ እሳተ ወወደዩ ዕጣነ ፡

አንዱም አንዱም ጽናውን አነሣ፤ ፍሕሙን አድርገው በዚያ ላይ ዕጣን ጨመሩበት፤

ወቆሙ ሙሴ ወአሮን ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ፡

ሙሴና አሮንም በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ቆመው ነበር ፤

፲፱፤ ወሮዶሙ ቆሬ ምስለ ኵሉ ትዕይንቱ ወአስተርአየ ስብሐተ እግዚአብሔር ለኵሉ ትዕይንት ፡

ቆሬም ሙሴንና አሮንን ከሠራዊቱ ጋር በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ከበባቸው፤ የእግዚአብሔርም ብርሃን ለሠራዊቱ ሁሉ ታየ ፤

፳፤ ወነበቦሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ፡

እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን ተናገራቸው፤



፳፩፤ ወይቤሎሙ ተገኀሡ እምነ ማዕከሎሙ ለዝንቱ ትዕይንት ወአጠፍእሙ በምዕር ፡

ከዚህ ሠራዊት መካከል ተለዩ፤ እነሱንም አንድ ጊዜ አጠፋቸዋለሁ አላቸው፤

፳፪፤ ወወድቁ በገጾሙ ወይቤሉ እግዚኦ አምላኩ ለኵሉ ዘሥጋ ወለኵሉ ዘነፍስ ለእመ አሐዱ ብእሲ አበሰ ዲበ ኵሉ ትዕይንት ይከውን መዓተ እግዚአብሔር ፡

ሙሴና አሮንም በግንባራቸው ወድቀው የሥጋዊና የደማዊ ፈጣሪ አቤቱ አንድ ሰው ቢበድል በሠራዊቱ ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ ይሆናልን፤ አንድም አንድ ቆሬ ቢበድል መላው እስራኤልን ታጠፋለህን አሉ፤

፳፫፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው ፤

፳፬፤ ንግሮሙ ለትዕይንት ይትገኀሡ እምዓውደ ትዕይንተ ቆሬ ፡

ከቆሬ ሠፈር ይርቁ ዘንድ ለሠራዊቱ ንገራቸው አለው፤

፳፭፤ ወተንሥአ ሙሴ ወሖረ ኀበ ዳታን ወአቤሮን ወሖሩ ምስሌሁ ኵሎሙ አዕሩገ እስራኤል ፡

ሙሴም ተነሥቶ ወደ ዳታንና ወደ አቤሮን ሰፈር ሄደ፤ የእስራኤልም ሽማግሌዎች ሁሉ ከሱ ጋር ሄዱ ፤

፳፮፤ ወነገሮሙ ለትዕይንት ወይቤሎሙ ተገኀሡ እምዓውደ ተዓይኒሆሙ ለእሉ ሰብእ እኩያን ወኢትግሥሡ እምነ ኵሉ ዘዚአሆሙ ከመ ኢትትኀጐሉ በኵሉ ኃጢአቶሙ ፡

ከነዚህ ክፉ ሰዎች ሰፈር ዙሪያ ተለዩ፤ በኃጢአታቸውም እንዳትጠፉ ከነሱ ገንዘብ ሁሉ አትንኩ ብሎ ለሠራዊቱ ነገራቸው ፤

፳፯፤ ወተግኅሡ እምዓውደ ትዕይንተ ቆሬ ወወፅኡ ዳታን ወአቤሮን ወቆሙ ኀበ ኆኅተ ደብተራሆሙ ወአንስቲያሆሙኒ ወደቂቆሙኒ ወንዋዮሙኒ ፡

ከቆሬ ሠራዊት ሠፈር ተለዩ፤ ዳታንና አቤሮንም ወጥተው ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር ገንዘባቸውን ይዘው በድንኳናቸው ደጃፍ ቆሙ፤

፳፰፤ ወይቤ ሙሴ በዝንቱ ተአምሩ ከመ እግዚአብሔር ፈነወኒ

www.ethiopianorthodox.org

በሙታኑና በሕያዋኑ መካከል ቆመ፣ ‹‹ተዘከር አብርሃምሃ ወይስሐቅሃ ወያዕቆብሃ ዘመሐልከ በርእስከ እያለ ጸለየ›› ቸነፈሩም ጸጥ አለ ፤

፴፱፤ ወኮኑ እለ ሞቱ በብድብድ እልፈ ወአርባዓ ምእተ ወሰብዓተ ምእተ ዘእንበለ እለ ሞቱ ምስለ ቆሬ ፡

ከቆሬ ጋራ ከሞቱ ሰዎች በቀር በቸነፈር የሞቱት እልፍ ከአራት ሺህ ከሰባት መቶ (አሥራ አራት ሺህ ሰባት መቶ) ሆኑ ፤

፵፤ ወገብአ አሮን ኀበ ሙሴ ውኀበ ደብተራ ዘመርጡል ፡

ቸነፈሩ ጸጥ ካለ በኋላ አሮን ሙሴ ወደ አለበት ወደ ደብተራ ኦሪት ተመለሰ፡፡

## ምዕራፍ ፲፯

፩፤ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ፡

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው ፤

፪፤ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወንሣእ በኀቤሆሙ በትረ ለለ አብያተ አበዊሆሙ እምኀበ ኵሉ መላእክቲሆሙ ዘዘአብያተ አበዊሆሙ ዐሠርተ ወክልኤተ አብትረ ወለለአሐዱ ጸሐፍ ስሞ ውስተ በትሩ ፡

እሊህ ሁሉ የሞቱ የሹመት ምልክት ባላሳይህ አይደለምን፣ አሁንም በየአባቶቻቸው ወገን ካሉት አለቆች አሥራ ሁለት በትር ተቀብለህ የያንዳንዱን ሰውስሙን በበትሩ ጻፍ ፤

፫፤ ወጸሐፍ ስሞ ለአሮን ውስተ በትረ ሌዊ እስመ ለለሕዝበ ቤተ አበዊሆሙ አሐተ በትረ ይሁቡ ፡

የአሮንንም ስም በሌዊ በትር ጻፍ አለው፣ የሌዊ በትር በእጁ ነበረችና ሕዝቡም በየአባታቸው ወገን አንዳንድ በትር ይሰጣሉና፤

፬፤ ወታንብሮን ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ቅድመ ታቦት በዘቦቱ አስተርኢ ለከ በህየ ፡

ያሥራ አንዱን አለቆች በትር አሥራ ሁለተኛ የአሮንን በትር ጨምረህ በታቦቱ አንጻር ልዩ በሆነች ድንኳን ውስጥ በዚያ በምትታይህ ቦታ አኑር ፤

፭፤ ወለዝክቱ ብእሲ ዘአነ ኃረይክዎ ትሠርፅ በትሩ ወአሴስል እምኔከ ነጐርጓሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ዘኵሎ ዘያንጐረጕሩ እሙንቱ በላዕሌክሙ ፡

እኔ ለሹመት የመረጥኩት የዚያ ሰው በትሩ ትለመልማለች፣ በሹመት ምክንያት በናንተ ላይ የሚያንጐራጕሩትን የእስራኤልን ልጆች እንጕርጕሮም ከናንተ አርቃለሁ ፤

፮፤ ወነገሮሙ ሙሴ ለደቂቀ እስራኤል ወወሀብዎ ኵሎሙ መላእክቲሆሙ በትረ ለለአሐዱ መልአክ፣

ሙሴም ለእስራኤል ልጆች በየአለቆቻችሁ አንዳንድ በትር አምጡ ብሎ ለእስራኤል ልጆች ነገራቸው፣ እያንዳንዱ አለቃም አንዳንድ በትር ሰጡት ፤

ወለለመልአክ በትር ዘዘአብያተ አበዊሆሙ ዐሠርቱ ወክልኤቱ አብትር ወበትረ አሮንሂ ማዕከለ አብትሪሆሙ ፡

በየአባቶቻቸው ወገን የተሾሙ የያንዳንዱ አለቃ በትር አሥራ ሁለት ነው፣ የአሮን በትርም በመካከላቸው ነበረች ፤

፯፤ ወአንበሮን ሙሴ ለውእቶን አብትር ቅድመ እግዚአብሔር ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ፡



ሙሴም እነዚያን በትሮች ልዩ በሆነች ድንኳን ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት አኖራቸው ፤

፰፤ ወኮነ በሳኒታ቉ ቦአ ሙሴ ወአሮን ውስተ ደብተራ ዘመርጡል ፡

በነጋው እንዲህ ሆነ፣ ሙሴና አሮን ወደ ደብተራ ኦሪት ገቡ ፤

ወናሁ ሠረፀት በትረ አሮን እንተ ቤተ ሌዊ ወአውፅአት ቈጽለ ወጸገየት ጽጌ ወፈረየት ከርካዓ ፡

እነሆ ከሌዊ የተገኘች የአሮን በትር ለመለመች፣ አበበች፣ ለውዝ ገውዝ በኰረሎሚ አፈራች፣ ሐተታ ለጊዜው በሹመት ተጣልተዋልና እንዲህ አድርጎ አለያይቷቸዋል፣ ለኋላው ግን ምሳሌ ነው፣ በትር የእመቤታችን፣ ፍሬው የጌታ፤ አንድም በትር የጌታ፣ ፍሬው የትሩፋት፤ አንድም በትር የመስቀል፣ ፍሬው የዕሤት፣ የሥጋው የደሙ ምሳሌ ነው፤

፱፤ ወአውፅኦን ሙሴ ለኵሎን አብትሪሆሙ እምቅድመ እግዚአብሔር ኀበ ኵሎሙ ደቂቀ እስራኤል ወርእዩ ወነሥኡ አሐዱ አሐዱ በትሮ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ከሌዋውያን ወገን ያይደለ ከሌላ ወገን የተወለደ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የገባ ይሙት፡

፰፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአሮን ናሁ አነሂ ወሀብኩክሙ ትዕቀቡ ዘያቀድሙ አብኡ ሊተ እምኵሉ ዘይትቄደሱ እምደቂቀ እስራኤል ለከ ወሀብኩከ እስከ ትረሥዕ ወእምድኅሬከ ለደቂቅከ ሕግ ዘለዓለም፤

እግዚአብሔርም አሮንን የእስራኤል ልጆች ከገንዘባቸው ለይተው አስቀድመው የሚያቀርቡትን ትጠብቁ ዘንድ እነሆ ሰጠኋችሁ፤ እስክታረጅ ላንተ ሰጠሁህ፤ ካንተም በኋላ ለልጆችህ የዘለዓለም ሥርዓት ነው፤

፱፤ ወዝንቱ ይኩንክሙ ለክሙ እምዘይትቄደስ ለቅዱሳን፤

እስራኤል ከገንዘባቸው ለይተው የሚያመጡት ይህ ለናንተ ይሁናችሁ፤

ወእምዘምሥዋዕ እምኵሉ ቍርባኖሙ ወእምኵሉ መሥዋዕቶሙ፤ ወእምኵሉ ዘንስሐሆሙ ወእምኵሉ ዘኃጣይኢሆሙ ኵሉ ዘያመጽእ ሊተ እምኵሉ ዘቅዱሳን ለከ ወለደቂቅከ ውእቱ፤

በመሠዊያው ካለ ከቍርባናቸው ሁሉ ከመሥዋዕተ ንስሓው ከመሥዋዕተ ኃጢአቱ ሁሉ ለይተው ያመጡት ሁሉ ለአንተና ለልጆችህ ነው፤

፲፤ በቅዱሰ ቅዱሳን ብልዕዎ ወኵሉ ተባዕት ለይብልዖ እስመ ቅዱስ ውእቱ ለከ፤

በተለየ ቦታ ሁናችሁ ብሉት፤ ከአንተ ወገን ወንድ ወንዱ ሁሉ ይብላው፤ ላንተ የተለየ ስጦታ ነውና፤

፲፩፤ ወዝንቱ ይኩንክሙ ለክሙ እምቀዳሜ ሀብቶሙ ወእምኵሉ ዘያበውኡ ደቂቀ እስራኤል ለከ ወሀብኩከ ወለደቂቅከ ወለአዋልዲከሂ ምስሌከ ሕግ ዘለዓለም፤

ይህ ለናንተ ሥርዓት ይሁናችሁ የእስራኤል ልጆች ከሚያገቡትና ከመጀመሪያ ስጦታቸው የተለየውን የዘለዓለም ሥርዓት ሲሆን ለአንተ ሰጠሁህ፤ ካንተ ጋር ላሉ ለሴቶች ልጆችህና ለወንዶች ልጆችህም ሰጠኋቸው፤

ኵሉ ዘንጹሕ በውስተ ቤትከ ለይብልዖ፤

በቤትህ ያለ ንጹሕ ሁሉ ይብላው፤

፲፪፤ ኵሎ ቀዳምያተ ቅብዕ ወኵሎ ቀደምያተ ወይን ወዘሥርናይ ወኵሎ ዘያበውኡ ለእግዚአብሔር ለከ ወሀብኩከ፤



የዘይቱን መጀመሪያ፤ የወይኑንና የሥንዴውንም መጀመሪያ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡትን ሁሉ ላንተ ሰጠሁህ፤

፲፫፤ ወኵሎ ቀዳሚ እክል ዘበኵሉ ምድሮሙ ወኵሎ ዘየመጽኡ ለእግዚአብሔር ለከ ወሀብኩከ ኵሉ ዘንጹሕ በውስተ ቤትከ ለይብልዖ፤

በምድራቸው ሁሉ ያለ የእህሉን መጀመሪያ ሁሉ ለእግዚአብሔር የሚያመጡትን ሁሉ ላንተ ሰጥቼኻለሁና በቤትህ ያለ ንጹሕ ሁሉ ይብላው፤

፲፬፤ ኵሉ ዘየሐርሙ በውስተ ደቂቀ እስራኤል ለከ ውእቱ፤

በእስራኤል ልጆች ዘንድ ሥርዓት የሚያደርጉት (የሚከለከለው) ሁሉ ላንተ ነው፤

፲፭፤ ወኵሉ ዘይፈትሕ ማኅፀነ እምነ ኵሉ ዘሥጋ ወኵሉ ዘያመጽኡ ለእግዚአብሔር እምሰብእ እስከ እንስሳ ለከ ውእቱ፤

ከሥጋዊ ከደማዊ ወገን መጀመሪያ የሚወለደው ሁሉ ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ ‹እስከ ከብት ድረስ› ለእግዚአብሔር የሚያገቡት ሁሉ ላንተ ነው፤

ባሕቱ በኵረ ሰብእ በቤዛ ይትቤዘው ወበኵረ እንስሳሂ ዘርኩስ ታቤዙ፤

ነገር ግን የሰውን የበኩር ልጅ በገንዘብ ይቤገፉት ማለት በገንዘብ ይለውጡት፤ የፈረስ የበቅሎ የአህያውን በኵርም ባለ ከብቱ ይቤገሮው ‹ይለውጠው፤

፲፮፤ ወቤዛሁ ለዘአሐዱ ወርኅ ሐምስቱ ሰቅል በሰቅል ዘቅዱስ ዕሥራ አቦሊ ውእቱ፤

አንድ ወር የሆነው ልጅ ዋጋው በቤተ መቅደስ ሚዛን አምስት ወቄት ነው፤ ይኸውም ሃያ መሐልቅ ነው፤

፲፯፤ ዘእንበለ በኵረ አልሕምት ወበኵረ አባግዕ ወበኵረ አጣሊ ዘኢታቤዙ እስመ ቅዱስ ውእቱ፤

ንጹሕ ነውና ከማትቤገሮው ‹ከማትለውጠው› ከላሙ ከበጉ ከፍየሉ በኵር በቀር፤

ወትክዑ ደሞሙ ኀበ ምሥዋዕ ወስብሖሙ ትገብር መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ለመዓዛ ሠናይ ፤

የነዚህንም ደማቸውን ከመሠዊያው ላይ አፍስሰው፤ ስባቸውንም በጎ መዓዛ ሲሆን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርገህ አቅርበው፤

www.ethiopianorthodox.org

በአባቶቻችንም መከራ አጸ
ኑብን፤

፲፮፡ ወጸራሕነ ኀበ እግዚአብሔር ወሰምዐ እግዚአብሔር ቃለነ ወፈነወ መልአኮ ወአውፅአነ እምግብጽ፤

ወደ እግዚአብሔር ጩኸን ስመንን፤ እግዚአብሔርም ልመ ናችንን ሰምቶ መልአኩን ልኮ ከግብጽ አወጣን፤

ወይእዜኒ ሀለውነ ውስተ ቃዴስ ጥቃ ደወለ ብሔርከ፤

አሁንም በአገርህ አውራጃ አጠገብ በቃዴስ አለን፤

፲፯፡ ወአኅልፈነ እንተ ብሔርከ ወሀገርከ ወኢነኀልፍ እንተ ገራህትከ ወኢላዕለ ዓፀደ ወይንከ ወኢንሰቲ እምዓዘቅትከ ማየ፤

በአውራጃህ በአገርህ አሳል ፈን፤ በእርሻህና በወይንህ ቦታ ላይ አንሄድም፤ ከጕድጓ ድህም ውሀ አንጠጣም፤

ፍኖተ መጽያህት ነሐውር ወኢ ንትገኃሥ ኢለየማን ወኢለፀጋም እስከ ነኃልፍ እምደወልከ፤

ጥርጊያውን ጎዳና እንሄዳለን እንጂ ከአውራጃህ እስክናልፍ ድረስ ወደቀኝም ወደግራም አንልም አለው፤

፲፰፡ ወይቤሎ ንጉሠ ኤዶም ኢተኀልፍ እንተ ላዕሌየ ወእመ አኮሰ ንትቃተል ወእወፅዕ እት ቀበልከ፤

የኤዶም ንጉሥም በኔ አገር ላይ አታልፍም፤ ይህም ካል ሆነ እንዋጋለን፤ በጦርነት እቀበልህ ዘንድ እወጣለሁ አለው፤

፲፱፡ ወይቤልዎ ደቂቀ እስራኤል እንተ መንገለ አድባር ነኀልፍ ወለእመኒ ሰተይነ እምነ ማይከ ንሕነ ወእንስሳነ ሤጦ ንሁብከ፤

የእስራኤልም ልጆች እንዲህ አሉት፤ ደጋ ደጋውን እንሄ ዳለን እኛም ከብቶቻችንም ከጕድጓድህ ውሀ ብንጠጣም ዋጋውን እንከፍልሃለን፤

ወዘንቱሰ ኢኮነ ወኢምንተኒ እንተ መንገለ አድባር ነኀልፍ፤

ይህስ መንገድን መከልከል አይገባም፤ ምንም አይጎዳህም ወዲያውም ደጋ ደጋውን እን ሄዳለን አሉት፤

፳፡ ወይቤ ኢተኀልፍ እንተ ላዕሌየ ወወፅአ ንጉሠ ኤዶም ወተቀ በሎሙ ለእስራኤል ምስለ ሰብእ ክቡድ ወበእድ ጽንዕት፤

በኔ አገር ላይ አትሄድም ብሎ የኤዶም ንጉሥ ከብዙ



ሠራዊት ጋር ወጥቶ እስ ራኤልን በጽኑዕ ሰልፍ ተቀበ ላቸው፤

፳፩፡ ወኢፈቀደ ንጉሠ ኤዶም የሀቦሙ ምኅላፈ እንተ ደወሉ ወተግኅሡ እስራኤል እምኔሁ፤

የኤዶምያስ ንጉሥ መንገድ ይሰጣቸው ዘንድ አልወደ ደምና እስራኤል ከሱ ፈቀቅ አሉ (ሸሹ)፤ ሙሴ ቃለ እግዚአብሔር ጠየቀ፤ ኤዶ ምን ለኤሳው ዕፃ አድርጌ ሰጥቼዋለሁና አትዋጋ አለው፤ ከሱ አልፈው ሂደዋል፤

፳፪፡ ወግዕዙ እምቃዴስ ወኃደሩ ኵሉ ትዕይንት ውስተ ደብረ ሆር፤

እስራኤል ከቃዴስ ተጕዘው ሆር በሚባል ተራራ ሰፈሩ፤

፳፫፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ ሆር በመንገለ ደወለ ምድሩ ለኤዶም እንዘ ይብል፤

እግዚአብሔር ለሙሴ በኤ ዶም አገር አውራጃ ባለ በደ ብረ ሆር እንዲህ ብሎ ነገረው፤

፳፬፡ ለይትወሰክ አሮን ኀበ ሕዝቡ እስመ ኢትበውኡ ውስተ ይእቲ ምድር ዘአነ እሁቦሙ ለደቂቀ እስራኤል እስመ አምዓዕክሙኒ በኀበ ማየ ቅስት፤

ጠብ ክርክር በተደረገበት ውሀ ስለ አሳዘናችሁኝ እኔ ለእስራኤል ልጆች ወደም ሰጣቸው ወደዚያች አገር አትገቡምና አሮን በሞት ወደ አባቶቹ ይጨመር፤ አባቶቹ፤ ወደ ወረዱበት መቃብር ይወ ረድ አለው፤

፳፭፡ ወነሥኦሙ ለአሮን ወለአል ዓዛር ወልዱ ወአዕረጎሙ ውስተ ደብረ ሆር በቅድመ ኵሉ ትዕይንት፤

አሮንንና ልጁ አልአዛርን ሙሴ በሠራዊቱ ፊት ወደ ሆር ተራራ አወጣቸው፤

፳፮፡ ወንሣእ አልባሲሁ ለአሮን እምላዕሌሁ ወአልብሶ ለአልዓዛር ወልዱ ወይትወሰክ አሮን ወይ ሙት በህየ፤

የአሮንን የሹመት ልብሱን ከሱ አንስተህ ለልጁ ለአል ዓዛር አልብሰው፤ አሮን ግን በዚህ ይሙትና ወደ አባቶቹ በሞት ይጨመር አለው፤

፳፯፡ ወገብረ ሙሴ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ወአዕረጎሙ ውስተ ደብረ ሆር በቅድመ ኵሉ ትዕይንት፤

ሙሴም እግዚአብሔር እንዳ ዘዘው በሠራዊቱ ሁሉ ፊት

www.ethiopianorthodox.org

ናበት ድምፁን ሰምቶ መል ኩን አይቶ ይዳን የጸናበት ግን ድምፁን ብቻ ሰምቶ ይዳን አለው፤

፱፤ ወገብረ ሙሴ አርዌ ምድር ዘብርት ወአቀሞ ኀበ ይትኤመሩ ወእምከመ ነሰኮ አርዌ ምድር ለሰብእ ይኔጽሮ ለዝክቱ አርዌ ዘብርት ወየሐዩ፡፡

ሙሴም አርዌ ብርቱን ሠርቶ በሚተያዩበት ቦታ ሰቀለው፤ ነዘሩ እባብ ሰውን በነደፈው ጊዜም ያን የብርቱን እባብ አይቶ ይድን ነበር፡፡ ይኸውም ምሳሌ ነው፡፡ አርዌ ምድር የዲያብሎስ፡፡ አርዌ ብርት የጌታ፡፡ በደማዊት ነፍስ ሕያው የሚሆን አርዌ ምድር የነደፋቸውን አርዌ ብርት እንዳዳናቸው፡፡ በባሕ ርዩ ሕያው የሚሆን ዲያብ ሎስ የጎዳቸውን ጌታም በሰ ውነቱ ሐማሚ መዋቲ ሁኖ ለማዳኑ ምሳሌ፤ አንድም መርዝ ያለው አርዌ ምድር የጎዳቸውን አርዌ ብርት እንዳ ዳናቸው የኃጢአት መርዝ ያለው ዲያብሎስ የጎዳቸውን ንጹሐ ባሕርይ ጌታ የማዳኑ ምሳሌ፤ አንድም አርዌ ምድር የአዳም፡፡ አርዌ ብርት የጌታ፡፡ አርዌ ምድር በመርዙ የጎዳ ቸውን አርዌ ብርት እንዳ ዳናቸው አዳም በኃጢአቱ የጎ ዳቸውን ጌታ በቸርነቱ የማ ዳኑ ምሳሌ፤ አንድም ብርት ጽሩይ ነው፡፡ ጌታም ጽሩየ ባሕርይ ነውና፤ አንድም ብርት ቀይ ነው፡፡ ጌታም ሥጋውን ቆርሶ፡፡ ደሙን አፍስሶ ዓለምን አድኗልና፡፡ አንድም ብርት ድምፁ ከሩቅ ይሰማል፡፡ የጌታም ሕማሙ ሞቱ ጽንፍ እስከ ጽንፍ ተሰምቷልና፤ አንድም ብርት ከቆላም ከደጋም ይለቀማል፡፡ ጌታም ከሕዝብ ከአሕዛብ ይወ ለዳልና ድምፁን ሰምተው መልኩን አይተው የዳኑ የሐ ዋርያት፡፡ ድምፁን ብቻ ሰም ተው የዳኑ እስከ ዕለተ ምጽአት የሚነሱ ምእመናን ምሳሌ ነው፤

፲፤ ወግዕዙ ደቂቀ እስራኤል ወኀደሩ ውስተ አጋቦት፡፡

የእስራኤል ልጆችም ተጉዘው በአጋቦት ሰፍረው አደሩ፤

፲፩፤ ወግዕዙ እምአጋቦት ወኀደሩ ውስተ ጌልጋይ ማዕዶተ ገዳም እንተ አንጻረ ገጹ ለሞዓብ መንገለ ምሥራቀ ፀሐይ፡፡



ከአጋቦት ተጉዘው በፀሐይ መውጫ በኩል በሞዓብ አንፃር ባለች ምድረ በዳ በጌልጋይ አደሩ፤

፲፪፤ ወግዕዙ እምህየ ወኀደሩ ውስተ ቆላተ ዛሬት፡፡

ከጌልጋይም ተጉዘው ዛሬት በሚባል በረሀ አደሩ፤

፲፫፤ ወግዕዙ እምህየ ወኃደሩ ውስተ ማዕዶተ አርኖን ዘይክዑ ማየ እምአድባር ዘአሞሬዎን፡፡

ከዛሬት ተጉዘው ከአሞሬዎን ደጋ ነቅቶ ውሀውን በአሞ ሬዎን ተራራዎች በሚያፈስ በአርኖን ማዶ አደሩ፤

እስመ ደወሎሙ ውእቱ ለሞዓብ ወማዕከለ ሞዓብ ወማዕከለ አሞ ሬዎን ውእቱ፡፡

እስመን አሁን አይሻውም፡፡ አርኖንም በአሞሬዎንና በሞ ዓብ መካከል ያለ የሞዓባ ውያን አዋሳኝ ነው፤ አንድም በአሞሬዎንና በሞዓብ መካ ከል አዋሳኝ ነውና (ዘይክዑ ማየ ሳለው)፤

፲፬፤ ወበበይነ ዝንቱ ይብል ውስተ መጽሐፍ ፀብዑ ለእግዚአብሔር አውዓያ ለዛኦሙ፡፡

ስለዚህ ነገር በወግ በታሪክ የእግዚአብሔር ሰልፉ ዛኦሙ የምትባል አገርን አጠፋት አለ፤ አንድም ለዛኦሞሙ ይላል፡፡ ዋንዛቸውን ጣዖታቸውን አጠፋ፤

ወአቀመ ወኃይዝተ አርኖን ዘሀለወ ውስተ ኤር ዘይሰመይ ደወለ ሞዓብ፡፡

የሞዓብ አውራጃ በሚባል በኤር ውስጥ ያለ የአርኖን ፈሳሾችንም አቆመ ማለት፤ የእስራኤል ሰልፉ የአርኖንን ኃያላን አጠፋ፤

፲፮፤ ወእምህየ ውስተ ዓዘቅት ዘይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ አስተጋብእ ሕዝበ ወእሁቦሙ ማየ ዘይሰትዩ፡፡

ከዚያም ተጉዘው እግዚአብ ሔር ሙሴን ሕዝቡን ሰብስብ፡፡ የሚጠጡት ውሀ እሰጣቸ ዋለሁ ብሎ ወደ ነገረው ቦታ ደረሱ፤

፲፯፤ ወይእተ አሚረ ኀለዩ እስራ ኤል ዛተ ማኅሌተ በኀበ ይእቲ ዐዘቅት አቅደሙ ሎሙ ዐዘቅተ፡፡

ያን ጊዜ እስራኤል ይህን ምስ ጋና በዚያች ጉድጓድ አመ ሰገኑ፤

www.ethiopianorthodox.org

በሐሴቦንና በሴዎን አገሮች ጦር ወጥታ የሞዓብን ሰዎች አጥፍታለችና የአርኖንንም ኃያላን አጥፍታለችና፤

፳፰፤ አሌ ለከ ሞዓብ አኅጐል ከዮሙ ለሕዝበ ኮሞስ እለ ገብኡ፣

ወደ ድካም የተመለሱ የጣዖቱን ወገኖች አጥፍተሻቸዋልና ሞዓብ ወዮልሽ፤

ወደቂቆሙሰ አድኃንክሙ ወአዋልዲክሙ ተዬወዋ ኀበ ሴዎን ንጉሠ አሞሬዎን፣

ወንዶች ልጆቻቸውን ግን አዳናችሁ፣ ሴቶች ልጆቻችሁም ወደ አሞሬዎን ንጉሥ ወደ ሴዎን ተማርከው ሄዱ፤

፳፱፤ ወዘርኦሙኒ ደምሰሶሙ እምሐሴቦን እስከ ዴቦን ፣

ከሐሴቦን እስከ ዴቦን ልጆቻቸውንም አጠፋባቸው፤

ወአንስቲያሆሙኒ ዓዲ አንደዳ እሳተ ላዕለ ምዓብ፤

ሴቶቻቸውም በሞዓብ ላይ ዳግመኛ እሳት አነደዱ፤ ማለት ጠብ አነሱ፣ ሴቶች ያመጡት ጠብ አይበርድምና፤ አንድም የሞዓብ ሴቶች ቲሀ (ችቦ) እያበሩ አዋግተዋልና፤

፴፤ ወነበረ እስራኤል ውስተ ኵሉ አህጉረ አሞሬዎን፣

እስራኤልም በአሞሬዎን ሀገሮች ሁሉ ኖሩ፤

፴፩፤ ወፈነወ ሙሴ ይርአይዋ ለኢያዜር ወእምዝ አስተጋብእዋ ምስለ አህጉሪሃ፤

ሙሴም ኢያዜርን ይሰልሏት ዘንድ ገብኛ ላከ፣ ከዚያም በኋላ ከአውራጃዋ ጋር እጅ አደረጓት፤

ወአውፅእዎሙ ለአሞሬዎን እለ ሀለዉ ህየ፣

በዚያ የሚኖሩ የአሞሬዎንን ሰዎችም ከዚያ አስወጧቸው፤

፴፪፤ ወተመይጡ ወዓርጉ ውስተ ፍኖተ ባሳን ፣

ተመልሰው ወደ ባሳን ጎዳና ሄዱ፤

ወወፅአ ዖግ ንጉሠ ባሳን ወተቀበሎሙ ምስለ ኵሉ ሕዝቡ ከመ ይትቃተሎሙ በአድራይን

የባሳን ንጉሥ ዓግም በአድራይን ይዋጋቸው ዘንድ ከሠራዊቱ ጋር ወጥቶ በጦርነት ተቀበላቸው፣



፴፫፣ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ኢትፍርሆ እስመ ውስተ እዴከ አገብኦ ወለኵሉ ሕዝቡ ወለኵሉ ምድሩ፣

እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፣ የዓግ ንጉሥ ባሳንን አትፍራው፣ ሠራዊቱንም አገሩንም በእጅህ እጥልልሃለሁና፤

ወትገብሮ ከመ ገበርከሁ ለሴዎን ንጉሠ አሞሬዎን ዘይነብር ውስተ ሐሴቦን፣

በሐሴቦን የሚኖር የአሞሬዎን ንጉሥ ሴዎንን ድል እንዳደረግኸው ድል ታደርገዋለህና አይዞህ አትፍራው አለው፤

፴፬፤ ወቀተሎ ሎቱ ወለደቂቁ ወለደቂቀ ሕዝቡ እስከ ኢያትረፈ ሎቱ ነፋጺተ ወወረሱ ምድሮሙ፣

ሽሽታ (ሽሽቶ) የሚያመልጥ ሳያስቀር እሱንም ልጆቹንም ሠራዊቱንም ሁሉ አጥፍቶ አገራቸውን ወረሱ።

## ምዕራፍ ፳፪

### ጉባኤ

፩፤ ወግዕዙ ደቂቀ እስራኤል ወነደሩ መንገለ ዓረባ ለሞዓብ ኀበ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ኢያሪኮ፣

የእስራኤል ልጆች ተጓዘው በኢያሪኮ አንጻር በዮርዳኖስ አጠገብ ባለች በሞዓብ በስተግራዋ ሰፍረው አደሩ፤

፪፤ ወሶበ ርእየ ባላቅ ወልደ ሶፎር ኵሎ ዘገብሩ እስራኤል በአሞሬዎን ፣

የሶፎር ልጅ ባላቅም እስራኤል በአሞሬዎን አገር ያደረጉትን ባየ ጊዜ፤

፫፤ ፈርህዎሙ ሞዓብ ለሕዝብ ጥቀ እስመ ብዙኃን እሙንቱ ወተሐውኩ እምቅድመ ገጾሙ ለደቂቀ እስራኤል፣

እስራኤል ብዙ ናቸውና የሞዓብ ሰዎች እስራኤልን እጅግ ፈሯቸው፣ የእስራኤልን ፊት ከማየታቸውም የተነሣ ታወኩ ተሸበሩ፤

፬፣ ወይቤሎሙ ሞዓብ ለአዕሩገ ምድያም ይእዜ ታኀልቆሙ ዛቲ ትዕይንት ለኵሎሙ እለ ዓውድነ ከመ ያኀልቅ ላሕም ሣዕረ ዘውስተ ገዳም፣

የሞዓብ ንጉሥ ባላቅም የምድያምን ሽማግሎች እንዲህ አላቸው፣ ላም የምድረ በዳውን ሣር በልቶ እንዲጨርስ በዙሪያችን ያሉትን ሕዝብ ይች ሠራዊት ትጨርሳለች አላቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

፪፡ ወአልዓለ አዕይንቲሁ ወርአዮሙ ለእስራኤል እንዘ ይግዕዙ በበሕዘቢሆሙ ወመጽአ ላዕሌሁ መንፈሰ እግዚአብሔር ምስለ ነገር፣

ዓይኑን አቅንቶ እስራኤልን በየወገኖቻቸው ሲጓዙ ባያቸው ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ረድኤት ትንቢት ከማናገር ጋር ወደሱ መጣ (አደረበት)፤

፫፡ ወይቤ በለዓም ወልደ ቢዖር ብእሲ ራትዕ ይቤ ዘይሬኢ ራእየ እምእግዚአብሔር ዘክሡታት አዕይንቲሁ እንዘ ይነውም፣

ወይቤና ይቤ አንድ ወገን ነው በንዋመ ሐኬት፣ በንዋመ ኃጢአት ተይዞ ሳለ ዓይነ ልቡናው የተገለጸ የእግዚአብሔርን ምሥጢር የሚያይ ቅን የሆነ የቢዖር ልጅ በለዓም እንዲህ አለ፤

፬፡ እፎ ሠናይ አብያቲከ ያዕቆብ ወተዓይኒከ እስራኤል፣

ያዕቆብ ወገንህ ምን ያምር፣ እስራኤል ሰፈርህ ምን ያምር፤

፭፡ ከመ አዕዋም ዘይጼልሉ ወከመ ገነት ዘኀበ ፈለግ ወከመ ትዕይንት ዘተከለ እግዚአብሔር ወከመ አርዘ ዘኀበ ማይ፣

እንስሳትን አራዊትን የሚጋርዱ ዛፎች ደስ እንደሚያሰኙ፣ በፈሳሽ አጠገብ ያለ ተክልም ደስ እንዲያሰኝ፣ እግዚአብሔር የፈጠረው የመላእክትም ከተማ ደስ እንዲያሰኝ፣ በውሀ ዳር ያለ ዛፍም በልምላሜው ደስ እንዲያሰኝ (ያማረ እንደሆነ) ወገንህ፣ ሰፈርህ ምን ያምር፤

፮፡ ወይወፅእ ብእሲ እምዘርኡ ወይቀኒ ብዙኃ አሕዛበ፣

ከልጁ ከነገደ ይሁዳ ዳዊት ይወለዳል፤ ብዙ አሕዛብንም ይገዛል፣ አንድም ክርስቶስ ከልጅ ልጁ ይወለዳል፣ ሕዝቡን አሕዛቡን ያስተምራል፤

ወትትሌዓል እምአጋግ እምጎግ መንግሥቱ ወተዐቢ

የዳዊት መንግሥት ከብዙ ነገሥታት መንግሥት ከፍ ከፍ ትላለች ትበልጣለች፤ አንድም የክርስቶስ መንግሥት ከብዙ ነገሥታት መንግሥት ትበልጣለች ማለት የባሕርዩ ናት፤

፯፡ ወእግዚአብሔር፣ መርሖ እምግብጽ ከመ ክብረ ዘአሐዱ ቀርኑ ውእቱ ሎቱ፣

እግዚአብሔር ከግብጽ መርቶ ያወጣው እስራኤል ቀንዱ



አንድ እንደ ሆነ በቀንዱ ተጠብቆ እንደሚኖር እንደ ርኤም ነው፤ አንድም በክፍለ ብርሃኑ ከጨረቃ ከከዋክብት ተለይቶ እንደ ከበረ እንደ ፀሐይ ነው፤

ወይበልዖሙ ለአሕዛብ ፀሩ ወያስተናጉዕ ስብሖሙ ወይነድፎሙ በአሕጻሁ ለፀሩ፣

ጠላቶቹ አሕዛብን ያጠፋቸዋል፣ ገንዘባቸውንም ይበላል፣ በጦሩም እየወጋ ይጥላቸዋል፤

፰፡ ይሰክብ ወየዓርፍ ከመ አንበሳ ወከመ ዕጓለ አንበሳ፣

እስራኤል የአሕዛብን ገንዘብ በልቶ እንደ አባት አንበሳ እንደ አንበሳ ግልገል ይተኛል ማለት አርፎ ተዘልሎ ይኖራል፣ መኑ ያነቅሖ ማንሻ፤ አንድም አባት አንበሳ፣ የአንበሳ ግልገል በልቶ ከተኛበት የሚቀሰቅሰው እንደ ሌለ፤

መኑ ያነቅሖ፣

እስራኤልን ማን ይቀሰቅሰዋል፤ አንድም የዐርፍ ከመ አንበሳ፣ አባት አንበሳ በልቶ እንዲያርፍ እስራኤልም ጠላቱን አጥፍቶ አርፎ ይኖራል፣ ወከመ ዕጓለ አንበሳ መኑ ያነቅሖ፣ የአንበሳ ግልገልም በልቶ ከተኛበት የሚቀሰቅሰው እንደ ሌለ እስራኤልን የሚቀሰቅስ ሰው ማነው?

እለ ይባርኩከ ቡሩካን ይኩኑ ወእለ ይረግሙከ ርጉማን ይኩኑ፣

የሚመርቁህ የተመረቁ ይሁኑ፣ የሚረግሙህም የተረገሙ ይሁኑ፤

፱፡ ወተምዐ ባላቅ ላዕለ በለዓም ወአስተጣፍሐ እደዊሁ፣

ባላቅም በበለዓም ተቆጥቶ እጁን አጨበጨበ፤

ወይቤሎ ባላቅ ለበለዓም ከመ ትርግሞሙ ሊተ ለጸላእትየ ጸዋዕኩከ ወናሁ ባርኮ ትባርክ ወሣልስከ ዝንቱ፣

ባላቅ በለዓምን ጠላቶቼን ትረግምልኝ ዘንድ ጠራሁህ እንጂ ተስፋቸውን ልትነግረኝ ጠራሁህን፣ እነሆ መመረቅን ትመርቃቸዋለህ፣ ይህም ሦስተኛህ ነው አለው፤

፲፡ ወይእዜኒ እቱ ቤተከ እቤ ከመ አክብሮ አክብርከ ወይእዜሰ ኢወሀበከ እግዚአብሔር ክብረ፣

አሁንም እንቢ ካልህ ወደ ቤትህ ግባ፣ እኔ ፈጽሜ እንዳከብርህ ተናግሬ ነበር፣ አሁን

www.ethiopianorthodox.org

ሚሆሙ መባሉ) መቅደሙ በምን ነው ቢሉ በመንግሥት ከእስራኤል ጋር በመዋጋት ነው፤

፳፡ ወርእዮሙ ለቄኔዎን ምስለ ነገር ወይቤ ጽንዕት እከይክ ወለ እመኒ ውስተ ኰኵሕ አንበርከ ዕጕሊከ፣

ቄኔዎንንም ነገር ከመናገር ጋር አያቸው፤ አንድም ነገር አድርጎ ተናገራቸው፣ ክፋትህ የጸናች ናት፣ ልጆችህንም በዋሻ ብታኖር፤

፳፩፡ ወለእመሂ ኮነ ለቤዖር ዕጕለ ጕሕሉቱ አሶር ይፄውወከ፣

ለቤዖርም ተንኮል ያለኝ ልጅ እኔ ብኖረው ባቢሎናዊ ይማ ርክሃል አለ፤

፳፪፡ ወርእዮ ለአግ ምስለ ነገር ወይቤ ኦ ኦ መኑ የሐዩ አመ ይገብሮ እግዚአብሔር ለዝንቱ፣

አግንም ነገር ከመናገር ጋር አየው (ነገር አድርጎ ተና ገረው)፣ እግዚአብሔር ይህን ነገር ባደረገው ጊዜ ወዮ ወዮ ማን ይድናል አለ፤

፳፫፡ ወይወፅእ እምእዴሆሙ ለቀጥያዎን ወየአክዩ አሶር በዕብ ራውያን ወዕብራውያን የአክዩ በአ ሶር ወእሙንቱሰ ኅቡረ ይጠፍኡ፣

ከአረማውያን እጅ የሚወጣ ማነው አሶራውያን በዕ ብራውያን፣ ዕብራውያንም በአ ሶራውያን ይከፋሉ ማለት አሕዛብ በእስራኤል በጠላት ነት ይነሣሉ፣ እስራኤልም በአ ሕዛብ ላይ በጠላትነት ይነሣሉ፣ እነሱ ግን ባንድነት ይጠፋሉ አለ፤

፳፬፡ ወተንሥአ በለዓም ወሖረ ወገብአ ውስተ ቤቱ ወባላቅሂ አተወ ቤቶ፣

በለዓም ተነሥቶ ሄደ፣ ወደ ሀገሩ ተመለሰ፣ ባላቅም ወደ ቤቱ ገባ፣ ሐተታ ሲሄድ መክሮት ሂዷል፣ ቁመህ አት ርገም አለኝ እንጂ ተቀምጠህ አትምከር አላለኝም፣ አሁንም የምነግርህን ስማኝ፣ እስራ ኤል መና ከደመና እያወረ ደላቸው፣ ውሀ ከደንጊያ እያ ፈለቀላቸው፣ ያለ ዓዕር ያለ ድካም እየተመገቡ በዝሙት ተናደዋልና፣ የሀገርህን ቆነጃ ጅት አስጊጠህ ጣዖቱን፣ ተረፈ መሥዋዕቱን አስይዘህ ስደዳ ቸውና በሰፈራቸው ዙሪያ ሁነው ይዝፈኑ፣ ወጥተው ፈቃዳችንን ፈጽሙ ሲሏቸው እናንተም የኛን ፈቃድ ፈጽሙ፣ ለጣዖቱ ስገዱ፣ ተረፈ



መሥዋዕቱን ብሉ ይበሏ ቸው፣ በዚህ ምክንያት (ይህን ሲያደርጉ) አምላካቸው ለአም ልኮቱ ቀንቶ ያጠፋልሃል ብሎ መክሮት ሂዷል፣ እንደ መከ ረውም በሚያመጣው ይታወ ቃል፡፡

## ምዕራፍ ፳፭

### ጉባኤ

፩፡ ወኃደሩ እስራኤል ውስተ ሰጢን ወተገመነ ሕዝብ ወዘመወ በአዋልደ ሞዓብ፣

እስራኤል በሰጢን ሰፍረው አደሩ፣ ንጹሕ የነበረ ወገንም በሞዓብ ሴቶች ልጆች ረከሰ፣ የአሕዛብን ሴቶች አስጊጦ የጣዖቱን ተረፈ መሥዋዕቱን አስይዞ ሰደዳቸው፣ በሰ ፈራቸው ዙሪያ ሁነው ይዘ ፍኑ ጀመር፣ እስራኤል ሂደው ሴቶችን ተነጣጠቋቸው፣ ፈቃዳ ችንን ፈጽሙ አሏቸው፣ ፈቃ ድስ የጋራ ነው፣ የኛን ፈቃድ በፊት ፈጽሙ፣ ለጣዖታችን ስገዱ፣ ተረፈ መሥዋዕታ ችንን ብሉ አሏቸው፣ ለጣዖቱ ሰገዱ፣ ተረፈ መሥዋዕቱንም በሉ፤

፪፡ ወጸውዓሆሙ ውስተ መሥዋ ዕተ አማልክቲሆን ወበልዑ ሕዝብ መሥዋዕቶን ወሰገዱ ለአማል ክቲሆን፣

ለጣዖቶቻቸው ወደ ሠዉት መሥዋዕት ጠሯቸው ማለት መሥዋዕቱን ብሉልን አሏ ቸው፣ ሕዝቡም የነዚያን መሥዋዕታቸውን በሉ፣ ለጣዖታ ቸውም ሰገዱ፤

፫፡ ወተፈጸመ እስራኤል በብዔል ፌጎር፣

እስራኤል በፌጎር የቆመውን ጣዖት በማምለክ በሞት ተፈ ጸመ፤ አንድም ወተፈጸመ ዘብ ዔል ፌጎር ይላል፤ የጣዖቱን ፍቅር ተቀባ፤ አንድም ቅብ ዓት እንጂ ማለት ኅድረት ማለት ነው፣ የጣዖቱን ፍቅር በልቡናው አሳደረ፣ ብዔል ጣዖቱ፣ ፌጎር የቆመበት ቦታ ነው፤ አንድም ፌጎር በጣዖቱ ያደረው ሰይጣን፣ ጣዖት ማም ለክ የጀመረው ሰው ነው፤

ወተምዓ መዓተ እግዚአብሔር ላዕለ እስራኤል፣

እግዚአብሔርም በእስራኤል ፈጽሞ ተቈጣ (ፈረደ)፤

፬፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ንሥኦሙ ለመላእክተ ሕዝብ

www.ethiopianorthodox.org

ወተዛለፎሙ በእንተ ትእዛዙ ለእግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር ሙሴን ሕዝቡ የሚበድሉ፣ አለቆቹ ባይመክሯቸው ባያስተምሯቸው አይደለምን፣ ሕዝቡን ምከሩ አስተምሩ ብለህ አለቆችን ዝለፋቸው ተቆጣቸው አለው፤

ፀሐይኒ ይሴስል እምቅድመ መንሱተ መዓቱ ለእግዚአብሔር እምነ እስራኤል፣

እግዚአብሔር ፈርዶ ካመጣው መዓት የተነሣ ፀሐይ ረድኤቱ ከእስራኤል ይርቃል፤

፭፤ ወይቤሎሙ ሙሴ ለሕዝበ እስራኤል ቅትሉ አሐዱ አሐዱ እምኔክሙ ሰብአ ቤትክሙ እለ ገብሩ በብዔል ፌጎር፣

ሙሴም የእስራኤልን ወገኖች ከናንተ አንዳዱም አንዳዱም በፌጎር ለቆመው ጣዖት የሰገዱትንና የጣዖቱን መሥዋዕት የበሉትን የቤታችሁን ሰዎች ግደሉ አላቸው፤

፮፤ ወናሁ አሐዱ አሐዱ ብእሲ እምደቂቀ እስራኤል መጽአ ወወሰደ ለእኁሁ ኀበ መድናዊት በቅድመ ሙሴ ወበቅድመ ኵሉ ተዓይኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል፣

ከእስራኤል ልጆች አንዱም አንዱም ሰው መጥቶ በሙሴና በሠራዊቱ ሁሉ ፊት አላፍር ብሎ አንዲቱን የምድያም ሴት አናጥቀኝ ብሎ ወንድሙን ወሰደው፤

ወእሙንቱሰ ሀለዉ ይበክዩ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል፣

እነሙሴ ግን ይህ ሥራ በመሠራቱ በደብተራ ኦሪት ደጃፍ ሁነው ያለቅሱ ነበር፤

፯፤ ወሶበ ርእየ ፊንሐስ ወልደ አልዓዛር ወልደ አሮን ካህን ተንሥአ እማዕከለ ትዕይንት ወነሥአ ረምሐ በእዴሁ፣

የአሮን የልጁ የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስም ይህን ባየ ጊዜ በእጁ ዘገሩን ይዞ ከሠራዊቱ መካከል ተነሣ፣

፰፤ ወቦአ ወተለዎ ለውእቱ ብእሲ እስራኤላዊ ውስተ እቶን ወረገዞሙ ለክልኤሆሙ ለውእቱ ብእሲ እስራኤላዊ መንገለ ሐቋሁ ወለይእቲ ብእሲት መድናዊት ወግአ እንተ መንገለ ኃፍረታ፣

ያን እስራኤላዊ ሰው ተከተሎት፣ ወደ ማዕድ ቤት ገብቶ የማይገባ ሥራ ስለሠራ ያን እስራኤላዊ ወገቡን ወጋው፣ ያችን የምድያም ሴትም ማኅፀኗን ወጋት፤

ወነደገ መቅሠፍት እምእስራኤል፣



ስለዚህም መዓቱ ከእስራኤል ጸጥ አለ፤

፱፤ ወኮኑ እለ ሞቱ በውእቱ መቅሠፍት ክልኤቱ እልፍ ወአርብዓ ምእት፣

በዚያም መቅሠፍት የሞቱት ሰዎች ሁለት እልፍ አራት ሺህ (ሃያ አራት ሺህ) ሆኑ፤

፲፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤

ፊንሐስ ወልደ አልዓዛር ወልደ አሮን ካህን አኅደገኒ መዓትየ እምደቂቀ እስራኤል፤

የአሮን የልጁ የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስ በእስራኤል ልጆች የተቆጣሁትን ቁጣ አበረደልኝ፤

፲፩፤ እስመ ቀንዓ ሊተ ቅንዓትየ ላዕሌሆሙ ወኢያጥፋዕክዎሙ ለደቂቀ እስራኤል በቅንዓትየ፣

ለአምልኮቴ የቀናሁትን ቅንዓት እሱ በነሱ ላይ ቀንቶ አጥፍቶልኛልና እኔ ለአምልኮቴ ቀንቼ የእስራኤልን ልጆች አላጠፋኋቸውም፤

፲፪፤ ወከመዝ እቤ ናሁ አነ እሁቦ ሕገ ሰላም፣

እንዲህ ስላደረገ እኔም እነሆ ሕገ ክህነትን እሰጠዋለሁ አልኩ፣ ሦስት መቶ ዘመነ ክህነት ተሠጥቶት ገዝቷልና፤

፲፫፤ ወይኩኖ ሎቱ ወለዘርኡ እምድኅሬሁ ሕገ ክህነት ዘለዓለም እስመ ቀንዓ ለአምላኩ ወአስተሥረየ ለደቂቀ እስራኤል፣

ለአምላኩ ቀንቷልና፣ የእስራኤልን ልጆች ኃጢአትም አስተሥርይዋልና ለሱ ከሱም በኋላ ለልጆቹ ሕገ ክህነት የዘለዓለም ይሆነው ዘንድ እሰጠዋለሁ፤

፲፬፤ ወስሙ ለውእቱ ብእሲ እስራኤላዊ ዘተቀትለ ምስለ መድናዊት ዘንበሪ ወልደ ሐሎ መልአኮሙ ለሕዝበ ስምዖን፣

የሚዶንን ሴት ሲነጥቅ ተገኝቶ የሞተው ሰው ስሙ የስምዖን ወገኖች አለቃ የሚሆን የሐሎ ልጅ ዘንበሪ ነው፤

፲፭፤ ወስማ ለይእቲ ብእሲት መድናዊት እንተ ተቀትለት ከስቢ ወለተ ሱር መልአኮሙ ለሕዝበ ሳሞት ዘቤተ አበዊሆሙ ውእቱ ለምድያም ፤

የሞተችው የምድያም ሴት የምትሆን የዚያችም ሴት

www.ethiopianorthodox.org

ስሟ የምድያም ሰዎች የአባቶቻቸው ወገን የሳሞት ነገድ አለቃ የሚሆን የሱር ልጅ ከስቢ ናት፤

፲፮፤ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፣

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤

፲፯፤ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ተፃረርዎሙ ለመድናውያን ወቅትልዎሙ እስመ እሙንቱ ይፃረሩክሙ በጕሕሉት፣

የምድያምን ሰዎች ተዋግታችሁ አጥፏዋቸው ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው፣ እነሱም በተንኮላቸው በጣያታቸው ያጠፏችኋልና፤

፲፰፤ ወኵሉ ዘይትጕሐለወክሙ በእንተ ፌጎር ወበእንተ ከስቢ ወለተ መልአከ ምድያም እኅቶሙ እንተ ተቀትለት አመ ዕለተ መቅሠፍት በበይነ ፌጎር፣

ጣዖት ስለ አመለኩ መቅሠፍት በታዘዘበት ቀን ስለሞተች እኅታቸው የምድያም አለቃ ልጅ ስለ ምትሆን ስለከስቢና ስለጣዖቱ የሚሸነግሏችሁንም ሁሉ አጥፏዋቸው ብለህ ንገራቸው አለው።

## ምዕራፍ ፳፮

፩፤ ወኮነ እምድኅረ መቅሠፍት ነበቦሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአልዓዛር ካህን፣

እስራኤል ከጠፉ በኋላ እንዲህ ሆነ፣ እግዚአብሔር ለሙሴና ለካህኑ ለአልዓዛር ነገራቸው፤

፪፤ ወይቤሎሙ ንሥኡ እምጥንቱ ውኍልቈ ኵሎ ተዓይኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ በበአብያቲሆሙ ኵሎ ዘይወፅእ ፀብዓ እምውስተ እስራኤል፣

ከሃያ ዘመን ጀምሮ እስከ ሐምሳ ዘመን ያለውን ለሰልፍ የሚወጣውን የእስራኤልን ሠራዊት ሁሉ ከሮቤል ጀምራችሁ ቍጠሩ አላቸው፤

፫፤ ወነገርዎሙ ሙሴ ወአልዓዛር በአራቦት ዘሞዓብ በኀበ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ኢያሪኮ፣

የኢያሪኮ አውራጃ በምትሆን በዮርዳኖስ አጠገብ ባለች በሞዓብ ዕፃ በአራቦት ሙሴና አልዓዛር ለሕዝቡ ነገሯቸው፤

፬፤ ወይቤልዎሙ ተፋቀዱ ዘእምዕሥራ ዓም ወላዕሉ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ፣



እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ከሃያ ዘመን ጀምሮ እስከ ሐምሳ ዘመን ድረስ ያሉትን እራኤልን ተቆጣጠሩ አሏቸው፤

፭፤ ወደቂቀ እስራኤል እለ ወፅኡ እምግብጽ ሮቤል በኵሩ ለእስራኤል፣

ከግብጽ የወጡ የእስራኤል ልጆች እሊህ ናቸው፣ የያዕቆብ የበኸር ልጁ ሮቤል ነው፤

ወደቂቀ ሮቤል ዘሄኖን ወነገደ ሄኖን ዘፋሉይ ነገደ ፋሉይ፣

የሮቤልም ልጆች እሊህ ናቸው፣ የሄኖን ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ የሄኖን ወገኖች የፋሉይ ወገኖች ተብለው የሚቈጠሩ ነገደ ፋሉይ፤

፮፤ ዘአስሮንሂ ነገደ አስሮኒ ወዘከርም ነገደ ከርሚ እሉ ሕዝብ ዘሮቤል፣

የአስሮኒ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ ነገደ አስሮኒ የከርሚ ነገድ ተብለው የሚቈጠሩ ነገደ ከርሚ የሮቤል ወገኖች እሊህ ናቸው፤

፯፤ ወኮነ ኍላቌሆሙ አርባዕቱ እልፍ ወሠላሳ ምእት ወሰብአቱ ምእት ወሠላሳ፣

ቍጥራቸውም አራት እልፍ ሦስት ሺህ ሰባት መቶ ሠላሳ (አርባ ሦስት ሺህ ሰባት መቶ ሠላሳ ነው)፤

፰፤ ወደቂቀ ፋሉ ኤልያብ ወደቂቀ ኤልያብ ናሙኤል ወዳታን ወአቤሮን፣

የፋሉ ልጅ ኤልያብ፣ የኤልያብ ልጆች ናሙኤል ዳታን አቤሮን ናቸው፤

፱፤ እሉ ዐበይተ ትዕይንት እለ ቆሙ ላዕለ ሙሴ ወአሮን ውስተ ትዕይንት ዘቆሬ አመ ተቃወሙ ላዕለ እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔርን በተቃወሙ ጊዜ ከቆሬ ወገኖች ጋር በአሮንና በሙሴ ላይ በጠላትነት የተነሡ የሠራዊቱ አበጋዞች እሊህ ናቸው፤

፲፤ ወአብቀወት ምድር አፉሃ ወውሕጠቶሙ ወለቆሬሂ ወሞቱ፣

ምድር ተከፍታ ዋጠቻቸው፣ ቆሬንም ዋጠችው፣ ሁሉም ሞቱ፤

ወለትዕይንቶሙሂ ክልኤቱ ምእት ወሐምሳ በልዓቶሙ እሳት ወኮኑ ለተአምር፣

ሁለት መቶ አምሳ የሚሆኑ ካህናቱን እሳት በላቻቸው፣ ለምልክትም ሆኑ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፬፤ ወደቂቀ ጋድሂ በበሕዘቢሆሙ ዘሳፎን ነገደ ሳፎኒ ወዘሐግ ውስተ ነገደ ሐጊ ወዘሱኒ ውስተ ነገደ ሱኑይ፤

በየወገናቸው የሚቆጠሩ የጋድ ልጆች እሊህ ናቸው፤ የሳፎን ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የሳፎኒ ልጆች፤ የሐጊ ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የሐጊ ልጆች፤ የሱኒ ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የሱኑይ ልጆች፤

፳፭፤ ወዘአዚን ውስተ ነገደ አዚኒ ወዘሳደፍ ውስተ ነገደ ሳደፍይ፤

የአዚን ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የአዚኒ ልጆች፤ የሳደፍ ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የሳደፍይ ልጆች እሊህ ናቸው፤

፳፮፤ ወዘአሩሐድ ውስተ ነገደ አሩሐዲ ወዘአሩሔል ውስተ ነገደ አሩሔሊ፤

የአሩሐድ ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የአሩሐዲ ልጆች፤ የአሩሔል ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የአሩሔሊ ልጆች፤

፳፯፤ እሉ ሕዝብ ዘጋድ፤

የጋድ ወገኖች እሊህ ናቸው፤

ወኍላቌሆሙ አርባዕቱ እልፍ ወሐምስቱ ምእት፤

ቍጥራቸውም አራት እልፍ ከአምስት መቶ (አርባ ሺህ አምስት መቶ) ነው፤

፳፰፤ ወደቂቀ አሴርሂ በበሕዘቢሆሙ ዘኢያምን ውስተ ነገደ ኢያምኒ ወዘኢያሱ ውስተ ነገደ ኢያሱይ ወዘባርያ ውስተ ነገደ ባርይ፤

በየወገናቸው የሚቆጠሩ የአሴር ልጆች እሊህ ናቸው፤ የኢያም ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የኢያምኒ ልጆች፤ የኢያሱ ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የኢያሱይ ልጆች፤ የባርያ ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የባርይ ልጆች፤

፳፱፤ ወዘኮቦር ውስተ ነገደ ኮቦር ወዘምልክያል ውስተ ነገደ ምልክያል፤

የኮቦር ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የኮቦር ልጆች፤ የምልክያል ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የምልክያል ልጆች እሊህ ናቸው፤

፴፤ ወስማ ለወለተ አሴር ሳራ፤

የአሴር ልጅ ስሟ ሳራ ይባላል፤ ደግ ሴት ናትና ከወንዶች መካከል አነሳት፤

፴፩፤ እሉ ሕዝበ አሴር ወኍላቌሆሙ ሐምስቱ እልፍ ወሠላሳ ምእት ወአርባዕቱ ምእት፤



የአሴር ወገኖች እሊህ ናቸው፤ ቍጥራቸውም አምስት እልፍ ሦስት ሺህ ከአራት መቶ (አምሳ ሦስት ሺህ አራት መቶ) ነው፤

፴፪፤ ወደቂቀ ዮሴፍ በበሕዘቢሆሙ ምናሴ ወኤፍሬም፤

በየወገናቸው የሚቆጠሩ የዮሴፍ ልጆች ምናሴና ኤፍሬም ናቸው፤

፴፫፤ ወደቂቀ ምናሴ ዘማኪር ነገደ ማኪሪ፤

የምናሴ ልጆች የማኪር ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የማኪሪ ልጆች እሊህ ናቸው፤

ወማኪር ወለደ ገለዓድ ወዘገለዓድ ነገደ ገለዓዲ፤

ማኪርም ገለዓድን ወለደ፤ የገለዓዲ ነገድ ሁነው የሚቆጠሩ የገለዓድ ልጆች፤

፴፬፤ እሉ ደቂቀ ገለዓድ፤

የገለዓድ ልጆች እሊህ ናቸው፤

ዘአክያዜር ነገደ አክያዜር ወዘኬሌግ ነገደ ኬሌጊ፤

የአክያዜር ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የአክያዜር ልጆች፤ የኬሌግ ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የኬሌጊ ልጆች፤

፴፭፤ ወዘኢሳርልያ ነገደ ኢሳርያሊ ወዘሴኬም ነገደ ሴኬሚ፤

የኢሳርልያ ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የኢሳርያሊ ልጆች፤ የሴኬሚ ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የሴኬም ልጆች ፤

፴፮፤ ወዘሲማኤር ነገደ ሲማኢሪ ወዘአፌር ነገደ ኦፌሪ፤

የሲማኢሪ ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የሲማኢሪ ልጆች፤ የአፌር ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የኦፌር ልጆች፤

፴፯፤ ወለሰለጰአድ ወልደ ዖፌር አልቦቱ ደቂቅ ዘእንበለ አዋልድ፤

ለዖፌር ልጅ ለሰልጰአድ ግን ከሴቶች ልጆች በቀር ወንድ ልጅ አልተወለደለትም ነበር፤

ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆን መሐላ፤ ወኑሓ ወሄግላ ወሚልካ ወቴርሳ፤

የሰለጰአድ የሴቶች ልጆቹ ስማቸው መሐላ፤ ኑሓ፤ ሄግላ፤ ሚልካ፤ ቴርሳ ናቸው፤

፴፰፤ ዝንቱ ሕዝበ ምናሴ ወኍላቌሆሙ ሐምስቱ እልፍ ወዕሥራ ምእት ወሰብዓቱ ምእት፤

የምናሴ ወገኖች እሊህ ናቸው፤ ቍጥራቸውም አምስት እልፍ

www.ethiopianorthodox.org

ሁለት ሺህ ከሰባት መቶ (አምሳ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ) ነው፤

፴፱፤ ወእሉ ደቂቀ ኤፍሬም ዘሱታላ ነገደ ሱታላይ ወዘጣናህ ነገደ ጣናሂ፣

የኤፍሬም ልጆች እሊህ ናቸው፣ የሱታላይ ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የሱታላይ ልጆች፣ የጣናሂ ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የጣናህ ልጆች፤

፵፤ እሉ ደቂቀ ሱታላ ወዘአዴን ነገደ አዴኒ፣

የሱታላ ልጆች እሊህ ናቸው፣ የአዴኒ ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የአዴኒ ልጆች፤

፵፩፤ እሉ ሕዝብ ዘኤፍሬም፣

የኤፍሬም ወገኖች እሊህ ናቸው፤

ወኍላቌሆሙ ሠለስቱ እልፍ ወስሳ ምእት ወሐምስቱ ምእት፣

ቍጥራቸው ሦስት እልፍ ስድስት ሺህ ከአምስት መቶ (ሠላሳ ስድስት ሺህ አምስት መቶ) ነው፤

፵፪፤ ወእሉ ሕዝብ ዘደቂቀ ዮሴፍ በበነገዶሙ፣

በየነገዳቸው የሚቆጠሩ የዮሴፍ ልጆች እሊህ ናቸው፤

፵፫፤ ወደቂቀ ብንያም በበነገዶሙ ዘበዓል ነገደ በዓሊ ወዘአሴቤር ነገደ አሴቤሪ ወዘአኪራን ነገደ አኪራኒ ወዘሰፊን ነገደ ሰፊኒ፣

በየነገዳቸው የሚቆጠሩ የብንያም ልጆች እሊህ ናቸው፣ የበዓሊ ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የበዓሊ ልጆች፣ የአሴቤሪ ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የአሴቤሪ ልጆች፣ የአኪራኒ ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የአኪራኒ ልጆች፤ የሰፊኒ ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የሰፊን ልጆች እሊህ ናቸው፤

፵፬፤ ወኮኑ ደቂቀ በዓል አዴር ወኑኃሚን ወዘኑሐሚን ነገደ ኑሐሚን ፣

የበዓሊ ልጆች አዴር ኑኃሚን ናቸው፣ የኑሐሚን ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የኑኃሚኒም ልጆች እሊህ ናቸው፤

፵፭፤ እሉ ደቂቀ ብንያም በበነገዶሙ ወኍላቌሆሙ አርባዕቱ እልፍ ወሐምሳ ምእት ወሰብዓቱ ምእት፣

በየነገዳቸው የሚቆጠሩ የብንያም ልጆች እሊህ ናቸው፣ ቍጥራቸውም አራት እልፍ አምስት ሺህ (አርባ አምስት ሽህ ሰባት መቶ) ነው፤

፵፮፤ ወደቂቀ ዳንሂ በበነገዶሙ ዘዓሣ ነገደ ዓሣ፣



በየወገናቸው የሚቆጠሩ የዳን ልጆች እሊህ ናቸው፣ የዓሣ ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የዓሣ ልጆች እሊህ ናቸው፤

፵፯፤ እሉ ሕዝብ ዘዳን በበነገዶሙ ወኍላቌሆሙ ለኵሉ ነገደ ዳን ሰብእቱ እልፍ ወሐምሳ ምእት ወአርባዕቱ ምእት፣

በየነገዳቸው የሚቆጠሩ የዳን ወገኖች እሊህ ናቸው፣ ቁጥራቸውም ሰባት እልፍ አምስት ሺህ ከአራት መቶ (ሰባ አምስት ሺህ አራት መቶ) ነው፤

፵፰፤ ወደቂቀ ንፍታሌምሂ በበነገዶሙ ዘአሴሔል ነገደ አሴሔሊ ወዘጎሄን ነገደ ጎሄኒ፣

በየነገዳቸው የሚቆጠሩ የንፍታሌም ልጆች እሊህ ናቸው፣ የአሴሔሊ ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የአሴሔል ልጆች፣ የጎሄን ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የጎሄኒ ልጆች፤

፵፱፤ ወዘዬሴር ነገደ ዬሴሪ ወዘሴሌም ነገደ ሴሌሚ፣

የዬሴር ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የዬሴሪ ልጆች፣ የሴሌም ነገድ ተብለው የሚቆጠሩ የሴ ሌሚ ልጆች፤

፶፤ እሉ ሕዝብ ዘንፍታሌም ወኍላቌሆሙ አርባዕቱ እልፍ ወሐምሳ ምእት ወአርባዕቱ ምእት፤

የንፍታሌም ወገኖች እሊህ ናቸው፣ ቍጥራቸውም አራት እልፍ ከአምስት ሺህ ከአራት መቶ (አርባ አምስት ሺህ አራት መቶ) ነው፤

፶፩፤ ወዝንቱ ኍላቌሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ስሳ እልፍ ወዓሠርቱ ምዕት ወሰብዓቱ ምእት ወሠላሳ፣

የእስራኤል ልጆች ቁጥራቸው ይህ ነው፣ ስሳ እልፍ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ከሠላሳ (ስድስት መቶ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሠላሳ) ነው፣ (ሐተታ) አበውን ቈጥሮ አልነበረምን፣ ውሉድን ለምን ቈጠራቸው ቢሉ አበው እኛ ከሞትን ልጆቻችን፣ ሚስቶቻችን ለብዝበዛ ይሆናሉ ቢሉ እናንተን አጥፍቼ ልጆቻችሁን አወርሳለሁ ብሏቸው ነበርና፣ ያ እንደ ተፈጸመ ለማጠየቅ ቈጠራቸው፤

፶፪፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ፣ ወይቤሎ፣

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤

፶፫፤ እሉ እለ ይወርስዋ ለይእቲ ምድር በበመክፈልቶሙ ወበበኍልቈ አስማቲሆሙ፤

ከሰልፍ የዋላችሁት ሁሉ በሰባተኛው ቀን ልብሳችሁን እጠቡ፤ ከኃጢአትም ትነ ጻላችሁ፤ ከዚህም በኋላ ወደ ከተማው ግቡ አላቸው፤

፳፭፤ ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፤

፳፮፤ ንሣእ መሠንየ ለዔዋ ወለምሕርካ እምሰብእ ወእስከ እንስሳ አንተ ወአልዓዛር ወመላእክተ አበዊሆሙ ለተዓይን፤

ከከብቱ ምርኮና ከሰዉ ምርኮ ያማረ ያማረውን፤ ከሰው ጀምሮ እስከ ከብት ድረስ ተቀበል፤ አንተና አልዓዛር የሠራዊቱ አባቶች አለቆች ሁናችሁ፤

፳፯፤ ወትከፍሎ ምህርካ ማዕከሎሙ ለእለ ፀብዑ ወለእለ ሖሩ ይትቃተሉ ማዕከለ ኵሉ ተዓይን፤

ሲዋጉ ወደ ሰልፍ በሄዱትና ከሰፈር በዋሉት መካከል ምርኮውን ክፈሉ፤

፳፰፤ ወታወፅኡ ጸባሕቶ ለእግዚአብሔር እምነቤሆሙ ለእለ ፀብዑ ወለእለ ሖሩ ይትቃተሉ አሐተ ነፍሰ እምነበ ኃምስቱ ምእት ሰብእ ወእምእንስሳ ወእም አልሕምት ወእምአባግዕ ወእም አዕዱግ፤

ሲዋጉ ወደ ሰልፍ ከሄዱት ከአምስት መቶ ሰዎች ለእግ ዚአብሔር ዓሥራት አንድ ሰው አውጡ ከላምና ከበግ ከፈረስና ከበቅሎ ከአህያም ከአምስቱ መቶ አንድ አንድ አውጡ፤

፳፱፤ ወትነሥእ እመንፈቆሙ ወትሁቦ ለአልዓዛር ካህን ቀዳም ያቲሁ ለእግዚአብሔር፤

ከእኩሌቶቹ ተቀብለህ የእግዚ አብሔርን ቀዳምያት ‹ዓሥ ራት› ለካህኑ ለአልዓዛር ስጠው፤

፴፤ ወእመንፈቆሙ ለደቂቀ እስራ ኤል ትነሥእ አሐደ እምነምሳ እምሰብእ ወእምአልሕምት ወእም አባግዕ ወእምአእዱግ ወእምእንስሳ ወሀቦሙ ለሌዋውያን እለ የዓቅቡ ሕገ ደብተራሁ ለእግዚአብሔር፤

ከእስራኤል ልጆች እኩሌታ ከሰዉም፤ ከላሙም፤ ከበጉም ከአህያውም፤ ከፈረሱም፤ ከበቅሎውም፤ ከአምሳው አንድ ተቀብለህ የእግዚአብሔር ማደ ሪያ የምትሆን የደብተራ ኦሪትን ሥርዓት ለሚጠብቁ ለሌዋውያን ስጣቸው አለው፤



‹ሐተታ› ከጓዝ የዋሉትና ከጦር የዋሉት ምርኮውን እኩል ይካፈላሉ፤ ከጦር ከዋሉት ከአምስት መቶው አንድ ተቀብሎ ለሊቀ ካህናቱ ለአልዓዛር ይሰጠዋል፤ ከጓዝ ከዋሉት ከአምሳው አንድ ተቀ ብሎ ለሌዋውያን ይሰጣቸዋል፤

፴፩፤ ወገብሩ ሙሴ ወአልዓዛር ካህን በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ፤

ሙሴና ካህኑ አልዓዛርም እግዚአብሔር ሙሴን እንዳ አዘዘው አደረጉ፤

፴፪፤ ወኮነ ኍልቈ አባግዕ ዘማህረኩ ዕደው እለ ፀብዑ ስሳ ወሰብዓቱ እልፍ ወኃምሳ ምእት፤

ወደ ሰልፍ የሄዱት ሰዎች የማረኩት የበጉ ቍጥር ስሳ ሰባት እልፍ አምስት ሺህ (ስድስት መቶ ሰባ አምስት ሺህ) ሆነ፤

፴፫፤ ወአልሕምት ሰብዓቱ እልፍ ወዕሥራ ምእት፤

ላሞቹም ሰባት እልፍ ሁለት ሺህ ‹ሰባ ሁለት ሺህ› ሆኑ፤

፴፬፤ ወአዕዱግ ሰብዓቱ እልፍ ወዓሠርቱ ምእት፤

ፈረሱና በቅሎው አህያውም ሰባት እልፍ አንድ ሺህ (ሰባ አንድ ሺህ) ሆኑ፤

፴፭፤ ወሰብእ ዘመንፈስ አንስት እለ ኢያእመራ ብእሴ ሠለስቱ እልፍ ወዕሥራ ምእት፤

ከወንድ ያልደረሱ የሴት አካል ያላቸው ሰዎችም ‹ደናግሉ›፤ ሦስት እልፍ ከሁለት ሺህ ‹ሠላሳ ሁለት ሺህ› ሆኑ፤ አንድም ወሰብእ ዘመንፈስ ወአንስት እለ ኢያእመራ ብእሴ ይላል፤ ከወንድ ያልደረሱ ሴቶ ችና እውቀት ያላቸው ወንዶች ሦስት እልፍ ሁለት ሺህ (ሠላሳ ሁለት ሺህ) ናቸው፤

፴፮፤ ወኮነ መንፈቀ ክፍሎሙ ለእለ ሖሩ ፀብዓ እምኍልቈ አባግዕ ሠላሳ ወሠለስቱ እልፍ ሰብዓ ምእት ወኃምስቱ ምእት፤

ከበጎች ቍጥር ወደ ሰልፍ የሄዱት ሰዎች ፈንታ ‹ድርሻ› ሠላሳ ሦስት እልፍ ከሰባት ሺህ ከአምስት መቶ (ሦስት መቶ ሠላሳ ሰባት ሺህ አምስት መቶ) ሆነ፤

፴፯፤ ወኮነ ጸባሕቱ ለእግዚአብሔር እምአባግዕ ሰብዓቱ ምእት ሰብዓ ወኃምስቱ፤

ከበጎች ለእግዚአብሔር የወ ጣው ሰባት መቶ ከሰባ አም ስት ሆነ፤

www.ethiopianorthodox.org

፶፩፤ ወነሥኡ ሙሴ ወአልዓዛር ካህን ውእተ ወርቀ እምኔሆሙ ወኵሎ ሠርጐ ወርቅ ዘግቡር፤

ሙሴና ካህኑ አልዓዛርም ያን ወርቅና የተሠራውን የወርቅ ጌጥ ከነሱ ተቀበሉ፤

፶፪፤ ወኮነ ኵሉ ወርቅ ዘመባእ ዘፈለጡ ለእግዚአብሔር እልፍ ወስሳ ምእት ወሰብዓቱ ምእት ወኃምሳ በሰቅል እምኀበ መላእክተ ዐሠርቱ ምእት ወመላእክተ ምእት፤

ከመቶ አለቆችና ከሺህ አለቆች የተቀበሉት ለእግዚአብሔር ለይተው ያገቡት ወርቅ ሁሉ በሚዛን በቤተ እግዚአብሔር ዓዋቂ› አንድ እልፍ ከስድስት ሺህ (ዓሥራ ስድስት ሺህ ከሰባት መቶ ከኃምሳ) ሆነ፤

፶፫፤ ወእልክቱሰ ዕደው እለ ፀብዑ አዕተዉ ለለርእሶሙ ዘሰለቡ፤

ከጦር የዋሉት እሊህ አርበኞች ግን የዘረፉትን ገንዘብ በየራሳቸው አገቡ፤

፶፬፤ ወነሥኡ ሙሴ ወአልዓዛር ካህን ውእተ ወርቀ እምኀበ መላእክተ ዐሠርቱ ምእት ወእም ኀበ መላእክተ ምእት ወአብኡ ውስተ ደብተራ መርጡል ተዝ ካሮሙ ለደቂቀ እስራኤል፤

ሙሴና ካህኑ አልዓዛርም ከሺህ አለቆችና ከመቶ አለቆች ያን ወርቅ ተቀብለው ለእስራ ኤል ልጆች መታሰቢያ ሊሆን ወደ ደብተራ ኦሪት አገቡት።

## ምዕራፍ ፴፪

፩፤ ወቦሙ ለደቂቀ ሮቤል ወለ ደቂቀ ጋድ ብዙኅ እንስሳ ጥቀ፤

ለሮቤል ልጆችና ለጋድ ልጆች ብዙ ከብት ነበራቸው፤ ሐታታ አሁን ኢያዜርን አይተው የከብት አገር ናትና ሙሴን ስጠን አሉት የሚል ነውና እንደ አርእስት አንሥ ቷቸዋል፤

ወርእይዎ ለብሔረ ኢያዜር ወለ ብሔረ ገለዓድ ከመ ብሔረ እንስሳ ብሔሩ፤

የገለዓድን አገርና የኢያዜርን አገር አገሩ የከብት አገር እንደ ሆነ አይተው፤

፪፤ ወመጽኡ ደቂቀ ሮቤል ወደቂቀ ጋድ ወይቤልዎሙ ለሙሴ ወለ አልአዛር ካህን ወለመላእክተ ተዓይን እንዘ ይብሉ፤

የሮቤል ልጆችና የጋድ ልጆች መጥተው ለካህኑ ለአልአዛርና ለሙሴ ለሠራዊቱም አለቆች እንዲህ አሏቸው፤



፫፤ አጣሮታ ወዴቦን ወያዜር ወናምራ ወሐሴቦን ወእልያሴ ወሴባማ ወናባው ወብያን፤

አጣሮታና ዴቦን፣ ያዜርና ናምራ፣ ሐሴቦንና እልያሴ፣ ሴባማና ናባው፣ ብያን የተ ባሉት አገሮች፤

፬፤ ምድር ዘወሀበ እግዚአብሔር ቅድሜሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ምድረ እንስሳ እማንቱ ወብነ ለአግብርቲከ ብዙኅ እንስሳ፤

እግዚአብሔር በእስራኤል ልጆች ፊት የሰጠን እሊህ አገሮች የከብት አገሮች ናቸው፣ ለኛ ለባሮችህም ብዙ ከብት አለን፤

፭፤ ወይቤልዎ ለእመ ረከብነ ሞገሰ በቅድሜከ ሀበነ እላንተ በሐውርተ ለአግብርቲከ መክፈልተ ይኩናነ ወኢታዕድወነ ዮርዳኖስ፤

በፊትህ ባለሟልነትን አግኝ ተን እንደ ሆነ እሊህ አገሮች ለኛ ለባሮችህ ዕድል ፈንታ ይሆኑን ዘንድ ስጠን፣ ዮር ዳኖስንም አታሻግረን አሉት፤

፮፤ ወይቤሎሙ ሙሴ ለደቂቀ ሮቤል ወለደቂቀ ጋድ አኃዊክሙ የሐውሩ ይትቃተሉ ወአንትሙሰ ትነብሩ ዝየ፤

ሙሴም የጋድን ልጆች፣ የሮ ቤልን ልጆች ወንድሞቻችሁ ሊዋጉ ይሄዳሉ፣ እናንተ ግን ከዚህ ትቀመጣላችሁ አላ ቸው፣ የቀጣ አነጋገር ነው፤

፯፤ ወለምንት ትገፈትዑ ልቦሙ ለደ ቂቀ እስራኤል ከመ ኢይሑሩ ውስተ ምድር ዘይሁቦሙ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር ወደሚሰጣቸው አገር እንዳይገቡ የእስራኤልን ልጆች ልቡና ለምን ታሰንፉላ ችሁ፤

፰፤ አኮኑ ከመዝ ገብሩ አበዊክሙ አመ ፈነውክዎሙ እምቃዴስ በርኔ ከመ ይርአይዋ ለይእቲ ምድር፤

ያችን አገር ያዩዋት ዘንድ ከቃዴስ በርኔ በላክኋቸው ጊዜ አባቶቻችሁ እንዲህ ያደረጉ አይደለምን፤

፱፤ ወዓርጉ ኀበ ቈላተ አጽቅ ከመ ይነጽርዋ ለይእቲ ምድር ወሜጥዎ ለልቦሙ ለደቂቀ እስራኤል ከመ ኢይባኡ ውስተ ይእቲ ምድር ዘይሁቦሙ እግዚአብሔር ፤

ያችን አገር ያዩዋት ዘንድ የወይን ሐረግ ወዳለበት ቆላ ወጥተው እግዚአብሔር ወደ ሚሰጣቸው ወደ ዚያች አገር

www.ethiopianorthodox.org

